# አበሻን የማቅናት ዘመቻ
# (ፉቱሕ አልሐበሽ)

## የኢማም አህመድ ቢን ኢብራሒም አልጋዚ

(አሕመድ ግራኝ)
ከአረብኛ ወደ አማርኛ የተተረጐመ
እውነተኛ ታሪክ

አንደኛ መጽሐፍ ቅፅ 2
ህዳር1995

# አበሻን የማቅናት ዘመቻ
# (ፉቱሕ አልሐበሽ)

የኢማም አህመድ ቢን ኢብራሒም አልጋዚ
(አሕመድ ግራኝ)
ከአረብኛ ወደ አማርኛ የተተረጐመ
እውነተኛ ታሪክ

አንደኛ መጽሐፍ ቅፅ 2
ኅዳር 1995

አማርኛውን ቅጂ አሳታሚ
ሜጋ ማስታወቂያ ኢንተርፕራይዝ

© የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
ALL WRIGHTS RISERVED
1995



# ደራሲ

*ሸሃቡዲን አህመድ ቢን አብዱልቃድር*
*ቢንሳሊም - ቢን ዑስማን አልጂዛኒ*
(ዓረብ ፊቂህ) በሚል ቅጽል ስም የሚታወቅ

የዓረብኛ ቅጅ አሳታሚ
የግብፅ መጽሀፍት ድርጅት
1974 (እ.ኤ.አ.) - 1394 ዓመተ ሂጅራ
አማርኛ ትርጉም
*ሐሰን ታጁ ለጋስ*

የአማርኛ ትርጉም ዕርማት
*ሬድዋን አብደላ ኢብራሂም*

የአማርኛ አርትኦት
*መኩሪያ መካሻ*

የኮምፒውተር ለቀማና ሌይ አውት
*መልካምሥራ ለማ*

የትርጉምና የህትመት አስተባባሪ
*መሠለ መኮንን እሸቴ*

# ማስታወሻ

በአረብኛ ፋቱሕ አልሐበሽ የተባለውን ወደ አማርኛ አበሻን የማቅናት ዘመቻ አንደኛ መጽሐፍ ቅጽ አንድ በህዳር 1994 ታትሞ ሲወጣ በገባነው ቃል መሠረት ቅጽ ሁለት እነሆ የህትመት ብርሃን አይቶአል:: እኛም ቃላችንን ጠብቀናል:: ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ታሪክ አንድ አካል ከመሆኑም ሌላ የኢትዮጵያዊው አህመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ በቅፅል ስም አህመድ ግራኝ የመሪነት ተጋድሎአቸውን በዝርዝር ይዟል:: በመጽሐፉ ውስጥ ያለው ታሪክ በወቅቱ በያንዳንዱ የአህመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ (አህመድ ግራኝ) መሪነት የተሰለፈውን ማህበረሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ተካፋይና የአይን ምስክር በነበረው ሽሀቡዲን አህመድ (አረብ ፋቂህ) በተባለ ሰው የተጻፈ በመሆኑ እውነተኛነቱ የማያጠራጥር ነው::

የዚህ መጽሐፍ ከአረብኛ ወደ አማርኛ የመተርጎሙ ምክንያት ታሪኩ አህመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚና የተገኙበት ሕብረተሰብ ታሪክ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ታሪክ በመሆኑ ሁሉም አንብቦ እንዲረዳው በማሰብ ነው:: የኢትዮጵያ ታሪክ የብሔር ብሔረሰቦች አጠቃላይ ታሪክ ነውና::

በአንደኛው መጽሐፍ ቅፅ አንድ ጥቂት ከእርማት ያመለጡ የፊደል ግድፈቶች ሳይታረሙ እንዳሉ ታትመዋል:: ለዚህም የፊደል ግድፈት ይቅርታ እንጠይቃለን::

አሁንም እንዳለፈው ቅፅ አንድ ሁሉ ይህን መጽሐፍ ለህትመት ለማብቃት የሐረር ብሄራዊ ጉባኤ ፋይናንስ በመመደብ ላደረገው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ምሥጋና ሊቸረው ይገባል:: ለሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጉባኤዎችና ክልሎች ምሣሌ የሚሆን ተግባር ነውና::



በቅጽ አንድ መጽሐፍ ላይ በመመርኮዝ በዛ ያሉ አስተያየቶች ደርሰውናል:: እናመሠግናለን:: ከተሰጡን አስተያየቶች የአፃፃፍ ስልቱን በተመለከተ ለዘመናዊ አንባቢ የሚጐረብጥ የቃላት አጠቃቀም ነው የተጠቀማችሁት የሚል ይበዛል::

በመሠረቱ የኛ ተልዕኮ ከአረብኛ ወደ አማርኛ በቀጥታ መተርጐም ነው:: መጽሐፉ በአረብኛ የተፃፈው ከጥቂት መቶ አመታት በፊት በመሆኑ በወቅቱ ፀሐፊው የተጠቀመውን የቃላት አጠቃቀም እንዳለ ተርጉመነዋል::

አበሻን የማቅናት ዘመቻ ብለን የሰየምነው ይህ መጽሐፍ በሁለት ቅጽ አትመን ለማውጣት ብዙ ውጣ ውረዶችና እንቅፋቶች አልፈናል::

በዚህ መጽሐፍ የትርጉምና የህትመት ሥራ ላይ ድጋፋቸውን ለሰጡን ማስጋናችን ይድረሳቸው:: በተለይ የአሳታሚነት ሃላፊነቱን የወሰደውን የሜጋ ማስታወቂያኢንተርፕራይዝ ከአረብኛ ወደ አማርኛ የተረጐመውን አቶ ሐሰን ታጁ አርታኢውን መኩሪያ መካሻ፣ ጊዜያቸውን ሰጥተው በአላቸው የቋንቋ ችሎታ የእርማት አገልግሎት የሰጡንን አቶሬድዋን አብደላን የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥትንና የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላትና የጽ/ቤት ሠራተኞች ምስጋናችን ይድረሳቸው::

በመጨረሻም የኢማም መሐመድ ቢን አልጋዚ ታሪክ የተፃፈው በሁለት መጽሐፍ እንደሆነ የታሪክ መሃደሮች ይናገራሉ:: ይህ በሁለት ቅጽ ያተመነው አንደኛውን መጽሐፍ ሲሆን ሁለተኛውን መጽሐፍ ልናገኘው አልቻልንም መጽሐፉን አለኝ ወይም ያለበትን አውቃለሁ የሚል ከተገኘ በአድራሻችን ቢጽፍልን ተርጉመን

አትመን ለማውጣት ዝግጁ ነን፡፡ ወሮታም እንከፍላለን፡፡ በዚህ አጋጣሚ የሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ታሪክ የትርጉምም ሆነ ጥናታዊ ሥራ አትመን ለማውጣት ዝግጁነታችንን እንገልፃለን፡፡ ለዚሁም የሌሎች ጉባኤዎችና ክልሎች ድጋፍ እንሻለን፡፡ ስለመጽሐፉ ያላችሁን አስተያየትም ሆነ ሌሎች መልዕክቶች በአድራሻችን ላኩልን፡፡

አድራሻችን፡- የፉቱሕ አልአበሻ መጽሐፍ
የትርጉምና የህትመት አስተባባሪ
የፖሣቁ 100192
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

መልካም ንባብ፡፡


መሠለ መኩንን
አስተባባሪ



# መታሰቢያ

በአፄው ዘመነ መንግሥት የዚህን መጽሐፍ አረብኛ ቅጅ ይዞ የተገኘ ሰው እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ ይታሠር፣ ይገረፍ፣ ይጋዝ እንደነበረ የታሪክ ሠነዶች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም በወቅቱ የዚህ መጽሐፍ ጦስ ሰለባ የሆኑና እስከ አሁን በሕይወት ያሉ የሐረሪ ብሄረሰብ አዛውንቶች ይህንኑ ያረጋግጣሉ፡፡

ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ምክንያት ለታሠሩ፣ ለተሠደዱ፣ ለተሰቃዩና በተለይ የደረሰባቸውን ሁሉ ተቋቁመው የአረብኛው መጽሐፍ ቅጂ ደብቀው ለአሁኑ ትውልድ ላስተላለፉ የሐረሪ ብሄረሰብ አባላት የዚህ መጽሐፍ መታሠቢያነት ተሠጥቷል፡፡



የአህመድ ግራኝ አመፅ
ከ1524 እስከ 1543
መግለጫ
የዘመቻ ስምሪት ከሐረር 1524-1532
የዘመቻ ስምሪት ከጸብረ ብርሃን 1532
ቤተክርስቲያን
ጦር ሜዳዎች
የዘመቻው የሐረር መምሪያ 1524-15
የዘመቻው የደብረ ብርሃን መምሪያ 15
የዘመቻው የዋጅ መምሪያ 1532
የዘመቻው የጸጥር መምሪያ 1532
የዘመቻው የአክሱም መምሪያ 1533
የአህመድ መንግሥት የጸምቢያ ማዕከል
መሥፈርት 1:8,250,000
የጦር ሜዳ ስምና ዓመት
1-አካም ............... 1524
2-ባደቄ ............... 1528
3-ሽምብራ ኩሬ ........ 1529
4-አደፈርስ ............ 1531
5-ዝሆንበር ........... 1531
6-ዋበል ............... 1531
7-አምባ ግሼን ......... 1531
8-የደብረ ብርሃን ሰልፍ ... 1532
9-ዜላሀ /ባሌ/ ........ 1532
10-አክሱም ............ 1533
11-ሰራዬ .............. 1534
12-ሽሬ ............... 1535
13-ወገራ .............. 1535
14-በጌምድር ........... 1535
15-ጣና ............... 1536
የቤተክርስቲያን ስምና ዓ.
1-ደብረ ሊባኖስ
2-መካነ ሥላሴ
3-አትርኖስ ማርያም
4-ደብረ ነጎድጓድ
5-ቤተሰማደት
6-ገነተ ጊዮርጊስ
7-ደብረ እግዚአብሔር
8-የሐይቅ ደብረ እስጢፋኖስ
9-ላሊበላ
10-አባላሙኤል
11-ደብረ ገሊላ
12-መርጡለ ማርያም
የአደን ባሕረ ሰላጤ
የተለያዩ የሶማሌ ጎሳዎች
ምንጭ Arab-Faqih, Histoire De la Conquete De L Abyssinie

## ኢማሙ ከበሽታቸው መፈወሳቸው በረመዳን 23 ቀን 937 ሂጅሪያ ነበር

እንደ ሂጅሪያ የዘመን አቆጣጠር በ938 ከረመዳን ወር 23ኛው ቀን በኋላ ኢማሙ ከበሽታቸው ተፈውሰው የሐበሻን ንጉስ በመሻት ወደ ዳሞት ለማቅናት አሰቡ:: የጉዞውን ጉዳይ በሚመለከት አብረዋቸው ካሉት ሙስሊሞች ጋር ምክክር አደረጉ:: ሙስሊሞችም:- "አሁን እዚህ ደርሰናል:: ከዚህ በኋላ የዳሞት ምድር ሩቅ ነው:: መንገዱን አንዳችንም አናውቀውም:: ቃፊርም የለንም:: ወረብም ረግረጋማ እና በኢአማንያን እርሻ የተሞላ" እንዲሁም ፈረሶችና በቅሎዎችን እያደለጠ የሚጥል መሬት ነው" በማለት ወደዚያ ላለማቅናት ምክንያቶችን አቀረቡ:: ኢማሙም ይህን ምክንያታችሁን ተዉት:: ወደ አገራችሁ መሄድ ትሻላችሁ በማለት ከአሚር ሑሴን ዘንድ የነበረውን ወደ እሥላምነት የገባ አንድ ሰው አስጠርተውት ስለመንገዱ ሁኔታ ሲጠይቁት፣ እኔ ሐበሻን በሙሉ አውቃታለሁ:: የወረብን፣ የዳሞትን፣ የጐጃምን እስከ አክሱም ድረስ እወስዳችኋለሁ:: የምትሹትን ቦታ እመራችኋለሁ አላቸው:: ኢማሙ መርቀውት ልብስም አጠለቁለት::

## ወረብ ምድር በመግባት ዙራራህ ከተማ ውስጥ መስፈራቸው

ሙስሊሞች ጉዞ በማድረግ ወረብ ምድር ውስጥ ገብተው ዙራራህ ከትምባል መንደር ሠፈሩ:: ዙራራህ ከግብጽና ካሻም (ሦሪያ) የሚመጡ የክርስቲያን ነጋዴዎችና እነርሱ ከሐበሻ የወለዷቸው ልጆቻቸው የሚኖሩባት ትልቅ ከተማ ናት:: አየሯ ተስማሚ በመሆኑ ይወዷታል::

የሐበሻው ንጉሥና አበጋዛቸው ወሰን ሠገድ አብረው ሳለ አበጋዙ ለንጉሡ እንዲህ አለ፦ ሙስሊሞቹ በአሁኑ ወቅት ከበስተጀርባችን ናቸው:: ጠቅላላችን ወደ ምድረ ዳሞት ከሄድን የዳሞት ምድር ጠባብ ናት፣ ሙስሊሞችም እኛን መከተላቸው አይቀርም:: እኔ ከሙስሊሞቹ በስተጀርባ እመለስና ወደአገራቸው አቅጣጫ አመራና፣ ወደ አገራቸው መሄዴን ካወቁ ደዋሮ እስኪደርሱ አስመስዬባቸው፣ ከዚያም ተበታትነው ወደ አገራቸው ይመለሳሉ:: እኔም ከዚያ ወደ እርስዎ እመለሳለሁ፤ አላቸው:: ንጉሱ ወሰን ሰገድ ባቀረበው ሐሳብ በመስማማት ወደ ዳሞት ሲያቀኑ፤ ወሰን ሰገድ ደግሞ ወደ ደዋሮ በማምራት ወጅ ምድር ገብቶ አልማያ ከተባለው ቦታ ከላይ በኩል ከሙስሊሞች በስተኋላ ሰፈረ:: ሙስሊሞቹ እንደሆኑ በዘርራራ ለ15 ቀናት ያህል እንደተቀመጡ ከኢማሙ ሰላዮች ተመልሰው የመጡት ንጉሡ ዳሞት ምድር መግባቱን ለኢማሙ አስታወቁአቸው:: ወሰን ሰገድም አገራችሁን የሚያጠቃ በመምሰል አታሎ እንድትከተሉት ሊያደርጋችሁ ወጅ ገብቶ ተቀምጧል:: እርሱን ተከትላችሁ ደዋሮ ስትደርሱ ወታደሮቻችሁ በሙሉ ይበታተናሉ:: ይህን አሲሮባችኋል:: ስለዚህ ማድረግ ያለባችሁን ወስኑ" አሏቸውም:: ኢማሙም ለሙስሊሞች "የክርስቲያኖች ቁንጮ የሆነውን ንጉሳቸውን በመሻት እንንቀሳቀሳለን:: ወደ ዳሞት ምድርም እንከተዋለን:: ወሰን ሰገድ እኛ ወደ ዳሞት ማምራታችንን ከሰማ እርሱም ጌታውን ለመርዳት ዳሞት ድረስ ይመጣል:: አለዚያም እዚያው ካለበት ይቀመጣል:: ካለበት ከተቀመጠ ወደ ሀገራችን ቢዘልቅም ግድየለንም:: ከቻለ ይሞክረው:: እኛ ግን የሐበሻውን ንጉስ ከገባበት ገብተን እናሳድደዋለን" በማለት ተናገሩ:: እንዲህም ሆነና ሙስሊሞች ወደ ዳሞት በማቅናት ዊዝ ከተማ ደረሱ::





ዊዝ ሐበሻ ውስጥ አምሳያ የማይገኝለት ትልቅ ገበያ ያለበት ታላቅ ከተማ ነው:: ገበያተኞቹ በወርቅ እንጂ አይገበያዩም::

ሙስሊሞች ዊዝን ለቀው ወደ ቁብ ምድር አመሩ:: ቁብንም አልፈው ምስር መሽክ ከተማ ገቡ:: መሽክ ማለት በአገሬው አነጋገር ጠባብ በር ማለት ነው:: ምስር ከዳሞት የአንዷ ከተማ ስም ናት::

ሙስሊሞች ከምስር መሽክ በላይ ቆሙ:: ኢማሙ ለሙስሊሞች እንዲህ አሉዋቸው፦ ማለፍ ትችሉ ዘንድ ይህንን በር አስፉት:: ቋጥኞችን አንከባሉ:: ዛፎችንም ቁረጧቸው ሲሉ አዘዟቸው:: የታዘዙትን አደረጉ:: "ወይዘሩህ" ገበያ ላይም አነጉ::

## የሐበሻው ንጉስ ኢማሙ ወደ እሱ ማምራታቸውን ሲያውቅ መከላከያ በሚሆን ተራራ መመሽጉ

የሐበሻው ንጉሥ፣ ሙስሊሞች የ"ዳሞክት" ምድርን መያዛቸው ዜና እንደደረሰው፣ አንድ መተላለፊያ መንገድ ያለው ተከላካይ የሆነ ጋራ ላይ ሠፈረ:: መተላለፊያው ላይ ያለ በር በምድረ ዳሞት "ጉራጌ" ተብሎ ይጠራል:: ከጋራው ላይ ሠራዊቱን አዘጋጀ:: የፈጥጋሩን አውራዒ ዑስማን ቢንዳር፣ ሠራዊቱን ይዞ በሩን እንዲጠብቅ በአዛዥነት አስቀመጠው፣ ይህ ሰው በዚያን ወቅት ከእሥልምና የወጣ ከሃዲ ነበር:: ከነሠራዊቱ ከበሩ እንዳይነቃነቅም ንጉሡ አዘዘው:: ንጉሡም ከጋራው በአንዱ በኩል "ዶኾን ዳውር" የተባለ ሥፍራን ያዘ:: የሥፍራውም መጠሪያ ትርጉሙ የዝሆን ማረፊያ ማለት ነው::

ሙስሊሞች "ወይዘሩህ" ገበያን አልፈው "ጉራጌ" ከተባለው በር በታች ሰፈሩ:: ከኢአማንያን ጋር በበሩ

በኩል ተያዩ:: በዚህ ጊዜ ኢአማንያን ከበሩ በላይ ረድፍ ያዙ:: ሙስሊሞች በበኩላቸው ኢአማንያንን ሲያዩ ምክክር ያዙ:: ዓድሊ፣ በለው ዓብድና ተከታዮቻቸው "መንገዱንም በሩንም ዘግተውብናል:: ከዚህ ውጭም ሌላ መንገድ የለም:: ስለዚህ ከእዚሁ አድረን በመድፍ እንወራቸዋለን:: በነገው ቀን ውጊያ እንገጥማቸዋለን:: አሚር ዘህረቦች ሙሐመድ፣ ዐብዱናስር፣ እና ገራድ አሕሙሻ በዚያን ወቅት እንዲህ አሉ:- ከዚህ ካደረንማ አቢጋዝ ወሰን ሰገድ ከኋላችን ደርሶ "መሰር መሸክ" በርን ይዘጋብናል:: በሁለት ጋራዎች መሐል እንሆናለን:: መውጣትም ወደጋራው መዝለቅም አንችልም:: ስለዚህ አሁኑኑ ውጊያ እንጀምርና እናውጣቸው:: አላህ ድልን ያጐናጽፈናል አሉ:: ኢማሙም ..እናንተ ያቀረባችሁት ሐሳብ መልካም ነው፤ በማለት የመጀመሪያውን ሐሳብ ውድቅ አደረጉና ወታደሮቻቸውን ለውጊያ አዘጋጁ::

## የኢማም አህመድ ወደ ንጉሡ ጦር ሰፈር ዘልቀው መግባት፣ የንጉሡ ጦር መሸነፉና ንጉሡ ለመሸሽ መገደዱ

ኢማሙና ሠራዊታቸው ከሓዲው አውራዒ ዑስማን ወደሚገኝበት በር ተመሙ:: ሙስሊሞችና ኢአማንያን ተፋጠጡ:: በዚህ ጊዜ ኢማሙ ይህን በር ትተው ከወታደሮቻቸው ጋር ንጉሡን በመሻት ወደ "ሡሄል" አቅጣጫ ወደ "ዶኾን ደውር" አመሩ:: አውራዒ ዑስማን ባለበት በር በኩል ዓድሊን አስቀምጠው ሠራዊቶቻቸውን ይዘው "ዶኾን ዶውር" ሥፍራ ሲደርሱ ንጉሡ የሙስሊሞችን እዚያ መድረስ ፈጽሞ አላወቀም ነበር:: ቦታው ጠባብና ማንም የማያውቀው በመሆኑ ነው:: ይህም በመሆኑ ነው ንጉሡ





እዚያ ተማምኖ መኖርን የመረጠው:: ማንም "ዶኾን ደውር" ይደርሳል ብሎ አልጠበቀም:: ኢማሙ ከዚያ ሲደርሱ በእሾህና በዛፎች የታጠረ ሦስት በሮችን አገኙ:: በሽምሱም የሚመራውን እግረኛ ወታደሮቻቸው ከአጥሩ እንጨትና እሾህ በላይ ጋሻዎቻቸውን በረድፍ በማስቀመጥ እነርሱን እየተረማመዱ በሩን አልፈው እጅግ ጠቃሚ የሆነ ቦታ ደርሰው ብቅ አሉ:: ከዚያም በሩን በመክፈትና የተዘጋበትን እንጨቶች ወደ ጐን በማድረግ ኢማሙና ጠቅላላው ሠራዊት እንዲገባ አደረጉ::

የሐበሻው ንጉስ ለትግራይ ሰዎች፤ ሙስሊሞች በሩን ከማለፋቸው በፊት ቀድማችሁ ደርሳችሁ ዝጉባቸው አላቸው:: ግን የትግራይ ሰዎች ወደበሩ ሲሄዱ በሙስሊሞች ተቀድመው ሲያገኙዋቸው፣ በሙስሊሞቹ አቅራቢያ ጠባብ በሆነ ቦታ ቆሙ:: ሙስሊሞችም ሲያዩዋቸው ፈረሰኞቻቸው ወደነርሱ ጋለቡ:: ከፈረሰኞቹም መሀል ሼክ ሚካኤል ኢብን፣ ሼኽ ደጅና፣ መታን ሱማሌው፣ ሠዬዲ ሙሐመድ፣ ዐብዱናስር፣ አውራዒ አቦኝ፣ አሚር አቡበከር፣ አውራዒ ዑስማን ቢን ዓሊ፣ ከቢር ሙሐመድ እነሱንም የመሳሰሉ አርባ ፈረሰኞች ይገኙባቸው ነበር::" በዚያው ይገኝ የነበረ ሸለቆን ተሻግረው፣ ወደ ክርስቲያኖቹ በመድረስ ሙስሊሞቹ ኢአማኒያኑን አጠቁአቸው::" ከትግራይ ሹም ሣራዊ ተኽሉ የሚባል ሼክ ሚካኤልን አጥቅቶ እግሩን በጦር ወጋው:: ጦሩ እግሩን ቀዶት በሌላ ጐኑ ወጣ:: ሼኽ ሚካኤል ሁለት ቀናት ቆይቶ ተሰዋ:: የአላህ ምሕረት ይውረድለት:: ዓምዱዋ ሚካኤል ቢን ሮቤል የተባለ አባቱ ሽምብራ ኩሬ ላይ በተደረገው ውጊያ የተገደለበት ከሓዲም አሚር አቡበክር ቀጪንን አጠቃ:: ሁለቱም ጦር ተወራውረው ከሓዲው የአሚሩን ረህመህ የተባለ ፈረስ ከአንገቱ

ላይ ወጋው፡፡ ጦሩ አካሉን ቀዶ በሌላ ጐኑ ዘለቀ፡፡ ሁለተኛ ጦሩን በመወርወር የአሚሩን ቀኝ እጅ ወጋ፡፡ አሚር አቡበክርም አበጋዝ ዓምዱዋን ደረቱ ላይ ወጋው፡፡ ጦሩ በጀርባው ዘልቆ እያብለጨለጨ ወጣ፣ ሽንፈትም አከናነበው፡፡ አበጋዙ መወጋቱን እንዳወቀ ከአሚሩ ጋር ትግል ገጠመ፡፡ በመታገል ላይ እያሉ የአበጋዙ የአጉት ልጅ የአጐቱን ልጅ በመርዳት አሚር አቡበክርን ከጀርባው ላይ ወጋው፡፡ ዐብደናስርም አሚር አቡበክርን የወጋውን ከሓዲ ወግቶ ገደለው፡፡ ከፈረሱም ወደቀ፡፡ አላህ ነፍሱን በፍጥነት ወደ ገሃነም ወሰዳት፡፡ ዓምዱዋም በአሚሩ ውግ ሳቢያ ለሕልፈት ተዳረገ፡፡ አላህ አይዘንለት፡፡ ኢአማንያኑ የሁለቱን ጓዶቻቸውን መሞት ሲያዩ እግሬ አውጭኝ ሸሸት ጀመሩ፡፡ ሙስሊሞችም እያሳደዱ ይገድሏቸውና ይማርኳቸው ጀመር፡፡ ሁለት የትግራይ አበጋዞችንም ማረኩ፡፡ አንደኛው ሼይኽ ሚካኤልን የገደለ ሹም ሠራዊ ተኽላይ ሲሆን የማረከውም አውራዒ አቦኝ ነበር፡፡ ሌላኛው ደግሞ ሹም ሸጀረህ ሲሆን፣ የሸርኹቱ ሰው የገራድ ሲዲቅ አገልጋይ ነበር የማረከው፡፡ ከትግራይ አበጋዞች የተገደሉት ስምንት ናቸው፡፡ ከሙስሊሞች ግን ከአንድ ሰው ውጭ የተገደለ አልነበረም፡፡ ሙስሊሞች 20 ፈረሶችን ማረኩ፡፡ ቀሪዎቹ የከሓድያን ወታደሮች ወደ ንጉሱ ሸሹ፡፡ የአበጋዞቹ አለቃ ኢዮኤልም ተሸንፎ ከሠራዊቱ ጋር ሸሽቶ አመለጠና ከንጉሱ ዘንድ ገባ፡፡ ሙስሊሞች በሩን አልፈው አበጋዞችን መግደላቸውን ነገረው፡፡ ንጉሱ ይህን ሲሰማ እጅግ ተረበሸ፡፡ "ዓምዱዋ ሚካኤል የሮኤል ልጅም ተገደለን?!" ሲልም ተናገረ፡፡ ዓምዱ ሚካኤል ከክርስቲያኖች ዘንድ የተከበረ ሰው ነበር፡፡ በርሱም ምትክ ልጁን ሾመ፡፡ ልጁ ጀግና ነበር፡፡ የአባቱ ባሮች አንድ መቶ አምሳ ፈረሰኞች የትቢያ ሰዎች





ነበሩ፡፡ ከጌታቸው ፊት ተሰልፈው በብርቱ ይዋጉም ነበር፡፡ እርሱም ልክ እንደአባቱ ሆነ፡፡

ከዚህ በኋላ ንጉሡ የነበረበትን ቦታ በመልቀቅ ዳሞትን ትቶ ወደ ወጅ አቀና፡፡ አውራዒ ዑስማን እሥልምናውን የከዳ እንደሆነ የንጉሱን መሸሽ ሲሰማ የነበረበትን "ጉራጌ" የተባለ በር ትቶ ንጉሱን ተከትሎ ሸሽቶ በንጉሡም ደረሰበት፡፡

ኢማሙ በር ላይ የተውት ወዚር ዓድሊ በበኩሉ ሌቱን በመንገድ ካሳለፈ በኋላ ከኢማሙ ጋር ከ"ዶኾንዶውር" በላይ ተገናኙ፡፡ በአንድ ላይ ሆነውም ንጉሱን ማሳደድን ያዙ፡፡ ጊዜው የክረምት ወቅት ነበር፡፡ ሐበሾች በክረምት ለአራት ወራት ያህል ከቤታቸው መቀመጥን ይመርጣሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ልምድ አላቸው፡፡ ምክንያቱ ከሰማይ ሌት ከቀን ዶፍ ዝናብ ያለ ማቋረጥ ይዘንብባቸዋልና ነው፡፡ ሙስሊሞች ግን በዝናብና በብርዱ ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ ከዝናቡ ብዛት የተነሳ ምድር ወደ ጭቃነት ተለውጣለች፡፡ ሙስሊሞች እጅግ ተዳከሙ፡፡ መድፍ የተሸከሙ ግመሎችም እስኪወድቁ ድረስ አንዱ ከሌላው ይላተማሉ፡፡ የነበሩዋቸውን ሰባት መድፍችና ከኢአማንያኑ የማረኳቸውንም ስድስት መድፎች መንገዱ እጅግ አስቸጋሪና ጭቃማ በመሆኑም ሁሉንም ጣሉት፡፡ ድንኳኖቻቸውንም መንገድ ላይ ትተው ለመሄድ ተገደዱ፡፡

ንጉሱ ቀድሟቸው ሸሽቷል፡፡ "ወይሐየሐር" ከተባለች ብርዳማ ከተማ እስኪገባ ድረስ አሳደዱት፡፡ ኢአማንያኑ ከዚህች ከተማ ሲገቡ በብርድና በዝናቡ ብርታት የተነሳ ሦስት መቶ ሰዎች ሞቱባቸው፡፡ አላህ ሙስሊሞችን ከመሰል ጥፋት አተረፋቸው፡፡ ኢማሙና ሙስሊሞች ኢአማንያኑ በብርዱ ሳቢያ መርገፋቸውን ሲመለከቱ ጉዟቸውን ገታ በማድረግ ሰፈሩ፡፡ የሐበሻው

ንጉስ ወናግ ሰገድ ግን ሌሊቱንም አላረፈም:: ገስግሶ በመጓዝ "ገበርጌ" ምድር ደረሰ:: ከመንገድ ላይም ወጅ ውስጥ ወሰን ሰገድ ነበር:: ከወጅ ተነስቶ ጌታውን (ንጉሱን) መንገድ ላይ ተቀበለው:: ንጉሱም ሙስሊሞች ዳሞት ውስጥ የፈፀሙትን አወጋቸው:: ወሰን ሰገድም ንጉሡ ፊት ለአበጋዞቹ እንዲህ አላቸው:- "ይህ ውርደት እንዴት በናንተ ላይ ሊደርስ ቻለ? የዳሞት እጅግ አስቸጋሪ መሬት፣ ተከላካይ ጋራዎችና ጠባብ መንገድ ያላትና በሮችንና መንገዶችን ከተቆጣጠራችሁ በኋላ በሙስሊሞች እንዴት ልትሸነፉና ዳሞትን ልትለቁ ቻላችሁ? ሞት ትፈራላችሁን? አባቶቻችሁና አያቶቻችሁ ለእምነታቸው ሲሉ ሞተዋል:: እንዲህ ዓይነቱን ውርደት አላዩም:: እኔ በበኩሌ ለእምነቴ እየተፋለምኩ እሞታለሁ:: ከሞትኩም በኋላ ያሻችሁን አድርጉ፤ በማለት ተናገረ:: አበጋዞቹም እንዲህ አሉት:- አምላክ ይጠብቅህ:: አንተ ከሞትክ እምነታችንም ይሞታል:: እሞታለሁ አትበለን:: አለቃችን ነህና አሉት:: አሁን ሙስሊሞችን የት ነበር ትታችኋቸው የመጣችሁት? ሲልም ጠየቃቸው:: "እዚህ ቦታ ልንልህ አንችልም:: ግን እየተከሉን ነው፤ አሉት:: ይህን ባሉበት ወቅት፤ የወጅ አበጋዝ አስላም ደህር የታለ? የንጉሥ እስክንድር አማች የንጉሥ ወናግ ሠገድ ቢን ናዖድ የአጎት (የአባት ወንድ) ልጅን ያገባውስ ኩም ዲሐር የት ነው? ሲል ጠየቀ:: የወጁ አበጋዝ ሲመጣ ወናግ ሰገድ እንዲህ አለው:- አሁን ንጉሡ አገርህ ደርሶአል፤ የት እንደምታገባው አንተው ታውቃለህ:: የምንቀመጥበት ተከላካይና ጠባብ የሆን ሥፍራን አንተ አስታውቀን:: ሙስሊሞች ሲመጡ ከናንተው ጋር ሆኜ እንዋጋቸዋለን አለው:: ታዛዥ ነኝ:: አለና እናንተ አሁን ያላችሁት "ገብረጌይ" ነው:: ገበርጌይ ውስጥ ናችሁ:: ወጅ ምድር ውስጥ ወደሚገኘው "ወይዝ ጅብየህ" ገቢያ ውረዱና ከዚያው ተቀመጡ::





ሙስሊሞች ሲመጡ ማንም ሊደርስበት ወደማይችል ቦታ እወስዳችኋለሁ አለው:: መልካም ነው ካሉ በኋላ ገበርጌን ለቀው ወደ ወይዝበህ ገቢያ በመሄድ ከዚያው ሰፈሩ::

## የኢማሙ ሠራዊት ወረብ ውስጥ መስፈሩ

ሙስሊሞች ብርዳማ ከሆነው አካባቢ ለሁለት ቀናት ያህል ከተቀመጡ በኋላ ወደ ወረብ ምድር አመሩ:: ወጅ ዳርቻ ከ"ገበርጌይ" አቅራቢያም ደርሰው ሰፈሩ:: በእነሱና በክርስቲያኖቹ ሠራዊት መሀል የነበረው ርቀት ከነጭነትና ድንኳኖች በዝግታ አካሄድ የሁለት ቀን ጉዞ በሚወስድ ሥፍራ ነበር የሠፈሩት:: ከዚያም የንጉሡን ቦታና ያለበትን የሚያጠያይቅ ቃፊር ኢማሙ በዐብዱናስር መሪነት ሁለት መቶ ፈረሰኞች አስከተለውለት እንዲህ ሲሉት ላኩት:- ንጉሱ ወደሚገኝበት "ገበርጌ" ሂድና የሚገኝበትን ቦታ አጣርተህ ተመለስ፤ በማለት መረጃ ሰብስቦ እንዲመጣ ወደ ገብርጌ ላኩት:: የኢአማኒያን ቃኞችን አያቸው፤ እነሱም አዩት:: እንደደረሰም ቃኙው የንጉሡ ጦር አሱንና ሠራዊቱን እንደተመለከቱ በፈረሶቻቸው ላይ ሆነው በቅሎዎቻቸውን ትተው በመፈርጠጥ ንጉሣቸው ዘንድ ቀርበው ሙስሊሞች እየተከታተሏቸው እንደሆነ ነገሯቸው:: ዐብዲናስር ኢማሙና ሠራዊቶቻቸው መስሎአቸው ነው::

ንጉሡም የጦር አበጋዛቸው የሆነውን አስላምደሐርን አስጠርተው "ሙስሊሞቹ ወደኛ እየቀረቡ ነው፣ ምን ይደረግ ትላለህ?" ሲሉ ጠየቁት:: የጦር አበጋዙም ዋግ ወደተባለ አካባቢ ወደሚገኝ ሠዋራ ቦታ ይዟቸው ሔደ:: በዚያም ከተሙ:: ዐብዱናስር በበኩሉ ወደ ኢማሙ ተመልሶ የሠራውን ሥራ ነገራቸው፡ "ንጉሡ ወደ ዋግ ሸሽተዋል፡ በማለትም አስረዳቸው:: ሙስሊሞችም

ከ"ወረብ" ምድር በ"ተራራ ቁጥ" ሠፍረው የእርስ በርስ ምክክር ያዙ። በዚህም ወቅት በቅርቡ ሙስሊም የሆነውና ሔይብ የሚባለው ሰው ተነስቶ፡ "ንጉሡ ወደ ዋግ መሸሻቸው ለኛ በእጅጉ መልካም ነገር ነው፡ ከዚያ አካባቢ ወደ ምድረ "ጉራጌ" ቢሸሹ መውጫ ቀዳዳ አያገኙም፡ ምክንያቱም ፀበኞቹ ናቸውና፡ ወደ ዳዋሮም እንሸሽ ቢሉ ልንከተላቸው ሆነ፣ ማምለጫ መንገድ አይኖራቸውም፡ ስለዚህ ከዚህ ተነስተን በሁለት ቀን እንደርስባቸዋለን አለ። ሙስሊሞቹ ግን የተለየ ሐሣብ ነበራቸው። ንጉሡ አሁን ያሉበትን ሥፍራ ካልለቀቁ በቀር እንከተላቸው ዘንድ አይገባም አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ "ወደ ንጉሡም ሆነ ወደ ዳዋሮ አንሄድም። ዳዋሮ ከደረስን ወታደሮቻችን ይበታተኑብናል። ሁሉም ወደየአገሩና ወደየቤቱ ያመራል። አብዛኞቹ ወደ አገራቸው የመመለስ ፍላጐት አላቸው አሉ። ሌሎችም ወደ ምድረ ሸዋ መሔዱ ይበጃል፣ የንጉሡ ግምጃ ቤትና ገንዘባቸው የሚገኘው በሸዋ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጡ። ኢማሙም የብዙኃኑ አመለካከት ከኋለኛው ሐሣብ ጋር መሆኑን ተገንዝበው ወደ ሔይብ ዞር ብለው፣ አንተ ዝም በል፣ የነዚህኞቹን ምክር ተቀብለናል። አለህ ቢሻ ንጉሡም በእጃችን፤ ነው አሉ። እንዲህ ሆነና ሙስሊሞቹ በ"ዊዝ" በኩል ወደ ምድረ ሸዋ ተመሙ።

## የአዋሽ ወንዝ መመንጫ ሆነችው አንደቀብጢን

ኢማሙ በዐብዲ ናስር መሪነት አንድ የጦር ቡድን ወደ አዋሽ ምንጭ ማመንጫ ወደሆነችው አንደቀብጢን ላኩ። አንደቀብጢን ከ"ሸዋ" ምድር ናት። በዚህች መንደር የጥንታውያን ነገሥታት ቤተክርስቲያን ትገኛለች። በዚች ቤተ ክርስትያን ውስጥ በርካታ ገንዘብና ወርቅ የያዘ ግምጃ ቤት ይገኛል። ኢማሙም ቤተክርስትያኒቱን





እንዲያቃጥሉ፣ ገንዘቡን በምርኮ እንዲወስዱ ወንዶቹን እንዲገደሉ አዘዙ። ዐብዱናስር ትዕዛዙን ተቀብሎ ፈፀመ።

ሌላ ወታደራዊ ቡድንም በአሚር ሑሴን ዕዝ ሥር አደራጅተው "ደርዳብኒ" ወደተባለ የሸዋ አካባቢ እንዲዘምት አዘዙ። የንጉሥ ወናግስገድ ቤተክርስትያን በዚህ አካባቢ ትገኛለች። በአማረ መልክ የተገነባችና ግርማ ሞገስ የተላበሰችም ነበረች። ንጉሡ ለልጃቸው ፊቅጡር የሰጡዋትና በልጃቸው ስም የሰየሙዋት ናት።

በብርና በወርቅ በተሠሩ በርካታ ቁሳቁሶችና በውድ የሐር ዓይነቶች የተመላች ናት። ዐብዱናስር እንደታዘዘው ከቤተክርስትያኒቱ ደርሶ አሰሳ ቢያደርግም አንዳችም ነገር አላገኘም። ሐበሾች ቀደም ሲል ንብረቱን ወደ "ጋፋት" አሸሽተውት ነበር፣ ቤተክርስትያኒቱን አቃጠላት።

አሚር ሑሴንም የጦር ቡድኑን ይዞ ሄድ ዐብዱናስርም መንገድ ከሚያሳየው ጋር በመሆን አሚር ሑሴንን ተከተለ። የመንገድ መሪው እንዲህ አለው፡- እኔ አሚር ሑሴንን የምንቀድምበት መንገድ አውቃለሁ። ዐብዱናስር ይኼንን ሲሰማ፡- በል ምራን አለው፤ የመንገድ መሪውም ወደ ሌላ መንገድ ቀጠለ። እንዲህም ሆነና ዐብዱናስር አሚር ሑሴንን አንድ ቀን ቀድሞት ደረሰ። ቤተክርስትያኒቱ በውስጧ የያዘችውን ሐብት ሁሉ በመሰብሰብ አቃጠላት። አሚር ሑሴን ከሥፍራው ሲደርስ ቤተክርስትያኒቱ በዐብዱናስር ተቃጥላ በማግኘቱ በእጅጉ ተከፋ።

"በኢማሙ የተሰጠኝን ቀጠና እንደምን ትደፍራለህ?" በማለትም ለዐብዱናስር ቅሬታውን አሰማ። ዐብዱናስርምይህች እኮ የኢአማንያን መንደር ናት፡ "እያንዳንዳችን የቻልነውንና የተመቻቸልንን ኢጋጣሚ መሻማት አለብን፡ በማለት አፅናንትአት ጥቂት ገንዘብም ለአሚር ሑሴን ሰጠው። እንዲህ ሆነና ሁሉም በወዳጅነት ስሜት ወደ ኢማሙ ጦር ሰፈር አመሩ። የዐብዱናስር ጭፍራ ከሰበሰበው ትሩፋት እያንዳንዱ የድርሻውን ወስዶ

ቀረውን ማለትም የብር ቁሳቁሶችንና የአእዋፍና የአራዊት ስዕሎችን ያካተተ በንጹህ ብር የተሠሩ ስዕሎችን ለኢማሙ አስረከቡ:: በርካታ ጨርቃ ጨርቅና በዓረብም፣ ዘንድ ሆነ ዓረብ ባልሆነም ታይተው የማይታወቁ እጅግ ያማሩ፡ ዋጋቸው አንድ መቶ ወቄት የሚገመት ሁለት መጋረጃዎችም ለኢማሙ ተሰጡ::

ኢማሙ በወቅቱ "አባረት" ላይ ነበሩ:: የ"አዋሽ" ወንዝ መመንጪያው ከሆነው ሥፍራ አናት ላይ ነበር:: የ"ወረብና" የ"ሸዋ" ሰዎች ለኢማሙ አሥራት ለመክፈል ተስማሙ:: እንዲህም በማድረግ ለአገራቸው መቃናትን አተረፉ:: ከዚህ በኋላ ኢማም አሕመድ ወደ "በርራራ" ተመሙ:: እግረ መንገዳቸውንም የወርቅ፣ የብርና የሐር ምርኮዎችን ያሰባስቡ ነበር:: አሥር ቀናት በዚህ ሁኔታ ጉዟቸውን ቀጥለው "በራራ" አቅራቢያ ሲደርሱ የ"በራራ" ሰዎች ተቀበሏቸው:: የዚህች መንደር ነዋሪዎች ለሐበሻው ንጉሥ ልብስ ሠፊዎች ናቸው:: ለጉሡ ፈረሶች እንደጋሻ ያለ መከላከያ የሚሆን መሣሪያም ይሠሩለታል:: በየሄደበት የሚሄዱም ናቸው:: ንጉሡ ወደ "ዋግ" በሸሸበት ጊዜ ወደ "በርራራ" ተመልሰው ሙሥሊሞችን በልግሥና ተቀብለው አስተናግዳቸዋል::

## ኢማሙና ሠራዊታቸው በርራራ ላይ ሠፍረው ሳሉ የደረሰባቸው ዝናብና አውሎ ንፋስ

ተራኪው የአሳህ ምሕረት ይዳስሰውና እንዲህ ይላል:- ከባድ አውሎ ንፋስና ዝናብ ሌሊት አየሁ:: በነበርንበት አድረንባት በነበረ ሌሊት ሰማዩን ጨለማ ወርሶታል ከዋክብት ጠፍተዋል፡ ከውሃ መያገር ስልቻ አፍ እንደሚደቀደቅ ውሃ ንፋሱና ዝናቡም ይወርድብናል:: ድንኳኖችን እየነቀለ ያበራቸው ጀመር:: ድንኳኖች ሁሉ ተንቃቅለው ወደቁ:: ኢማምና ገረዳቸው ሃጀራ ከሁለት





ጭፍሮቻቸው ጋር ሆነው ድንኳናቸውን ደግፈው በመያዝ ታህሊልና ተክቢራ በከፍተኛ ድምጽ ያሰሙ ነበር:: በዚያች ቅዕበት በዚያችው ቦታ ላይ የመውደሚያቸው ሰዓት የተቃረበ መሰላቸው:: ብዙም ሳይቆይ ጨለማው ተገፈፈ:: ዝናብና አውሎ ንፋሱ ቆመ:: ሙስሊሞቹም ወደ ኢማሙ ዘንድ በመምጣት ተሰባሰቡ:: "ምን ዓይነት ሌሊት ነው?" ሲሉ ተጠያየቁ:: ከመከከላቸው አንዳንዶቹ ይህ የኖህ ማዕበል ነው አሉ:: ሙስሊሞቹ ""በራራ" ስድስት ቀናት ቆዩ፣ የአካባቢውም ሰዎች ኢማሙ ፊት ቀርበው በአቅራቢያችሁ አንድ እጅግ ትልቅ ቤተ ክርስትያን አለች ሲሏቸው፣ ኢማሙም በትክክል የት አካባቢ ነች? ሲሉ ጠየቁ:: ሰዎቹም በ"ጀርራራ" አካባቢ ነች እዚያም "አውሮማ" የሚባል ትልቅ ወንዝ ይገኛል::

## ደብረሊባኖስ በአውሮማ ወንዝ ዳርቻ ላይ በመጀመሪያ የተገነባች የሐበሻ ቤተክርስቲያን

አውሮማ የሚባል ትልቅ ወንዝ በሚፈስበት ዳርቻ ላይ ደብረሊባኖስ የተሰኘች ቤተክርስትያን ትገኛለች:: በክርስትያኖች ዘንድ በእጅጉ የከበረ ስም አላት:: ክርስትያኖች ሁሉ በየአጋጣሚው ወደሷ ይጐርፋሉ:: መጋረጃ፣ የወርቅና የብር ቁሳቁስ፣ ሻማና ሌላም የከበረ ስጦታ ሁሉ በስለት ያቀርቡላታል:: በሐበሻ ከተገነቡ አብያተ ክርስትያናት ሁሉ በቀዳሚነቷም ትታወቃለች:: የአካባቢው ሰዎች በማናቸውም ረገድ የሚመስሏት ሌሎች አብያተ ክርስትያናት ቢኖሩ አክሱምና ላሊበላ ብቻ ናቸው በማለት ተናገሩ:: ኢማሙም ከምንገኝበት ሥፍራ ምን ያህል ትርቃለች በማለት ጠየቁ:: የስድስት ቀን ጉዞ ቢሆን ነው በማለት መለሱ ሰዎቹ::

ኢማም አሕመድ አሳህ በምሕረቱ ይዳብሳቸውና አቡበከር ቀጪንን አስጠርተው ሦስት መቶ ፈረሰኞችን

መደቡለት። ከመካከላቸውም አሚር ሙጃሂድ፣ አብስማ ኑር፣ ደል ሰገድ የመሳሰሉት ጀግኖች ይገኙባቸው ነበር። አካባቢውን የሚያውቅ ቃፊር ይዘው በዝናብ ወቅት ወደዚያው ተመሙ። አሚር አቡበከርና ሠራዊቱ ከዘመቻው ከመመለሳቸው በፊት የ"በርራራ" ሰዎች ኢማሙ ፊት ቀርበው "ባድቄ" ይገኝ የነበረው የንጉሡ ሃብት በአሁኑ ጊዜ የት እንደሚገኝ እናውቃለን። መርተን እናሳያችሁ በማለት ተናገሩ። ኢማሙም ወዚር ዓድሊን አስጠርተው ሠራዊቱን ይዞ ወደ "ባድቄ" እንዲዘምት አዘዙ። ሰዎቹ እንዳሉትም ዓድሊ ብዙ ምርኮ ሰበሰበ።

በ"ፈጥጋር"ና በ"መሲን" ለስድስት ቀናት በአደረገው አሰሳ በርካታ ወርቅ፣ ብርና የተለያየ ሕብረ ቀለም ያለው ሐር ማርኮ ወደ ኢማሙ "በርራራ" ሆነው ሳሉ ተመለሰ። ኢማሙም ለቅርብና በዙርያቸው ለሚዋጉ ጥበበኛ ጀግኖች ምርኮውን አከፋፈሉ።

እነዚህ ሰዎች ምንግዜም ከኢማሙ ጐን ሳይጠፉ እንደሌላው ሠራዊት በየአገሩ ሄደው ማጥቃት የማይችሉ ከኢማሙ የማይለዩ ከእርሳቸው ጋር ሆነው የሚዋጉ ክብ ዘበኞች ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው። ለዚህም ነው ይህን ትሩፋት ያከፋፈሉቸው። ዓድሊም ስለ ንጉሡ ያገኘውን መረጃ ለኢማሙ አስረዳቸው። "ንጉሡ ያሉት በምድረ "ዋግ" ነው። እርሱም የሚገኘው በመካከላችን በሁለት ቀን ጉዞ ርቀት ነው። ይሁን እንጂ አዋሽ ወንዝ በሁኑ ወቅት በመሙላቱ ምናልባት መሰናክል ሊፈጥርብን ይችል ይሆናል አለ።

የሐበሸው ንጉሥ ኢማሙ "በርራራ" መግባታቸውን ሲሰሙ:- እነዚህ ሙስሊሞች በርራራ ገብተዋል፤ አገሮችን አጠፉ፣ በአሁኑ ወቅት ወደ አገራቸው ይመለሳሉ። ግን እኔ ወደእሱ ሄጄ "አዋሽ"ን ተሻግሬ ቦታ ይዤ እዋጋቸዋለሁ። በማለት አብረዋቸው የነበሩት አርባ የሚያህሉ ፈረንጆችን እንዲህ አሉዋቸው።





# ከሐበሻው ንጉሥ ጋር ከነበሩት ፈረንጆች ንጉሡን የጠየቁት

ንጉሡ ለፈረንጅ ባለሟሎቻቸው አዋሽን የሚያሻግራቸው ጀልባዎች ይሠሩላቸው ዘንድ ጠየቁ። ፈረንጆቹም ጥያቀውን ተቀብለው በርካታ ጀልባዎችን ሠርተው አስረከቧቸው። ለወገኖቻቸውም በአገር ቤት አጠራር ለኺ ተብለው የሚጠሩ የታንኳ ዓይነቶች እንዲሠሩ አዘዙ። እነሱም አምስት መቶ ያህል ታንኳዎችን ሠራተው አቀረቡ። የንጉሱ ባለሟል ወሰን ሰገድ ንጉሡ ፊት ቀርቦ መሬት ከሳመ በኋላ፣ የአዘዙንን ሠርተናል። እኔ ባርያዎ ወደ እነዙ (ሙስሊሞቹ) እሄድና የ"አማጀህ" በርን ይጄ ከመጡብኝም እዋጋቸዋለሁ። በዚያ ውጊያ ላይ ብወድቅ ያሻዎትን ማድረግ ይችላሉ፤ እርስዎን የመሠለ በዚህ ወቅት ወደዚያ መሄድ የለበትም። ይህ የነገሥታት ባህልም አይደለም። ለዚህ ተልእኮ እኔ እበቃለሁ ሲል፤ ንጉሡም ለመልካም አመለካከቱ አመሰገኑት። የንጉሱ አበጋዞችም በአነጋገሩ ደስ ተሰኝተው አመሰገኑትና እንዲህም አሉት:- አንተ አባታችን ነህ፣ ገመናችንን በጥልቀት ታውቃለህ። አባ መላም ነህ በማለት አወደሱት። እንዲህ ሆነና ንጉሡ የዳዋሮ፣ የጐጃም፣ የፈጥጋር፣ የአፋት ሰዎችን ያከተተ ጦር ሰብቀው ከእስልምና የተመለሰውን ከሀዲ አውረዒ ዑስማንን በአዛዥነት መድበው ሌሎችንም የጦር አበጋዞች ጨምረው ንጉሡ ሸኙአቸው። አዋሽ ወንዝ ዳርቻ ሲደርሱ በጀልባዎቻቸው ላይ ታቅፈው አዋሽን ተሻግረው ፈጥጋር ደረሱ። ቁርቁራ መግቢያ ላይም ሠፈሩ።

ዓድሊ ከባድቄ ተነስቶ "በርራራ" እንደደረሰ ለኢማሙ ስለንጉሡና ከወሰን ሠገድ ጋር ስለአደረገውም ድርጊት፣ ወሰን ሰገድ አዋሽን ተሻግሮ ቁርቁራህ ላይ መስፈሩን ነገራቸው። ልዘምትባቸው አስቤ ነበር። ግን ያለፈቃድዎ መንቀሳቀሱን ፈራሁ አላቸው።

## ኢማም ከባለሚሌቻቸው ጋር ተማክረው ከዚያም የጋራድ አሕሙሻን አስተሳሰብ መቀበላቸው

በዚያም ጊዜ ሀድሊ በአደረገው ድርጊት ኢማሙ ሙስሊሞችን አማከሩ:: ሙስሊሞቹ ሁሉም በአንድ ቃል እንዲህ አሉ:- አሁን ያለንበት ወቅት ክረምት ነው፣ የዝናብ ጊዜም ነው፣ በዚህ ወቅት ከተጓዝን ባለፈው ጊዜ እንደደከምን አሁንም እንደክማለን:: የዝናቡ ወቅት እኪያልፍ እዚህ ቆይተን ከዚያ ወደዚያው አቅንተን እንዋጋለን:: በማለት አስተያየታቸውን ሰጡ:: ኢማሙ ንግግራቸውን በጥሞና ካዳመጡ በኋላ፤ ይሁን! መልካም ብላችኋል፣ ወደ ሥፍራችሁ ተመለሱ፤ ብለዋቸው ከኢማሙ ዘንድ ተበተኑ:: ኢማሙ ብቻቸውን ሆነው ጋራድ አሕሙሻን አስጠሩት:: ይህ ሰው ቅን ልቦናና የምክር ባለቤትም ነበር:: እንደመጣም ኢማሙ እንዲህ አሉት:- ሙስሊሞቹ ያሉትን ሰምተህ የለም? ሲሉት ከእነሱው ጋር ነበርኩ፣ የተናገሩትንም ሰማሁ፤ የዝናቡ ወቅት እስኪያልፍ እዚሁ መቆየት እንደሚሹ መናገራቸውን ሰምቻለሁ" አላቸው:: የአንተስ ሐሳብ ምንድ ነው?" ሲሉ ጠየቁት:: የዝናቡ ወቅት እንዲያልፍ ይፈልጋሉ:: ካለፈም በኋላ ወደውጊያው ይመሩን፣ አሁን እንዋጋለን ብለዎታል:: እርስዎም ተነቃንቀው "ፈጥጋር" ምድር ከገቡና ጦርነት ከገጠማቸው ይዋጋሉ:: ጦርነት ከሌለ ግን ወደ አገራቸው ወደ ሰዓደዲን አምባ እንዲሔዱ ይፈቀድላቸው ዘንድ መጠየቃቸው አይቀርም:: እርስዎ ፈቀዱም አልፈቀዱ እያንዳንዱ በራሱ ፈቃድ አገሩ ገብቶ ይቀራል፡ እርስዎም ብቻዎን ይቀራሉ ሲል፤ አስተያየቱን ሰጣቸው:: ኢማሙም አሁን ምን እናድርግ? ሲሉ ጠየቁት:: ገራድ አሕሙሹም ምን መደረግ እንዳለበት እኔ አውቃለሁ፡ አሚር አቡበከር ቀጪን እስኪመጣ ድረስ እዚህ እንቆይ፣ ከጦረኞቹ ጋር እዚህ እንደደረሰም





ሴቶቻችንና ንብረታችንን እንዲጠብቅ አደራ ብለን ወደ ሐበሾቹ መዝመት ነው:: አላህ ድሉን ካደለን የሐበሻውን ንጉሥ እንገድላለን:: ሕዝቡም ይሰልማል:: የአዋሽ ወንዝ ስለሚሞላ ለሙስሊሞቹ የሚሻገሩበት መንገድ አይኖራቸውም:: ግን በዝርፊያ ይዋከባሉ:: የክረምቱ ቀናት ካለፈና ሳንዋጋ ከቀረንም መሳፍንቱም ሆነ ተወወጀሌ ወደ አገሩ እንዳይሄድ መከልከል አንችልም:: ሁሉም መሔድ ይፈልጋልና አላቸው:: ኢማሙም በጥሞና ካዳመጡት በኋላ ያልከው ሁሉ መልካም ነው:: ይህን ሐሳብ በምስጢር በልብህ ያዘው ብለውት አቡበከር ቀጪን እስኪመጣ ድረስ ተቀምጠው ይጠባበቁ ነበር::

አሚር አቡበከር ወደ ጠቀስናት ቤተክርስቲያን ደርሶ በቅራቢያዋም ሠፈረ:: በቤተ ክርስትያኒቱ የነበሩ ባሕታውያን ሸሽተው ተራራ ላይ በውጣት ተደበቁ:: አንዳንዶቹም ካቃጠሉዋት ከቤተክርስትያኒቱ ጋር እንቃጠል በማለት ተመለሱ:: በውስጧም ገብተው ተቀምጠው መቃጠሉዋን ይጠባበቁ ጀመሩ:: አንዳንዶቹም ወደ አሚር አቡበከር መልዕክተኛ በመላክ ቤተ ክርስትያኒቱን ማቃጠል ምንም አይጠቅምህም፣ አታቃጥላት:: ያሻህን ያህል ወርቅ፣ ብርና ሐር እንሰጥሃለን አሉት:: አገሬውና በአካባቢዋ የሚኖሩትም ለመገበር ዝግጁ እንደሆኑ አስረዱት:: አሚር አቡበከርም ጓደኞቹን ሰብስቦ በዚሁ ጉዳይ ላይ ምክክር ያዘ:: አንዳንዶቹ ገንዘብ ወስደን ቤተክርስትያኒቱን ከማቃጠል መቆጠቡ ይሻላል ሲሉ፡ ሌሎች ደግሞ ገንዘብ አንፈልግም፣ በእነሱ ዘንድ ገናናነት ያላት ስለሆነች ቤተክርስቲያኒቷን ማቃጠል አለብን አሉ::

አሚር አቡበከር ገንዘብ መውሰድን የመረጡት ንግግርን በመቀበል፣ ለመልዕክተኛው እንዲህ አሉት:- በገንዘብ እንታረቃችኋለን:: ወደ ሰዎችህ ተመልሰህ የነገርንህን ንገራቸው፣ እናም ወደ እኛ ይምጡ:: ወደ እኛ በሚመጡበትም ጊዜ የምንፈልገውን ገልፀንላቸው ይሰጡናል፣ ቤተክርስቲያኒቷንም እንተዋታለን፣

አናቃጥላትም፣ አሉት፡፡ መልዕክተኛውም ወደ ሰዎቹ ተመልሶ አሚር አቡበክር የተናገሩትን ነገራቸው፡፡ ተደስተውም የምሥራች አሉ፡፡ ወደ አሚር አቡክርም መጡ፣ እንታረቃችኋለን አሚሩ ሲሏቸውም፣ የምሥራች ብለው፣ እያንዳንዱ ቀሚስ በአንድ መቶ ሃምሳ ወቄት ንፁሕ ወርቅና በአንድ መቶ ሃምሳ ወቄት ንፁሕ ብር ያጌጡ ሁለት ቀሚሶች ለአሚር አቡበከር አበረከቱ፡፡ እርቅን ለለገስከን ለአንተው ይህ የምሥራቻችን ነው አሉት፡፡ ለምንታረቅበት የምትጥልብንን ግብር፣ ወርቅና ብር ንገረን አሉ፡፡

## የአውረዒ በለው ዓብደላና የደብረ ሊባኖስ ገዳም ቃጠሎ ክስተት

እነሱ ንግግር በመለዋወጥ ላይ ሳሉ፤ ከሙስሊሞቹ አንድ ሰው አውራዒ አቡበከር የሚባል ተደብቆ ወደ ቤተክርስቲያኒቷ በመሄድ ከተሳኩስ እሳት አንድ ችቦ በመምዘዝ ቤተክርስቲያኒቷን አቀጣጠላት፡፡ ባሕታውያኑና አሚር አቡበከር ንግግር በመለዋወጥ ላይ ሳሉ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቷ ዞር ብለው ሲያዩ፣ ተቀጣጥላ የእሳቱ ቃጠሎ ሠማይ ደርሶአል፡፡ ባህታውያኑና አሚሩ እሳቱን ሲያዩ እርቁ በዚሁ ፈረሰ፡፡ ባህታውያኑ ተነሥተው ከጥቂቶቹ በስተቀር በኩራዝ ዙሪያ እንደምትወዛወዝ ብራብሮ በእሳቱ ዙሪያ ይጯጯሁ ጀመሩ፡፡

አውራዒ አቡበከር፣ ቤተ ክርስቲያኒቷን ያቃጠለው ከተደራዳሪዎቹ ከበለው ጐሣ ነው፡፡ በለው የመጀመሪያው ጐሣቸው የተመሠረተበት ነው፡፡ ከአገራቸው ከ"ትግራይ" በዘመነ ሣዕድአዲን ወደ ምድረ ሣዕድአዲን ከፈለሰው አያታቸው የተመሠረተ ጐሣ ነው፡፡ ስሙም በለው ዓብደላ ነው፣ ሣዕዳዲንም ሴት ልጁን ድሮለታል፡፡ ልጅቷም ወልዳለታለች፡፡ ወንድ ልጅ በተወለደለት ቁጥር "አውረዒ" ሴት ልጅ ስትወለድለትም "በዕቲያ" በሚል ይሰይማቸዋል፡፡ አሚር አቡበከር ቀጪን ቤተክርስትያኒቱን ያቃጠለውን





አውረዒ አቡበከርን አስጠርቶ በድርድር፣ ላይ እያለን ለምን አቃጠልካት? በማለት ጠየቀው፡፡ አቃጥያታለሁ በቃ! በኔ ላይ የፈለግኸውን እርምጃ መውሰድ ትችላለህ፡ የኢማሙ መመሪያ ቤተክርስትያኒቱን እንድናቃጥል እንጂ በገንዘብ እንድንደራደር አይደለም" በማለት በእርጋታ መለሰለት፡፡ አሚሩም ተወው፡፡ እንዲህ ሆነና ከአካባቢው ያገኙትን ምርኮ አሰባስበው ወደ ኢማሙ አቀኑ፡፡ ከአሥራ ሁለት ቀናት ጉዞ በኋላ በዓረፋ ዕለትኢማሙ ከሚገኙበት ምድረ "በርራራ" ደረሱ፡፡

አሚር አቡበከር ስለቤተክርስቲያኒቷ መቃጠል ለኢማሙ አስረዳቸው፡፡ ኢማሙም "ቀድሞውኑ የተላካችሁት ለዚህ ነው፡፡ በእነሱም ዘንድ ከሁሉም የሚበልጥ ይህ ነው፣ "ካሉ በኋላ" ወደ እየሠፈራቸው እንዲመለሱ አዘዙዋቸው፡፡ አቡበከር ከአንተ ጋር ጉዳይ አለኝና ሲነጋ እፈልግሃለሁና እንድትመጣ" ብለው በተለይ አዘዙት፡፡ ኢማም አሕመድ ቀጥለውም ለወረራ ከ"በርራራ" ውጪ ወደ ጠረፍ ክልሎች ተልኮ የነበረውን አሚር ሑሴንንም አስጠሩ፡፡

አሚር ሑሴን አስተዋይና አባመላ ነበር፡፡ እንደመጣም ኢማም አሕመድ ከገራድ አሕሙሻ የሰሙትን አስተያየት ልቅም አድርገው ነገሩት፡፡ አሚር ሑሴን የኢማሙን ንግግር በጥሞና ካዳመጠ በኋላ መልካም አስተያዮት ነው፤ ነገውኑ ወሰን ሰገድ ላይ ቢዘምቱ ያለ ጥርጥር ወሰን ሰገድን ገድለው አላህ ቢሻ ሐበሻን ያቀናሉ፡ ሁለትና ሦስት ቀን እዚህ የሚቆዩ ከሆነ ግን አሕሙሻ ያለው ነገር ይደርሳል፡ አላቸው፡፡ የወታደሮቹ ፍላጐት ወደአገራቸው መመለስ ነው፡፡ ኢማሙም የአሚር ሑሴንን ንግግር ካዳመጡ በኋላ ለመዝመት ቆረጡ፡፡ ሲነጋ ወታደሮችህን ይዘህ ወደኔ እንድትመጣ፣ ሌሎችም አሚሮች ወታደሮቻቸውንና ትጥቃቸውን ይዘው እንዲመጡ ንገር ብለው አሚር ሑሴንን አስናበቱት፡፡

በነገው ቀን ፈረሶቻችሁን ጫኑ፣ ፈረሰኞቻችሁና እግረኞቻችሁም በአጠቃላይ ወደእኔ እንድትመጡ፣ የሰማሁት ወሬም አለ፣ አሉት፡፡

## ኢማሙ ወደ ሐበሻ ለመንቃነቅና ከዚያም ወደ ወሰን ሠገድ ለማምራት ከጦር አዛዦቻቸው ጋር በድጋሜ መማከራቸው

ኢማም አሕመድ ባለሟሎቻቸውንና ፈረሶቻቸውን አነቃቅተው፣ ጦሮቻቸውን ሰብቀው ሲነጋ እንዲመጡ እምቢልታ አስነፉ፣ ነጋሪት አስጐሸሙ፡፡ ይህን የሰማ ሁሉ ኢማሙ ዘንድ ተጠናቅቆ ከተተ፡፡ ኢማሙም፣ እኔ ወሰን ሰገድ ላይ መዝመት እፈልጋለሁ ምን አስተያየት አላችሁ? ሲሉ ጠየቁ፡፡ ዘመቻው የክረምቱ ወራት ካለፈ በኋላ እንዲሆን ተማክረን አልነበረምን? አሁን ይህ መመካከር ምን ይሆን? ሲሉ ኢማሙን ጠየቋቸው፡፡ ኢማሙም ንግግራችሁን ተውት፣ ወሰን ሰገድን ማግኘት የምንችለው በክረምት ወራት ብቻ ነው፤ ይህን ጉዳይ የማውቀው እኔ እንጂ እናንተ አይደላችሁም አሏቸው፡፡ ሰዎቹም ሀብታችንን እና ጭነታችንን እንደምን አድርገን እንዘምታለን? ይዘነው እንዘምታለን ወይስ እዚሁ እንተወዋለን? አሉ፡፡ ኢማሙም ይህ ሊሆን አይችልም ካሉ በኋላ ወደ አሚር አቡበክር ዞር ብለው ይህ ያመጣኸው ቀሚስ ላንተ ይሁን፤ አንተ እዚሁ ሆነህ ሴቶችንና ንብረታችንን አስጠብቅ በማለት አዘዙት፡፡ አራት መቶ ያህል ጠንካራ የጦር ሰው የሆኑ ፈረሰኞችን መደቡለት፡፡ ከዚህ ሥፍራ ነቅነቅ እንዳትል፣ ንጉሡ ወደ አንተ ከመጣም ተዋጋው፣ በእርሱም ላይ አላህ ድሉን ያጐናጽፍሃል ብለው አስጠነቀቁት፡፡ እርሱም ትዕዛዝ ሰምቻለሁ፡፡ አከብራለሁም በማለት "በርራራ" ውስጥ ቆየ፡፡ ኢማሙም አልፋቲሐ የተሰኘውን የቁርአን ምዕራፍ ካነበቡ በኋላ አሚሮችንና ወታደሮቻቸውን አስከትለው ቃፊራቸውን አስቀድመው





ተመሙ፡፡ ሰማዩ በአናታቸው ላይ ዝናቡን ይረጫል፡፡ መንገዱ ጨቅይቷል፡፡ አንዳንዱ ከፈረሱ ላይ ወድቆ ጭቃው ላይ ይነጠፋል፡፡ ሌላው ከበቅሎው ይወድቃል፡፡ ሌሎችም እንዲሁ በቅሎዎቻቸው ላይ እየወጡ ሌላ ጊዜም እየወረዱ መንገዱን ይገፋሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ተጉዘው ክርስቲያናቱ ከሰፈሩበት አቅራቢያ ደርሰው ከተሙ፡፡ ወሰን ሰገድ የሙስሊሞች በአካባቢው የመስፈር ዜና ከአገሬው ደረሰው፡፡ ይህ የሐሰት ወሬ ነው፣ ሙስሊሞች በዓረፋ ቀን ሆነ በክረምት ወራት አይንቀሳቀሱም ሲባል ሰምቻለሁ አላቸው፡፡

ወሰን ሰገድ ከህዲውን አውረዒ ዑስማንን አስጠርቶ "ሙስሊሞች በበዓላቶቻቸው ቀናት ይንቃነቃሉን? በዝናብ ጊዜያትስ ይዋጋሉን? መቆናጠጣቸውን (ፈረስ-በቅሎ) ስለሚያደክም፣ ሲል ጠየቀው፡፡ ቀደም ሲል አገራችን በነበርኩበት ጊዜ፣ ይህን በመሰለ ዝናብ በሚሆንበት ጊዜና በዓላታቸው እስኪወጣ አይዘምቱም ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ምን በማድረግ ላይ እንዳሉ አላውቅም አለው፡፡ ከዚያም ወሰን ሰገድ፣ ከ"ደዋሮ" ሰዎች ከመሪዎቻቸው ሁለት ፈረሰኞች አበጋዞችን አንዳቸው ሚካኤልን ሁለተኛው ሮቤልን አስጠርቶ፣ ኢማሙና ሠራዊቶቹ በእኛ አቅራቢያ መኖራቸውን፤ ባካባቢው ሙስሊሞቹ መታየታቸውን የአገሩ ሰዎች ተናግረዋልና ፈረሶቻችሁን ጭናችሁ በአካባቢ ቅኝት በማድረግ ስለሁኔታው መረጃ ይዛችሁ እንድትመጡ" በማለት ላካቸው፡፡ እንደተባሉትም ሽምጥ እየጋለቡ ሙስሊሞች ሰፍረውበታል ወደተባለው አካባቢ ነጐዱ፡፡ ኢማሙም ለወታደሮቻቸው እንዲህ አሉዋቸው፡- ኮረብታው ላይ አትሥፈሩ፣ ኢአማንያኑ ስለእኛ የሚያውቁት ምንም ወሬ የላቸውም፡፡ አላህ ቢሻልን እኛ እናሜርባቸዋል፡፡ ኮረብታውም ሥር ሠፈሩ፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ አንድ ደለን የተባለ ሙስሊም መኰንን አራት ወታደሮችን አስከትሎ ኮረብታው ላይ በእንጨት ሰበራ በተሰማራበት ወቅት ወሰን ሰገድ ከላካቸው ሰላዮች ጋር ፊት ለፊት ተገናኙ፡፡ አንደኛው

ሚካኤል የሚባለው፡ አንተ ሰው! ስለሙስሊሞች ምን ወሬ አለህ" ሲል ጠየቀው። ደለንም የትኞቹን ሙስሊሞች ነው የምትፈልገው? ሲል ጠየቀው። ሚካኤልም ጠረኞቹን ሲል መለሰለት። ደለንም እዚሁ ከቅርብህ አሉልህ አለው። ከቅርብህ አሉ ሲለው ደለን ሙስሊም መሆኑን ተረዳ። ፈረሰኛው ከቆመበት ሥፍራ ወደታች ቢመለከት ኖሮ የሙስሊሞችን ሠፈር በጉልህ ማየት በቻለ ነበር። እንዲህ ሆንና ወደ ኋላ ዞሮ ሽምጥ ሊጋልብ ሲል ደለን ፈረሰኛው ላይ ተወርውሮ በርኖሱን በመጐተት ከፈረሱ ላይ አፈናጥሮ ጣለው። ጐራዴውን መዝዞ እፊቱ ላይ አሳረፈበት። ከዚያም ፈረሱ ላይ ሆኖ ህፍረት አከናንቦ ከፊት ለፊት እየነዳ ኢማሙ ፊት አቆመው። ጓደኛው አምልጦ ወደ ሰፈሩ ተመለሰ። ኢማሙና ሙስሊሞቹ በዚህ ድል እጅግ በጣም ተደሰቱ። በዚህም አላበቁ፣ ኢማሙ ለደለን የምርኮኛውን ፈረስና ቀሚስ ሸለሙት።

ኢማም አሕመድ ምርኮኛው ስለ ወሰን ሰገድ የሚያውቀውን እንዲነግራቸው ሲጠይቁት እዚህ ቅርባችሁ ነው ያለው፤ እኔና ጓደኛዬ ወደዚህ አመጣጣችን ስለ እናንተ መረጃ ለማግኘት ነበር። እኔ በዚህ አገልጋይ እጅ ገባሁ። "ጓደኛዬ ግን አመለጠ አላቸው። ኢማሙ የሚሹትን መረጃ ካገኙ በኋላ እንዲገደል ወሰኑበት። በሽሽት ሕይወቱን ያተረፈው ፈረሰኛ ሰፈሩ እንደደረሰ ሙስሊሞች በአካባቢው መኖራቸውና ጓደኛው መገደሉን ለወሰን ሰገድ አረዳው። በዚህ ወቅት በሐበሾች አምባ ሽብርና ፍርሐት ነገሠ። ሌሊቱን ነቅነቅ ሳይሉ በዚያው አሳለፉ።

## ወሰን ሰገድ ከወታደሮቹ ጋር መመካከሩ

ሲነጋም ሙስሊሞቹ ወደ ክርስትያናቱ ለመድረስ ገሰገሱ። ወሰን ሰገድም ወታደሮቹን ሰብስቦ ምክክር ያዘ። ሙስሊሞቹ በዙሪያችሁ ነው ያደሩት። አሁን ደግሞ እንደምን አደራችሁ ሲሏችሁ ነው። ለውጊያ ተዘጋጁ





አላቸው። ሁላቸውም በአንድ ላይ፣ በእንዲህ ያለ ወቅት ለውጊያ አትዘዙን፣ አሉት። ካልተዋጋችሁ ምን ልትሠሩ ነው? ሲላቸው፣ አንተ የሃይማኖታችን መሪያችን ነህ፣ አንተ ከወደምክ ሃይማኖታችንም ወደመ ማለት ነው፣ የክርስትና ሃይማኖት እሱም ታዲያ ምን እናድርግ? አላቸው። ወደ "ቡሣት" ተራራ እንሂዳለን፣ እዚያ ድረስ የሚመጣብንን እንዋጋዋለን፣ አንተም ከፊትአችን ሆነህ ትሂዳለህ፣ እኛም ኋላህ ሆነን እንዋጋለን አሉት። እኛ እስከ መጨረሻችን ብንገደልም ክርስቲያኖች ምናችውም አይደለም። አንተ የሃይማኖታችን ጀግና ከተገደልክ አገራችን ጠፋች። ብለው ተማፀኑት። እንዲህ ሆንና ወሰን ሰገድ በወገኖቹ ሐሣብ ተስማምቶ ወደ ተራራው ቀጠለ። ከሃዲውን አርወዒ ዑስማን አንተ ከኋላ ሁን ብሎት የሠራዊቱን ግማሽ ከፊል መድቦለት አሱም ግማሽ ሠራዊቱን እየመራ ቀጠለ።

ሙስሊሞቹ ከሱብሒ ሰላት በኋላ (ማለት ንጋት ላይ) ወደ ክርስትያኖቹ ጉዞ ሲያደርጉ፣ ኢማሙ ከሠራዊታቸው ጋር ወደ ጣቢያቸው የደረሱት ወደ ቀትር ወቅት አቅራቢያ ነበር። ወሰን ሠገድ ቀተዳሚ ሠራዊቱን ይዞ የተጓዘው ኢማሙ ወደ ጣቢያው ከመድረሳቸው ቀደም ሲል ነበር። አውራዲ ዑስማን እንደሆነ ድንኳኖችን እያጓጓዘ ለመሄድ ሲዘጋጅ ባለበት ሁኔታ ላይ ኢማሙ ደረሱበት። ሙስሊሞቹም ከኢአማኒያኑ በስተጀርባቸው ደረሱባቸው፣ ሲያዩቸውም ያለውጊያ ተሸንፈል ጣቢያውን ከነድንኳኖቹ ለቀቁ። ሙስሊሞቹ እንዲህ አሉ፡- ይህ ከአበጋዝ ወሰን ሰገድ የተጠነሰሰ ተንኰል ነው። ጣቢያውን ለእኛ ለቋል፣ እኛ ወደ ጣቢያው እስክንገባና በምናገኘው ስንዋከብ በእኛ ላይ ብቅ ብሎ ለወጣብን ያዘጋጀልን መውደቂያ ነው። ሌሎቹም እንዲህ አሉ፡- ይኼ ተንኰን ሊሆን አይችልም። እሱ ግን የኋላውን ሠራዊት እዚህ አስቀርቶ ከእኛ ቀድሞ ሸሽቷል። ገራድ ሸምሁንም ለሙሥሊሞቹ እንዲህ አላቸው፡- ወሰን ሠገድን በጣቢያው

ውስጥ ካገኛችሁት ግደሉኝ! እሱ እንደሆነ ወደ "አዋሽ" አካባቢ ሸሽቶአል። ኢማሙም የእሱን ሃሳብ ተቀብለው የሌሎችን አስተሳሰብ ተውት። ፈረሶቻቸውንም ተቆናጥጠው ተከተሉት።

የሙስሊሞች ጦር በአራት ዕዝ ተከፋፈለ። አንዱ እዝ አውረዒ ዑስማንን እንዲከታተል ተደረገ። ይህ እዝ አውረዒ ዑስማን ጋር ለአንድ ሰዓት ያህል ትንቅንቅ ውስጥ ከገባ በኋላ አሸነፈው። ሌላው እዝ ወሰን ሰገድን ተከተለ። በኢማም አህመድ እዝ ሥር የተሰለፈው ጦር በሌላ አቅጣጫ እየተመመ ነበር።

## የኢማሙ እዝ በተደጋጋሚ ከተሸነፈ በኋላ በወሰን ሠገድ ላይ ድል ተቀዳጀ

ወሰን ሰገድ ሙስሊሞች እንደደረሱበት ሲያውቅ ከበቅሎው ላይ ወርዶ መንበር ትከሉልኝ ብሎ አዘዘ፣ የብረት መንበርም ተከሉለት። መንበሩ ላይ ተቀምጦ ወታደሮቹን ማነሳሳትና ማነቃቃትን ያዘ። ነጋሪት ያስጐሽማል። የደረሱበት ሙሥሊሞችም ቁጥራቸው አነስተኛ ሆኖ እንደ አንድ ሰው ሆነው ዘምተውበት ለአንድ ሰዓት ያህል በብርቱ ተዋጉ። ከሙስሊሞቹ ፈረሰኞችም ዓብደላ ትግራዊ የተባለው ጀግና ፈረሰኛ ተሰዋ። ገዳዩ የጐጃሙ ነጋሽ ልጅ ነበር። ይህ ጀግና መውደቁን የተመለከቱ ሙስሊሞች በራሳቸው ተሸንፈው በመሸሽ ላይ እያሉ ሌሎች ሙስሊሞች ፈረሰኞች አግኝተዋቸው፣ ወዴት ነው የምትሸሹት? ተመልሳችሁ ጠላቶቻችሁን ተዋጉ፣ እኛም ከጐናችሁ ነን በማለት መለሷቸው። ለአንድ ሰዓት ያህልም ተዋጉ። ከአንድም ሁለት ሦስቴም ድል ራቃቸው። እንደገና ለሽሽት ፊራ ተባ ሲሉ ከቆዩ በኋላ በድፍረታቸውና በጀግንነታቸው የታወቁ ሙስሊም ፈረሰኞች ደረሱላቸው።





እነሱም፡ ገራድ ሽምዑን፣ ዓሊ አልወርዳይ፣ የአምባው ተሠዋ አውረዒ ዑመር ዲን ቢን ሱልጣን መሐመድ፣ ገራድ ዓቢድና መሰሎቻቸው ነበሩ። ለመሆኑ ያሸነፏችሁ እነማን ናቸው? በማለት ጠየቋቸው። እነሱም በከፍተኛ ደረጃ ተደራጅተው በቁጥርም በዝተው የመጡት የወሰን ሰገድ ጭፍሮች ናቸው፡ ከመካከላችን ዓብደላ ትግራዊንም ገደሉብን፡ እንደዚሁ ለአራት ወይም ለአምስት ጊዜ አሸንፈውናል፡ በማለት መለሱ። ገራድ ሽምዑን፣ አውረዒ ዑመር እና ጓደኞቻቸውም አሁን ደርሰንላችኋል፡ እኛ እንደሌሎቹ አይደለንም፡ ግምባር ቀደም ሆነን እንዋጋለን፡ እናንተ ተከተሉን በማለት አነቃቅተው ወደ የትግል ጐራ ይዘዋቸው ሔዱ። ገራድ ሽምዑን ጓደኞቹን በግምባር ቀደምትነት እየመራ የክርስትያናቱን ሰልፍ ሰንጥቆ ፊልሚያውን ቀደሰ። በመጀመሪያ የወሰን ሰገድ ወንድም ከሆነው ግርማ ጋር ፊት ለፊት ገጠመ። ግርማ ጦሩን ወድሮ ፊት ለፊት ተጋፈጠው። ሽምዑን በኩሉ በሠይፍ ጦሩን ከእነ እጁ ቆረጠው፣ ግርማ ከፈረሱ ላይ ተፈናጥሮ ወደቀ። አውረዒ ዑመር ዲን ቢን ሱልጣን መሐመድ በበኩሉ ከወሰን ሰገድ አጠገብ የነበረውን የጦር አበጋዝ በሰይፉ ወግቶ መሬት ላይ አነጠፈው። ወዲያውኑም ሕይወቱ አለፈች። ዓሊ አልወሪዲም በአንድ አበጋዝ ላይ በሠነዘረው ምት ጭንቅላቱን ሰይፎ ከአካሉ ለየው። እንዲህ ሆንና የወሰን ሰገድ ሠራዊት ተፍረከረከ።

## የገራድ ዓቢድ ግጥሚያና ወሰን ሠገድን ወግቶት ከዚያም መገደሉ

ወሰን ሰገድ የሠራዊቱን መፍረክረክና የወታደሮቹን ሽሽት ሲመለከት ወዴት ነው የምትሸሹት? በማለት እየጮኸ ሳለ ገራድ ዓቢድ ቢን ራጅሕ ውጊያ ገጠመው። ዓቢድ ቢን ራጅሕ በሱልጣን መሐመድ ኢብን ሰዕዳዲን

ወሰን ሰገድ ዓቢድን ሲያይ ወደሱ በመጠጋት የፈረሱን አንገት ዓቢድ አፍንጫው ድረስ እያስጠጋ ያሾፍበትና ይሰድበው ጀመር:: ወሰን ሰገድ የያዘው ጦር ሲሆን ዓቢድ ሠይፍ ይዞ ነበር:: ዓቢድ ሰይፉን መዝዞ ይበልጥ ተጠጋው:: በሰይፉ የወሰን ሰገድን አንገት ለመቅላት ሲዘጋጅ ወሰን ሰገድ ቀድሞት ግራ እጁን በጦር ወጋው:: ብዙ መከላከያዎች ቢኖሩትም የወሰን ሰገድ በግራ እጁ ላይ የሠነዘረበት ጠማር ውግ በአንድ በኩል ገብቶ በሌላ በኩል ብቅ አለ:: ወሰን ሰገድ ጦሩን ለመንቀል ቢታገልም በሙስሊሙ እጅ ላይ ተሰብሮ ቀረ:: እንደገና ሰይፉን መዝዞ ዓቢድን ሊመታው ሲል ዓቢድ ቀድሞ ሰይፉን በመምዘዝ ወሰን ሰገድን ራሱ ላይ አሳረፈበት:: ወሰን ሰገድ ሰይፉን ለመምዘዝ ሲታገል ዓቢድ ለሁለተኛ ጊዜ ከአንገቱ በላይ ጥቂት ከፍ ብሎ በከረረ ምት አሳፈረበትና ከፈረሱ ላይ አሽቀንጥሮ ጣለው:: አትግደለኝ እኔ ወሰን ሰገድ ነኝ በማለት ጮኸ::

ዓቢድ ክርስትያኖቹ የመሪያቸውን መውደቅ እንዲያዩና እንዲሰሙ በማለት ጮክ ብሎ ወሰን ሰገድ ሞተ፣ ወሰን ሰገድ ወደቀ ሲል፤ ድምፁን አስተጋባ:: ሙስሊሞችም እየጮሁ ወሰን ሠገድ ሞተ ማለት ጀመሩ:: ወሰን ሰገድ በበኩሉ ተወግቶ መሬት ሳለ፣ "አለሁ" "አለሁ" "አለሁ" ጦርነቱም ይቀጥላል እያለ ነበር:: ክርስትያናቱ የመሪያቸውን መገደል ሲሰሙ በድንጋጤ ተሞሉ፣ ሽሽትም ገቡ:: ሙስሊሞችም እየተከታተሉ አጠቋቸው:: የሞተው ሞቶ የቀተሩትም ተማረኩ::

ቀደም ሲል እንደገለጽነው ኢማም አሕመድ በዝቋላ በኩል ሌላ መንገድ ገብተው ነበር:: በዚህም ወቅት ኢማሙ መንገድ ላይ ሳሉ፣ ከባለሟላቸው ዓድሊ ጋር ተገናኙ:: ዓድሊም የአዳል አንባጅ ባላባት የሆነውን ጃን ነህድን ማርኮ ስለነበር ኢማሙ ፊት ገተረው:: ኢማሙም ምርኮኛውን ከአንተ ዘንው አቆየው፣ ዓርማም ያዝና ሙስሊሞችን እንድታሰባስብ በማለት አዘዙት:: እኛ ክርስትያኖችን እናሳድዳለን ብለውም ከበቅሏቸው





ላይ ወርደው ፈረሳቸው ላይ ተፈናጠጡ:: ወዚር ዓድሊም እጃቸውን ይዞ ዓርማውን ይወስዱ፣ ከዚህ አይንቀሳቀሱ:: ከሀዲዎችን ሌሎች ይከታተሉ በማለት ለኢማሙ ያለውን ከበሬታና አዘኔታ ገለፀ:: ኢማሙ አሻፈረኝ በማለት ፈረሳቸውን ፈረሳቸውን ተፈናጥጠው አሚር ሑሴንን፣ ጋራድ አሕሙሻን፣ ዓሉሽ ቢን ቢሻራንና ከነሱም ጀርባ በርካታ ሠራዊት አስከትለው ተመሙ::

## ኢማም አሕመድና ሦስት ፈረሰኞቻቸው ከተሸናፊው የወሰን ሰገድ ጦር ላይ መንገድ መዝጋታቸው

ተሸናፊው የወሰን ሰገድ ጦር በሽሽት ላይ እያለ ቀድመው መንገድ በመዝጋት አድፍጠው አደጋ ለመጣል ኢማም አሕመድና ሦስት ጀግኖች ፈረሰኞቻቸው መንገድ ገቡ:: መንገድ ላይ የገጠማቸውን አንድ እረኛ የወሰን ሰገድን ጦር አይቶ እንደሆነ ጠየቁት:: እሱም ጧት ከወታደሮቹ ግምባር ቀደም ሆኖ አለፈ አላቸው:: በእርግጥ ግን ቀደም ሲል እንደገለጽነው ወሰን ሰገድ ከኋላ ባለው የሙስሊሞች ጦር አዛዥ በዓቢድ እንዳልሆን ሆኖ ተሸንፎ በሙስሊሞች እጅ ወድቋል::

ኢማም አሕመድ መሬቱን ቢቃኙ አንዳችም የጋማ ከብትም ኮቴ ምልክት አላዩም:: ይህ መንገዳቸው ነው፣ ግን የኮቴ ምልክት አይታይበትም አሉና፣ ክርስትያኖቹ ከጀርባችን ናቸው ብለው አሰቡ:: ኢማም አሕመድና ሦስቱ ፈረሰኞች ጓዶቻቸው አንድ ቦታ አድፍጠው አካባቢውን ከሩቁ መቃኘት ያዙ::

አሥር ክርስትያኖች በቅሎዎቻቸውን ተቆናጥጠው በመሄድ ላይ ሳሉ ኢማሙና ተከታዬቻቸው እነዚህ ቀዳሚዎቻቸው ይሆናሉ ብለው፣ ሲያጠቁዋቸው ሰዎቹ ከበቅሎዎቻቸው ወርደው ፈረጠጡ:: ኢማም አሕመድ፣ ወደ ምሽጋቸው ተመልሰው ከጓዶቻቸው ጋር አደፈጡ::

በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ሌሎች ክርስትያኖች ከሩቁ ወደነሱ አቅጣጫ ሲመጡ ተመለከቱ:: እየቀረቡ ሲመጡ የጦር አበጋዞችንና የሴቶቻቸውን ንብረቶችን፣ ሐርና የመሳሰሉትን አጭቀው የያዙ ሳጥኖች መሆኑን ተረዱ:: በያዙትም እንዳይዋከቡ (በቁሳቁሱ እንዳይማረኩ) አድፍጠው አሳለፏቸው:: የሚፈልጉት (ቁሳቁስ ሳይሆን) ጦረኞቻቸውንና ፈረሰኞቻቸውን ነው:: ከነሱ ቀጥሎ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሠራዊታቸው ተከተለ:: እነዚህ ሁሉም ተስፋ የቆረጠና የተሸነፈው የወሰን ሠገድ ሠራዊት እንደሆነም ተረዱ:: ሙስሊሞቹም ይህ ተሸናፊው የክርስትያን ጦር ስለሆነ እንውረረው በማለት ኢማሙን አማከሯቸው:: ኢማሙም ይህ አይሆንም! እኛ አራት ፈረሰኞች ነን:: እነሱ እንደምታዩዋቸው ብዙዎች ናቸው:: ከመካከላቸውም የታጠቁ ሰዎች አሉባቸው፤ እኛ ማድረግ ያለብን አሉ:- ሁሉንም ካሳለፍን በኋላ ከጀርባ ደርሰን ሰልፋቸውን መበተንና መውጋት ነው፤ ከኋላቸው ያሸነፋቸው ከፍተኛ ጦር የሚከተላቸው ይመስላቸውና፣ ከውጊያው በፊት ይፍረከረካሉ በማለት ለተከታዮቻቸው ነገሩዋቸው:: ጀግኖቹ ሦስቱ ፈረሰኞች የኢማሙን ሐሣብ በአድናቆትና በታላቅ ክብር ተቀበሉት::

ክረስቲያኖቹ አርባ ያህል ፈረሰኞች ነበሩ:: ፈረሶቻቸውም የብረት መከላከያ ልባስ ነበራቸው:: እነዚህም የሠራዊቱ ተቀዳሚያኑን የሚጠብቁ ናቸው:: ከነዚህም ኢአማኒያን በስተጀርባ የሚከተል የለም አሉ:: አራት ሙስሊም ፈረሰኞች ከአርባ ክርስትያኖች ጋር ትንቅንቅ ጀመሩ:: ብርቱ ፍልሚያም ተጀመረ:: ደራሲው እንደሚናገረው:- በወቅቱ ከኢማሙ እንደተደመጠው ኢማሙ ስለዚህ ያልተመጣጠነ ፍልሚያ ሲናገሩ፡ ክንዶቻችን እስኪዝሉ ድረስ ገደልናቸው ማለታቸው ተዘግቧል:: ከአራቱ ሙሥሊሞች በአንዳቸው እጅ የተመታው ላይ የቀሩት ሦስቱ ሙስሊሞች ፈረሰኞች እጅ ያርፍበታል:: ኢማም አሕመድ የክርስትያኖቹን ፈረሰኞች አምበል በጉራዴ ጭንቅላቱን ሲመቱት ገራድ





አሕሙሻ፡ አሚር ሁሴንና ዓሉሽ እንደ አንድ ሰው ሆነው ተከታታይ ጥቃት በመሠንዘር ከፈረሱ ላይ አሽቀንጥረው ጣሉት:: ጋራድ አሕሙሻ በአንዱ የጦር አበጋዝ ላይ ምቱን አክርሮ ቢሠነዝርም ሰውየው ጥሩር አጥልቆ ስለነበረ ንቅንቅ አላለም:: በዚህ ጊዜ ዓሉሽ ወደ አበጋዙ ጠጋ ብሎ ዓይኑን ወጋው፡ በመቀጠልም በጦር ወጋግቶት በድን ሆኖ ወደቀ:: ተኽለ ሐዋርያት ጉጃም የተባለ አበጋዝ በንጉሡና በወሰን ሰገድ ዘንድ እንደ ብረት ምሽግ የሚቆጠር የጎጃም ሰው ከአሚር ሑሴን ጋር ፍልሚያ ገጠመ:: አሚር ሑሴን ተኽለሐዋርያትን ከፈረሱ ኮርቻ ላይ ፈንግሎ ከመሬት ደባለቀው:: ፈረሱ ሸሸ:: አሚር ሑሴን ፈረሱን ተከታትሎ ለመመለስ ሔዶ እስኪመለስ ድረስ ተኽለ ሐዋርያት ሸሽቶ ጫካ ገባ:: ሌሎች ክርስትያኖች ተሸንፈው ፈረጠጡ:: ኢማም አሕመድ ወደ አሚር ሑሴን መጥተው እንዲህ አሉት:- አንተ ፈረሱን ስትከተል አበጋዙ ዛፎች መሀል ገብቷ፣ አሚር ሑሴን ወደ ዛፎቹ መሀል ሲመለከት አበጋዙን ቆሞ ያገኘዋል:: አሚር ሑሴን በሰይፍ የከረረ ምት ቢሰነዝርበትም ምቱ ዛፍ ላይ በማረፉ የጦር አበጋዙ አልተጐዳም:: ኢማም አሕመድም በበኩላቸው ቢመቱትም አሁንም ምቱ በዛፉ ላይ አረፈ:: በዚህን ጊዜ አሚር ሑሴን በእግሬ ጫካ ገብቼ ይህን ሰው ፊት ለፊት ብጋፈጠው ይሻላል በማለት ለኢማሙ አስተያየቱን አቀረበ:: ኢማሙም ታገስ አይሆንም! አሉት:: ይህ በእንዲህ እያለ ወዲያውኑ ሁለት ሙስሊሞች መጡ:: አንዱ አቡበከር ነበር:: ኢማሙም አቡበክርን ተጣሩና እዚህ ጫካ ውስጥ ገብተህ ይህን ሰው በጦር ውጋው በማለት አዘዙት:: እሱም እንደተባለው አበጋዙን ተጠግቶ በጦር ደረቱ ላይ ሁለት ጊዜ ወጋው:: ይሁን እንጂ ሰውየው ንቅንቅ አላለም:: እንድያውም ሙስሊሙን ሰው በጅራፍ እየገረፈ ወደ ኋላው እንዲመለስ አደረገው::

ኢማም አሕመድ ስብረዲን የሚባለውን በሰይፍ ተዋጊነቱ እጅግ የታወቀ ወታደራቸውን ይህን ሰው አንገቱን ቀልቶ እንዲጥለው አዘዙት:: እሱም ከበቅሎው ላይ ወርዶ የአበጋዙን እጅ ቆርጦት ጣለው:: ያለውንም ገፈፈው:: ከዚያም ከሜካ አውጥቶ አውላላ ሜዳ ላይ ጨረሰው::

## የሙስሊሞች ጦር ኢማሙ ዘንድ መድረስ

የሙስሊሞቹ ሠራዊት ኢማም አሕመድ አሉበት ሥፍራ ሲደርስ፣ ኢማሙ እንዲህ አሉዋቸው:- የኢአማኒያኑ ስንቅና ትጥቅ፣ ፈረሶቻቸው፣ በቅሎዎቻቸው፣ እና ሀብታቸው ያለው እዚሁ ቅርብ ነውና፣ አሁኑኑ ቀጥሉ ሲሉአቸው፣ መርሐባ አሉ:: ኢማሙና ስድሳ ያህል የሚሆኑ ፈረሰኞች ባለሚሎቻቸውም ወደፊት ተመሙ:: በትጋትና በፍጥነት ሽምጥ እየጋለቡም ደረሱባቸው:: ኢማም አሕመድና፣ ፈርሽሐም ዓሊ፣ ጋራድ ሽምሁን፣ ጋራድ አሕሙሻ፣ ፈርሽሐምዲን፣ እና ሌሎችም እነሱን የመሰሉ ኢአማኒያኑ ላይ ሠይፎቻቸውን ወድረው ገደሉአቸው:: ከአሥር ፈረስ በቀር ምንም አልተረፈም:: እነዚህ ፈረሶችና ጭነታቸው፣ ጠባቂዎቻቸው የነበሩት የኢአማኒያኑ አርባ ፈረሰኞች ከመድረሳቸው በፊት፣ ኢማም አሕመድና ሦስቱ ባለሚሎቻቸው አንድ ሰዋራ ሥፍራ ላይ አድፍጠው የኃይል መመጣጠን ባልነበረበት ሁኔታ ሆን ብለው ያሳለፏቸው ናቸው:: የተከተሉዋቸውም ለዚህ ነበር:: ከአለቁት ክርስትያኖች ላይ ከፍተኛ ምርኮ ሰብስበው ኢማሙ የት ቦታ እንዳሉም እየተጨነቁ ከወዚር ዓድሊ ጋር ወደሚገኘው ሠራዊታቸው ተመለሱ:: ኢማምም ከዒሻእ (የምሽት ሰላት) ወቅት በኋላ ተመለሱ:: በመመለሳቸውም አላህን አመሰገኑ:: ኢማሙም የነበሩበት ሁኔታን ገለፁላቸው:: ኢማሙ ዓቢድን እንዲህ አሉት:- ወሰን ሠገድን እኔ ሳላየው ለምን ገደልከው? ውሻን ማየት ለምን ፈለጉ? አላቸውና፣ዓቢድ ሲመልስ:- ተማርኮ





ሳለ ጌታዬ ዘንድ ሳድርስህ እፈልጋለሁ ሲለው፣ በዚያው ሥፍራ በነበረች ዛፍ ሥር ተጋድሞ አልነሣም ብሎ በማስቸገር እዚሁ ባለሁበት ቦታ ግደለኝ ብሎ ሲሰድበኝ እዚያው እንዲገደል አዘዝኩ::

ከዚያም ኢማም አሕመድ ምርኮኞችን አስጠርተው ከፊታቸው ገተሯቸው:: ከምርኮኞቹ መካከል በወዚር ዓድሊ የተማረከው የጦር አበጋዝ ጃን ነህድ፣ የጃን አሞራው ባላባት ሙስሊም የነበረውና በኋላም ክርስትያን ሆኖ በንጉሡ ጃን አሞራን የተሾመው ቃሚም፣ ይገኙበታል:: ጃን አሞራ ማለት በ"ትግራይ" እና በ"ዓንጉት" መካከል የሚገኝ ስፍራ ነው:: ቃሚም በብርቱ ተዋግቷል:: ክርስቲያኖቹ በተሸነፉ ቁጥር እሱ እየተመላለሰ ይከልላቸዋል:: በአደራረጉም ሙሥሊሞችን በእጅጉ አድክሞአቸዋል:: የማረከውም ሰው ከሱማሌ የመታን ጐሣ ነው:: አበጋዝ ሐና የ"ላሊበላ"ው ሰው የተማረከው በዚሁ ሰው ነበር:: ኢማሙ ፊት የቀረቡት በአጠቃላይ ሰላሳ ያህል የጦር አበጋዞች ነበሩ:: ኢማሙም እንዲገደሉ አዘዙ:: በተጨማሪም ገብረ እንድሪያስ የተባለና ከወሰን ሰገድ ጋር በተደረገው ፍልሚያ የተማረከውም ሰው ተገደለ:: በሐበሻ ምድር ከንጉሥ አድማስ ጀምሮ ዘመነ እስክንድርን ይዞ እስከ ናውድና ንጉሥ ወናግ ሰገድ ድረስ ከሹመት ሹመት እየተሸጋገርኩ አገሮችን እገዛ የነበርኩ ለዚህ በቃሁ እያለ ይፎክር ነበር:: በተገደለበት ዕለት የዘጠና ዓመት አዛውንት ነበር:: ወሰን ሰገድ ከተገደለ በኋላ ሐበሻን ማቅናት ተቻለ:: የክርስትያኖቹ ጦርም አንገቱን ደፋ:: አብዛኞቻቸውም ወደፊት በዘርዝር እንደምናየው ሙሥሊም ሆኑ::

ሙስሊሞቹ አርበኞች "አዋሽ ጠቡ" አካባቢ ለሦስት ቀናት ቆዩ፣ ከዚያም ወደ "ጃን ዘለቀ" አቅንተው በዚያው ሰፈሩ:: የወሰን ሰገድን መገደልና የክርስትያኖችን የሽንፈት ዜና የሚነግር ብስራት ነጋሪ ወደ "በራራ" አሚር አቡበከር ቀጪን ዘንድ ተላከ:: አሚር አቡበክር ዜናውን ሲሰማ ለብስራት ነጋሪው ልብስ ሸለመው::

## ኢማሙ አሕመድ በየአገሩ የጦር ቡድን መላካቸውና የየአገሬው ሰዎች ሙሥሊም ሆነው ተገኘነታቸውን ማስታወቃቸው

ኢማም አሕመድ ጃን ዘለቀ አምባ እንደደረሱ አገሬው ወደ "ሸገራ" ሸሽቶ ነበር:: ኢማሙ ነሥራ የተባለውንና በ"ዙሬ" ወጊያ ተማርኮ የነበረውን የሙርጋይን ሰው አስጠርተው፡ አንተ የ"ሸገራን" አገር ታውቃታለህን? ሲሉ ጠየቁት:: እሱም "አዎ! አውቃታለሁ፣ ልጆቼና ሃብቴም እዚያው ይገኛሉ:: እኔ ወደ አካባቢው በመሔድ አገሩን አቀናለሁ፡ እዚያ እንደደረሳችሁም ሕዝቡ በመላ ሙሥሊሞች ይሆናሉ፤ አላቸው:: ኢማሙም ፈርሸሐም ዲንን ጭምር ወታደሮች አሰለፉለት:: ወደ "ሻገራ" እና ዙሪያዋ ሄደው እዚያ ሲደርሱም ሕዝቡ ከቀዬው በነቂስ ወጥቶ ተቀበላቸው:: ኢማሙ በተጨማሪ ወዚር ዓድሊን ወደ "ዙቃላ" ና "ላሊበላ" አዘመቱ:: ወዚር ዓድሊ ሠራዊቱን እየመራ ወደ ግቡ ነጐደ፣ የወሰን ሰገድን ሞት የሰማው አሚር ሙጃሂድ ቀድሞት "ዝቋላ" በመድረስ ዘርፎና ብዙ ምርኮ ሰብስቦ ወደ "በርራራ" ተመልሰው ከአሚር አቡበከር አቡበከር ቀጨን ጋር በመገናኘት እዚያው ተቀምጦ ነበር:: እዚያው ዓድሊ አካባቢው ሲደርስ፤ አገሬው ከበአሚር ሙጃሊድ የተዘረፉ እለት ሠልመው የአገሬው ሰዎች ሙሥሊሞች ሆነው ዓድሊ አገኛቸው:: ወዚር ዓድሊ ከዚያም ወደ "አዋሽ ጠቡ" ሄደና የአገሩ ሰዎችም ሙስሊሞች ሆኑ::

ኢማም አሕመድ በበኩላቸው ከ"ጃን ዘለቀ" ተነስተው ወደ "አንጢጣ" ምድ ገቡ:: በዚህ ሥፍራ የንጉሥ እስክንድር በወርቅ የተሞላች ትልቅ ቤተ ክርስትያን ነበረች:: ሙስሊሞቹ በአቅራቢያዋ ሰፈሩ:: የ"ጃን ዘለቀ" አምባ ሰዎች ግን ሳይሰልሙ በየተራራው ፣ በየዱሩና በየሸለቆው ተብቀው ስለነበር ኢማሙ በኻሊድ





አልወርዳይ የሚመራ ፈረሰኛ ጦር አዘመቱባቸው:: ኻሊድ አልወርዳይ አገሩን በሚገባ ያውቅ ነበር:: እንደደረሰም፣ እኔ ኻሊድ አልወርዳይ ነኝ ታውቁኛላችሁ፣ አገራችሁንም መግቢያና መውጫዋን አውቃታለሁ፡ በመካከላችን ደም መፋሰስ ሳይፈጠር ስለሙ፡ በማለት አገሬውን በብርቱ አስጠነቀቀ::

የጃን ዘለቀ አምባ ሰዎችም ተሰባስበው "የኻሊድ አልወርዳይን ጥሪ አንቀበልም ብንል ለጌታው ለኢማሙ መልዕክት ያስተላልፋል:: ኢማሙም ከዚያም ከዚህም ሠራዊት ይሰዱብናል፡ አብዛኛው ሐበሻም በእሥልምና ገብቷል:: ሙሥሊሞቹም በአገሩ ውስጥ ተሠራጭተዋል:: እኛ ያልተቀበልናቸው መሆናችንን ከሰሙም አንዳችንም አንተርፍም:: ጌታችን ወሰን ሰገድም ተገድሏል:: ከመስለም በመለስ መላ የለንም፡ በማለት ተስማሙ:: ለኻሊድ አልወራዳይ በላኩት መልእክት:- በሀገራችን አማን የምናገኝ ከሆነ እንሰልማለን፤ በማለት አስረዱት:: "የቁት" ሰዎችን ጨምረን በሕብረት ኢማሙ ፊት ቀርበን እንሰልማለን፤ ጥያቄያችን አማን ማግኘት ነው፤ ሲሉም አስረዱ:: ከዚያም ኻልድ አልወራዲ አማን ሰጥቷአቸው ኢማሙ ወደሚገኙበት ቤተክርስቲያኒቱ ወደ አለችበት "አንጢጣ" አቀና:: ኻሊድ አልወራዲ ለኢማሙም እንዲህ አላቸው:- "የጃን ዘለቅ" ምድርን ትተው አንጢጣ ላይ የወጡት ለምንድነው? አገሬው አማን ይጠይቆዎታል:: እኔም የበኩሌን አማን ሰጥቻቸዋለሁ አላቸው:: የኔ ምኞት ወደ "በርራራ" መመለስና ፈረሰኞቻችንን በየሀገሩ ማስማራት ነበር፡ አሉት:: ኻሊድ በበኩሉ ሲመልስ፡ ወደ "በርራራ" የምታቀኑ ከሆነ የ"ጃን ዘለቀ"ና የ"ቁት" ሰዎች አይሰልሙም፡ ይልቅ ወደ "ጃን ዘለቅ" ተመልሰን እንስፈር:: አገሬውም ከጦር አበጋዞቹ ጋር ፊትዎ ቀርቦ ሊሰልም ተዘጋጅቷል፡ አላቸው:: ኢማሙም ምክሩን ተቀበሉት:: መሐመድ ሕሩቦኝንና ገራድ አሕመሻን አስጠርተው ከኻሊድ አልወርዳይ የሰሙትን ምክር አካፈሉዋቸው:: እነሱም፡ ይህ መልካም ምክር ነው በማለት

ተቀበሏቸው:: ኢማሙ ወደ አሚር አቡበከር ቀጨን መልዕክተኛ ልከው እኛ ወደ "ጃን ዘለቅ" መሔዳችን ስለሆነ ከበርራራ እስከ ባድቄ ድረስ ያለውን አገር አረጋጋ፡ መልእክታችን እስኪደርስህ ድረስ ወደ ፈጥጋር አትዝለቅ፣ አሉት:: ከዚያም አንጢጣ በምትገኘው ቤተ ክርስትያት ውስጥ የተደበቀውን ወርቅ ካስወጡ በኋላ አቃጥለዋት፡ ወደ "ጃንዘለቀ" ጉዟአቸውን አቀኑ:: ኢማሙ አሕመድ ወደ ኻሊድ ወርዳይና ገራድ ዑስማን ቢን ጀውሀር ዘንድ መልዕክተኛ ልከው ወደ ምድረ "ቁት" ሔዳችሁ ሕዝቡን ለእስልምና ጥሩት በማለት አዘዟቸው:: አነሱም በታዘዙት መሠረት በስፍራው እንደደረሱ የ"ጃን ዘለቅ"ና የ"ቁት" ሰዎች በነቂስ ወጥተው አሉበት ድረስ መጡ:: በሕብረት ሰልመውም ኢማሙ ወደሚገኙበት "ጃን ዘለቅ" በመሔድ ከኢማሙ ፊት እስልምናቸውን አፀደቁ:: ከሐበሻ የጦር አበጋዞች መካከል ከዋናዎቹ አበጋዝ ሐይዙ፣ አበጋዝ ደሎ፣ አበጋዝ ደብለይ የተባሉት ሦስቱ ሰዎች ይጠቀሳሉ:: እነዚህ ሰዎች እስልምናውን አሳምረው ከያዙ በኋላ በተካሔዱት አያሌ ፍልሚያዎች ውስጥ ተሳትፈው ጀብዱ ሠርተዋል::

## የኢማሙና የአበጋዝ አይብስ ላህጤ ወግ

ከሁለቱ አበጋዞች አንዳቸው አይብስ ሊህጤ ከእናቱ በኩል ከንጉሡ ጋር ዝምድና ያለው ለኢስላምና ለሙስሊሞች የከረረ ጥላቻ የነበረው ሰይጣን ነበር:: በክህደት የማያህለው ሰው ማምለጫ ያልነበረው ነው:: ማምለጫ በማጣቱ ብቻ ከሰለሙት ሦስቱ አበጋዞች ጋር ተቀላቅሎ ገባ:: ከ"ቁት" ሰዎችም ጋር አበጋዞቹ ኢማሙ ፊት ቀረቡ:: ኢማሙ ፊት የቀረቡት በአጠቃላይ አንድ መቶ ፈረሰኞችና አራት ሺ እግረኞች ነበሩ:: ኢማሙም ወደ እሥልምና ጥሪ አደረጉላቸው:: አይብስ ላህጤ ሲቀር ሁሉም እስልምናን ተቀበሉ:: በዚያው ቀን እንዲህ አለ:-





እኔ እሥላም አልሆንም፡ ለዚህም አልመጣሁም፣ አባቶቼና አያቶቼ የሞቱበት ኃይማኖቴን አልለቅም፡ በማለት በድፍረት ተናገረ:: ኢማሙም ከነዚህ ከሰለሙት አንተ ትሻለህን? ከእነሱም የበለጠ ጠንካራ አማኝ ነህን?" አሉት:: እሱም:- እነዚህ ሰዎች መሃይሞች ናቸው፣ ሃይማኖታቸውንም ሆነ ሃይማኖታችሁን የማያውቁ ናቸው:: እኔ በእሥልምና ከገባሁ ንጉሡና መንፈሳውያን (ባህታውያን) ያዋርዱኛል፡ አይባስ ለሕጤይ ሠለመ ይሉኛል፣ ለእኔም ይህ ትልቅ ውርደት ነው:: ከማርያም ሃይማኖት አልወጣም አለ:: ኢማሙም አታድርገው፣ አንተ ትልቅ ክርስቲያን ነህ፣ በእኛና በአንተም መካከል አማችነት አለን፣ አሉት፡

የኢማሙ እቁባት ሃጅራ የአይብስ የቅርብ ዘመድ አባቱ ወንድም ልጅ ናት:: ኢሥላም ውስጥ አጋር የምትሆን ነህ ኢማሙ ሲሉት፣ ግትር አለና ተቃወመ፣ እናም ለኢማሙ እንዲህ አላቸው:- እኔ አማችህ ነኝ፣ ለአንተ በሃይማኖቴ ሆኜም አጋር እሆንሃለሁ:: ከሙስሊሞችም ሆነ ከክርስቲያኖቹ በኩል በመካከላችሁ አለመግባባት ቢነሣ፣ ከአንተው ጋር ሆኜ እዋጋለሁ ለኢማሙ አላቸው:: ኢማሙም እንዲህ አሉት:- ከክርስትያኖች አንዳችም እርዳታ አልፈልግም፣ አንተም አትጠቅመንም፣ አትጐዳንምም፤ ስለዚህ ፈረስህንና ትጥቅህን አስረክበህ እየገበርክ በኃይማኖትህ ፀንተህ ኑር፤ በማለት ሸኙት::

በእሥላም የገቡት አበጋዞች ጓደኞቹ ለደህንነትህ ዋስትና የሰጡህ ኢማሙ ብቻ ናቸው:: ሌሎች ወታደሮች ግን ይህን ዋስትና አልሰጡህም:: እኛም ብንሆን እናጠቃህና እንገድልሃለን:: አለበለዚያ በእሥልምና ግባ፣ አንተ ከኛ በምን ትበልጣለህ?" አሉት:: በዚህ ጊዜ ፈራና በእሥልምና ገባ:: ከኢማሙ ጋርም ሦስት ወር ያህል ከተቀመጠ በኋላ ኢማሙ ወደ "ቤተ አምሐራ" ሲዘምቱ አምልጦ ክርስቲያን

ከንጉሡ ጋር ተቀላቀለ። ሌላው አቢጋዝም ከእሱ በኋላ በጥቂት ቀናት ሸሸ። ኢማሙ ለጃን ዘለቀ ሰዎች ገራድ ዑስማንን፣ ለቂት ሰዎች ደግሞ ኻሊድ አልወራዲንን ሾሙላቸው። ኻሊድ ከቂት ሰዎች ጋር በመሆን ወደ ቂት አመራ። ሲቶቻቸውንና ልጆቻቸውንም አሰለመ። እነርሱም እስልምናቸውን አሳምረው ያዙት። ኻሊድ ቂት ውስጥ የሚገኘውን የኢአማንያን የወርቅና ሌሎች ሀብታቸውንም፣ መገልገያዎቻቸውን በማውጣት ወደ ኢማሙ ላከው። ኢማሙ የአዋሽ ወንዝ ውኃው እስኪጎድል ድረስ "ፈጥጋር" በመቀመጥ ወንዙ ከጐደለ በኋላ ወደ ደዋሮ የማምራትና ነዋሪዎቿን የማስለም ሐሳብ ነበራቸው። ሰዎቻቸው ግን የ"አዋሽን" ወንዝ ከሁለት ወራት በኋላ እንጅ አይጐድልም አሏቸው። ወራት ሥራ ፈትተን ለምን እንቀመጣለን? ወደ "ሸገራ" ምድርና ወደ "ደብረ ብርሃን" መሄድ አለብን አሉ።

## ኢማሙ ወደ "ደብረ ብርሃን" ሠራዊት መላካቸው

ኢማሙ የ"አንጉት"ን ገዥ አሚር ዓሊን አንተ በ"ሡርማት" እና በ"ደርጃህ" መንገድ አድርገህ ወደ "ደብረ ብርሃን" ሂድ ሲሉ አዘዙት። አንድ መቶ ፈረሰኞችም አከሉለት። ከነዚሁም፦ በሻራህ፣ ሡልጣን ዓሊ፣ ዓሊ አልወራዲ፣ ገራድ ዓሊድ፣ ወሰን ሠገድን የገደሉ አውራዒ ዑመር ዲን፣ አውራዒ ቃጥ ዑመር፣ ገራድ ዑስማን፣ ከጃን ዘለቅ ሰዎች ጋር ሆነው ነበር የተላኩት። እናንተ በላይኛው መንገድ ሂዱ። እኔ በታችኛው መንገድ እሄድና በአላህ ፈቃድ "ደብረ ብርሃን" ላይ ቤተ ክርስቲያኒቷ አለችበት ቦታ እንገናኛለን፣ አሏቸው። የዚያኑ ዕለት ተጉዘው





ኢማሙም በ"ሹጀረህ" መንገድ አድርገው "ሹጀረህ" ሲደርሱም ገራድ ነስር ተቀበሉዋቸው። አገራችን፣ ልጆቻችንና ቤተሰቦቻችን ሁሉ በገናናው አላህ በረከትና በእርስዎም በረከት ኢሥላም ሆነዋል አሏቸው። በእሥልምና በገቡት አገርህም ላይ መሪ አድርሄገለሁ። ወደ አልሠለሙትም ሂድና ማርካቸው ብለውት እናም አወደሱት። ፈንጅ ሰበር የተባለውን ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር አክለው ሰጡት። በሌሊት ተጓዙና የተባሉትን ሰዎች አጠቁና ገደሏቸው። ሁለት አቢጋዞችንም ማረኩ። ተልዕኳቸውን ሲያጠናቅቁ ወደ ኢማሙ በመመለስ ሁለቱን ምርኮኛ አቢጋዞች ከፊታቸው አቀረቡላቸው። ኢማሙም አገር ምድሩ ሰልሞ እናንተ የማትሰልሙት ለምንድን ነው? ሲሉ ጠየቋቸው። ይህ ሁሉ ይደርሳል ብለን ስላላሰብን ነው፣ አሏቸው። ኢማሙም አንገታችሁ በሰይፍ እንዲቀላ ወስነናል አሉ። እነርሱም እሺ፣ ይሁን አሉ። ኢማሙ በአባባላቸው ተገረሙ። እንዲገደሉም አዘዙ።

## ይፋት በሸምሱ እጅ መቅናትዋ

የ"በሐር" ጦር ተቀዳሚ የሆነ ሸምሱዋ የተባለውን ኢማሙ እንዲህ አሉት፦ ወደ ይፋት ሂድና አቅናት። መሪዋ አድርጌም ሾሜሃለሁ። ሸምሱ ለተልዕኮው ተንቀሳቅሶ ይፋት ደረሰ። ፈረስ የሚያሳልፍ መንገድ የሌላት ጠባብ ናት። እግረኞች የሆኑት ነዋሪዎችዋን እስኪያሸንፏቸው ተዋግቶአቸው በቆራጥነት አቀናት። ነዋሪዋቹዋን ከአንድ ተራራ አጠገብ ከከበባቸው በኋላ ሰለሙ። በዚያ ስፍራ የቀድሞው ንጉስ የእስክንድር አንዲት ቤተክርስቲያን ትገኛለች። ውስጧ ብዙ ወርቅ ይገኝባታል። ንጉስ እስክንድር ብዙ የወርቅና የብር ቁሳቁሶችን በስለት

አስገብቶላታል:: ወረቀቱም ሽፋኑም ወርቅ የሆነ አንድ ትልቅ መጽሐፍም ይገኝባታል:: ወንጌላቸው የተጻፈበት ነው:: ይህን መጻሕፍ ለመሸከም ሁለት ጠንካራ ሰዎች ያስፈልጋሉ:: ሸምሱ ከቤተክርስቲያኗ ውስጥ ገባና አቃጠላት:: ከውስጧ ያሉ ንብረቶችንም በሙሉ ዘረፈ:: ሐምሳ ወቄት የሚመዝን የወርቅ ዘለበት ያለው አንድ የንጉስ እስክንድር በርኖስም አገኘ::

ኢማሙ ወደ ሸምሱ በማቅናት ይፋት ዳርቻ ላይ "አቦነህ" ከተባለ ሥፍራ ተገናኙ:: ሸምሱ ንብረቱን ሁሉ ለኢማሙ አስረከበ:: ኢማሙና ሙስሊሞቹ በዚህ የወርቅ መጽሐፍና በሥዕሎቹም እጅግ ተደነቁ::

## የደረጀህ ምድር በአሚር ዓሊ እጅ መቅናት

አሚር ዓሊ በበኩሉ የላይኛውን መንገድ ይዞ በመጓዝ "ደረጃህ" ምድር ገባ:: ተቆጣጠራትም:: በነዋሪዎቿም ላይ ግብር ጣለ:: ከዚያም ወደ "ደብረ ብርሃን" በማቅናት ከነሥራዊቱ እዚያው ደረሶ ኢማሙን ይጠባበቅ ጀመር::

ኢማሙ "አቦነህ" ላይ ተቀምጠው ገራድ አህሙሽህን ወደ ይፋት ላኩት:: እስክታቀናት ነዋሪዎችዋን ተዋጋቸው፣ እኔም ከኋላህ አለሁ" ሲሉም አዘዙት:: ገራድ መታንን አስከትሎ ወደ ተልዕኮው አመራ::

ኢማሙ ከአምስት ፈረሰኞች ጋር ብቻ ቀሩ:: ይፋት በአቅራቢያቸው ናት:: ሙሥሊሞቹ ለኢማሙ እንዲህ አሉዋቸው:- ወታደሮችዋን አዝምተው ጨረሱ:: ከአጠገብዎ ያሉት አምስት ፈረሰኞች ብቻ ናቸው:: ከእንግዲህ ማዝመቱ ይብቃዎት" በሁለተኛው ቀን ከገራድ አህሙሻህ ጋር ተቀላቀሉ:: ወደ ተለያየ አቅጣጫ ያዘመቷቸው የጦር ሹማምንቶች ሐምሳ ያህል ነበሩ::





## ከሓዲው አውራዒ ዑስማን ወደ እስልምና መመለሱን በማብሰር ለኢማሙ ምሥጢር ደብዳቤ ስለመጻፉ

ከሓዲው አውራዒ ዑስማን ወሰን ሰገድ በተገደለ ጊዜ ወደ አገሩ ወደ ይፋት ሄዶ ከዚያው ተቀመጠ:: የራሱን ወታደሮችና፣ የ"ጋፋት" እና የ"ወናግጂራ" ወታደሮችንም አሰባሰበ:: ኢማሙ "አቦነህ" ሲደርሱ፣ አውራዒ ዑስማን ለወታደሮቹ፣ ሙስሊሞችን እዋጋቸዋለሁ፣ ከሀገሬ እንዲገቡ አልፈቅድላቸውም አላቸው:: የቅርብ ባለሟሎቹን በምሥጢር እንዲህ የሚል መልዕክት አስይዞ ወደ ኢማሙ ላከ፣ "እኔ ጥንትም ቢሆን ሙስሊም የሙስሊም ልጅ ነኝ:: ኢአማንያን ማርከው ክርስቲያን ያደረጉኝ ቢሆንም ልቦናዬ አሁንም ድረስ በእስልምናዬ እምነቴ እንደረጋ ነው:: ከእንግዲህ እኔ የአላህ ተማማኝ፣ የመልክተኛውም ተማማኝ፣ የእረስዎም ተማማኝ ነኝ:: ንስሐዬን ይቀበሉኝ:: እስካሁን የፈፀምኳቸውን ድርጊቶችንም ይቅር ይበሉኝ:: ወደ አላህ በንስሐ ተመልሻለሁ:: በሥሬ ያሉ የንጉሱ ወታደሮችንም እርስዎ ዘንድ እንዲገቡና እንዲሰልሙ አግባባቸዋለሁ::"

የይፋት ሰዎች የሆኑ ሙስሊሞችን ይህን መልዕክት አስይዞ ወደ ኢማሙ ላካቸው:: "ይህን ምሥጢር ለአንድም ክርስቲያን እንዳትነግሩ" በማለትም አስጠነቀቃቸው:: ደብዳቤው ገራድ አህሙሻህ በሄደበት በዚያኑ ቀን ለኢማሙ ደረሰ:: ኢማሙ አንብበው የያዘውን መልዕክት እንዳወቁ ለገራድ አህሙሽህ "ተመለስ፣ መልዕክት አለኝ" በማለት ላኩበት:: ገራድ አህሙሽህ ወደ ኢማሙ ተመለሰ:: የአውራዒ ዑስማንን ዜና አጫወቱት:: "አቡነህ" ውስጥም ረጉ:: የአቡነህ ነዋሪዎች ሁሉም ከኢማሙ ዘንድ

በመቅረብ ሁላቸውም ሰለሙ:: አቢጋዛቸው አሰላሙዋም እንዲሁ ሰለመ:: ግን ኢማሙ ወደ "ቤተ አማራ" ካቀኑ በኋላ መሪያቸው ኢስላሙዋ ወደ ክህደት በመመለስ ከንጉሱ ጋር ተቀላቀለ:: ወታደሮቹ ግን በእስልምናቸው በመርጋት ከሸምሱ ጋር ሆነው ሐበሻ ሙሉ በሙሉ እስክትቀና በተደረጉ ዘመቻዎች ሁሉ ተሳተፉ::

## ኢማሙ ለአውራዒ ዑስማን መልዕክት በጉ ምላሽ መስጠቻውና ጠቢያ ምድር ላይ እንዲገናኙ ቀጠሮ መስጠቻው

ኢማሙ አውራዒ ዑስማን የላከውን ደብዳቤ ካነበቡ በኋላ እንዲህ በማለት መልስ ላኩለት:: "ንስሐ ለመግባት ከወሰንክ አላህ እነዚያ የካዱት (እኩይ ድርጊታቸውን) ቢያቆሙ (ከንስሐ) በፊት የፈፀሙትን (ጥፋት) ሁሉ እንደሚማርላቸው አላህ ተናግሮአል፣ (ሱረት አልአንፋል አያህ 38) ምንም የሚያስጋህና ያሚያሳስብህ ነገር የለም:: በእኛና በአንተ መካከል መገናኛ ቀጠሮአችን ጠቢያ ምድር ላይ ይሆናል:: እኔ አሁኑኑ ወደዚያው አቀናለሁ:: እዚያው እንገናኝ በማለት፣ እርጋታና በልብ እርካታም እንዲያገኝ መቄጠሪያቸውን ላኩለት:: የኢማሙ ደብዳቤና መቄጠሪያው በምስጢር ደረሰው:: ደብዳቤውን ከፍቶ በማንበብ መልዕክቱን ሲያውቀው:- ጨነቀው፣ እኔ አንድ ብቻዬን ነኝ:: ይህን ሁሉ ክርስቲያን ሠራዊት ምን ላደርገው ነው:: ብቻዬን ወደ ሙስሊሞች ብሄድ ብዙ ጥፋት ስላደረስኩባቸው እንዳይበቀሉኝ እሰጋለሁ:: ጦሩን ከእኔ ጋር ሠልሙና እንሂድ ብላቸው ደግሞ ሊገድሉኝ ወይም ሊያስሩኝ ይችላሉ::. የሚል ሐሳብ አስጨነቀው::





## አውራዒ ዑስማን የቅርብ ሰዎቹን ማማከሩ

ከዚህ ቀደም ሰልመው የኢማሙ አገልጋዮች የነበሩ ሁለት ሰዎች አብረውት አሉ:: አንደኛው ሽኩር ሌላኛው ደግሞ የዕቂም ይባላሉ:: ሽኩር አንድ የኢማሙን ባለሚል በሌሊት በመግደሉ ኢማሙ ይዘው በሰንሰለት አስረው በሞት ሊቀጡት ሲሉ የታሰረበትን ሰንሰለት በመበጠስ አምልጦ ወደ ሀገሩ ከንጉስ ጋር የተቀላቀለና ወደ ክርስትና የተመለሰ፣ ንጉሱም ይፋት ውስጥ አንዲት ቀዬ ሰጥተውት ይፋት መንገድ ላይ ከአውራዒ ዑስማን ጋር ያስቀመጡት ነው:: የዕቂም በበኩሉ ከሙስሊሞች አገር እዳ ነበረበት:: ሙስሊሞች እዳውን እንዲከፍላቸው ሲጠይቁት ምንም ገንዘብ ስላልነበረው ኢማሙ ሳያውቁ ወደ ሐበሻው ንጉስ በመሸሽ ወደ ክርስትና የገባና ንጉሱም ይፋት ውስጥ መሬት ሰጥተው ያስቀመጡት ነው:: አውራዒ ዑስማን እነዚህን ሁለቱን ሰዎች በማስጠራት ለብቻቸው አነጋገራቸው:: ምን ምክር አላችሁን? እኚህ ኢማም ወደእኛ ተቃርበዋል:: ነገ ከነገ ወዲያ ሀገራችንን ይቆጣጠሯታል:: ያጠፏታልም:: ስለዚህ ምን እናድርግ? ወታደሮቻችንን ይዘን ወደ ንጉሱ እንሸሽ ወይስ አገራችን ውስጥ ሆነን እንዋጋና እንሙትላት:: ሃሣባችሁን ስጡኝ፡ አላቸው:: እኛ አገልጋዮችህ ነን:: የማማከር አቅሙ የለንም:: የምታዘንን ግን እንፈጽማለን:: እንሸሽ ካልከን እንሸሻለን:: እንድንዋጋ ካዘዝከንም እንዋጋለን:: እንድንሰልምም ከጠየቅከን እንሰልማለን" አሉት:: "እንሰልማለን ካላችሁ ከመዋጋትና ከመሸሽ የተሻለው አማራጭ ነው:: ከኢማሙ ዘንድ እንገባና በክህደት ወቅት ለፈፀምነው ጥፋት ሁሉ ንስሐ እንገባለን:: ደብዳቤ ጽፌላቸዋለሁ:: አሁን

ያላችሁትንም ጉዳይ አውስቼላችዋለሁ:: ደብዳቤና ማኅተማቸውን (የፀሎት መቁጠሪያቸውን) ለእኔና ለሁላታችሁም ደህንነትን እንደሚጠብቅ ማረጋገጫ ልከውልኛል:: ካላቸው በኋላ፡ ይህንን ከፊት ያለው ሠራዊትስ ምን እናድርገው ትላላችሁ? ሁሉም ክርስቲያኖች ሆነውስ እንዴት ይከተሉናል? ሲል ጠየቃቸው:: ለደህንነታችን መተማመኛ ካገኘህልን የሠራዊቱን ጉዳይ ለኛ ተወው:: አገልጋይህን ዓናንየህን አሁኑኑ ፈልገው አሉት:: ዓናንየህ ከአውራዒ ዑስማን የበታች ሆኖ ወታደሮችን የሚመራ ሰው ሲሆን፣ ክርስቲያን ነው:: አውራዒ ዑስማንም ለዓናንየህ ይህንን ብናማክረው ይቀበለናል? ሲል ጠየቃቸው:: ሁለቱም "አዎ፣ ይከተልሃል:: እሳት ውስጥ እንኳ ብትገባ ተከትሎህ ይገባል አሉት:: እንግዲያውስ ፈልጋችሁ አምጡልኝ አላቸው:: ወደ ዓናንየህ በመሄድ ይዘውት ከአውራዒ ዑስማን ፊት አቀረቡት:: አውራዒ ዑስማን ለዓናንየህ አንተ ልጄ ነህ የወታደሮቼም አለቃ ነህ:: በኛ ላይ የደረሰውን ጉዳይ እያየህ ነው:: ምን እናድርግ? አለው:: ዓናንየህም እኔ ተከታይህ ነኝ፣ የትም ብትሄድ ከአንተ አልለይም:: አብሬህ እሄዳለሁ:: እንዋጋ ካልክ ታዛዥ ነኝ:: ወደ ንጉስ እንሸሽ ካልክም ይሁን:: አገልጋይህ በመሆኔ ያዘዝከኝን ሁሉ ከመፈፀም ወደኋላ አልልም ሲል መለሰ:: አውራዒ ዑስማንም በመሐላ እጄን ምታ አለው:: ከፈቃዱ እንደማይወጣ ማለለት:: ከዚህ በኋላ አውራዒ ዑስማን ለመሠለም እንዳሰበ ነገረው:: ዓናንየህም እኔም ከአሁን ቀደም መርጋይ ምድር የሾምከኝ ጊዜ ልሰልም አስቤ ነበር:: ለኢማሙ ከተንቀሳቃሾች ጋር ደብዳቤ ጽፌላቸዋለሁ:: እስካሁን ከዚህ የተቀመጥኩት ላንተ ስል ብቻ ነው አለው:: አውራዒ ዑስማን ይህን ቃሉን ሲሰማ በጣም ተደሰተ:: ይህ ከሆነ ለሠራዊቱ ምን እንበለው? በምን መልኩስ





ሐሳባችንን እንግለጽለት? ሲል ዓናንየህን አማከረው:: ዓናንየህም ይህን ጉዳይ ለኔ ተወው:: የቅርብ ታማኞቹ ሰዎችህን አናግራቸዋለሁ:: ቀሪው የሠራዊቱ ክፍል ግን በሐሳባችን ከተስማማና ከታዘዘን መልካም:: ካመፀ ግን እንዋጋዋለን:: ለቅርብ ሰዎቻችን ጉዳዩን ከነገርንና ከተስማሙበት ወታደሩ ውጊያ አይችሉንም" በማለት መለሰለት:: ከዚያም ዓናንየህ ለአውራዒ ዑስማን የቅርብ ሰዎች ምሥጢሩን አካፈላቸው:: አምሳ ፈረሰኞችና ሁለት ሺህ ባለጋሻ እግረኞች ናቸው:: አለቃችን እሳት ቢገባ እንኳ አብረነው እንገባለን:: ያዘዘንን እንፈጽማለን አሉት:: ዓናንየህ ለጌታው ለአውራዒ ዑስማን ታማኞቹ ታዛዥነታቸውን ነገረው:: አውራዒ ዑስማን እጅግ ተደሰተ:: የዚያን ቀን በዚህ ሁኔታ አነጋ:: በበነጋታው ለባለሚሎቹ ይህ ያለንበት ተራራ ለውጊያ አመች አይደለም:: ለፈረስ ግልቢያ ወደሚያመች ስፊ መሬት አሁኑኑ እንሂድና ለቀሪው ሠራዊት ያሰብነውን ጉዳይ እንንገረው:: ከተቀበሉን አላህ ያገራው ጉዳይ ስለሆነ መልካም:: ካመፁ ግን እዋጋቸዋለን፤ አላቸው:: መልካም ሐሳብ አቅርብሃል አሉት:: ጦሩ ጋራውን እንዲለቅ ትእዛዝ አስተላለፈ:: ከጋራው ወረደ:: ባለሚሎቹና ታማኞቹም ተከተሉት:: ስምንት የይፋት የጦር አበጋዞች ከነሠራዊቶቻቸው ተከተሉት:: የጋፋት ወታደሮችም እንዲሁ ተከተሉት:: የ"ወናግ ጃራ" ወታደሮች ብቻ ወደ ኋላ ቀሩ:: እነሱም አንድ ሺህ እግረኞች ናቸው:: ሁላቸውም እጅግ ከመንጣቱ ነጭ-ዘንቢል (ቅርጫት) የሚመስል ከቆዳ የተሠራ ነጫጭ ጋሻዎች አንግበዋል:: ከ"ባሕር አንባ" ወታደሮች ውስጥ መሰል የላቸውም:: አውራዒ ዑስማን ሊሰልም ማሰቡን ሲሰሙ ጋራው ላይ ቀሩ:: አውራዒ ዑስማን ከተራራው ወደ ሰፊው መሬት ወርዶ ወታደሮቹን ሲያሠልፍ፣ ምነው የ"ወናግ ጃራ" ወታደሮችን የማላያቸው የት

ቀርተው ነው? ሲል ጠየቀ:: "አልወረዱም" የሚል መልስ ተሰጠው:: ወደ ጋራው ሲያዩ ከዚያው ከጋራው ላይ እንደሆኑ ለውጊያ ሲዘጋጁ ተመለከቷቸው:: በዚህ ጊዜ አውራዓ ዑስማን "ምን አገኛችሁ? ከኔ ተነጥላችሁ የቀራችሁበት ሰበቡ ምንድን ነው? በማለት መልዕክት ላከባቸው:: ያሰብከውን አውቀናል:: ንጉሱን መክዳትህን ደርሰንበታል:: እኛ ግን የንጉሱ ታማኞችና ባሪያዎቹም ነን:: እንሞትለታለን:: ወደንተም አንመጣም:: ውጊያ ከፈለግክ ወደኛ ዝለቅ፣ ልንገጥምህ ዝግጁ ነን" የሚል በመልዕክተኛው መልሰው ላኩበት:: ጋሻዎቻቸውንም ወድረው ወደ "ቤተ አምሐራ" አቀኑ::

አውራዓ ዑስማን በበኩሉ ከይፋት ሙስሊሞች ጋር ሆኖ "ይፋት"ን በመልቀቅ ወደ "ጦቢያ" አመራ:: ከዚያም ደርሶ ኢማሙን ይጠባበቅ ጀመር:: ኢማሙ በዚያው በነበሩበት ሥፍራ "አቦንህ" ውስጥ ነበሩ:: ከአውራዓ ዑስማን ጋር ለመገናኘት ወደ "ጦቢያ" አቀኑ:: "ጦቢያ" ሲደርሱም የአውራዓ ዑስማንን ድንኳኖች ሲመለከቱ በአቅራቢያቸው ሰፈሩ:: አውራዓ ዑስማን ኢማሙ እንደመጡ ስላየ ከቦታው በመነሳት ፈረሶችንና ወታደሮችን ረድፍ አስይዞ ወደ ኢማሙ አቀና:: እንዲምሩትም ታላላቅ ሰዎችና የሃይማኖት አባቶች ቀድመውት ወደ ኢማሙ ገቡ:: ከኢማሙ ዘንድ ደረሰ:: ከላይ ያወጋናችሁ ሁለቱ ወደ ክርስትና የገቡት የኢማሙ አገልጋዮችም፣ የአውራዓ ዑስማን አጐት (የእናት ወንድም) ዋፋት ራስ፣ እና ገራድ አደም አብረውት አሉ:: ከኢማሙ ዘንድ በመግባት እጃቸውን ሳመ:: ኢማሙም መልካም አቀባበል አደረጉለት:: "አትፍራ" አሉት:: ለወታደሮቹም ስልሙ አላቸው:: ከዙህር (ቀትር) እስከ ዐሐይ መጥለቂያ ጊዜ ድረስ የመስለሙ ሥርዓት ተካሄደ:: ቁጥራቸው





ከልጆቻቸውና ከሴቶቻቸው ጋር 20000 (ሃያ ሺህ) ይደርሳል:: ኢማሙ አላህን አመሰገኑ:: አውራዓ ዑስማንንም አሞገሱት:: "ጦቢያ" ውስጥም ተቀመጡ::

## ኢማሙ ለጦር ሹማምንቶቻቸው ኃይላቸውን እንዲያሰባስቡና ውጊያ እንዲቀጥሉ ደብዳቤ መላካቸው

ከዚያም ኢማሙ ለወዚር ዓድሊ ደብዳቤ ላኩለት:: በወቅቱ "ዙቃላ" ውስጥ ነበር:: በርሱና በኢማሙ መካከል ያለው ርቀት 12 ቀናት ያስኬዳል:: አውራዓ ዑስማንና ወገኖቹ ባጠቃላይ መስለማቸውን አበሰሩት:: የተበታተኑ የጦር ሹማምንቶችን ከአንተ ዘንድ ሰብስብ፣ የበላይ አዛዣቸው አድርጌሃለሁ:: "በራራህ" ወደሚገኘው አሚር አቡበክርና ወደሌሎችም ወታደሮች በፍጥነት ከአንተ ዘንድ እንዲደርሱ ላክባቸው:: ከዚያ በኋላም ወደየትም አታዝምታቸው:: ፈጥጋር ውስጥ ተቀመጥ:: ቤተሰቦቻችንና ልጆቻችንም ከአንተው ጋር ይቀመጡ፣ በአላህ በአላህ አደራ እንልሃለን ሲሉም አሳሰቡት::

ኢማሙ ዓድሊን የጦሩ የበላይ አዛዥ ያደረጉት ሌሎቹ ወደየአገሮቻቸው የመሄድ ሐሳብ ስለነበራቸው ነው:: ዓድሊን አዛዥ ያደረገበት ምክንያት፣ የኢማም አህመድ አባት ሉሊ ስለነበርና ኢማሙንና ወንድሞቻቸውን ያሳደገ ታማኛቸው በመሆኑ ነው:: ይህም በመሆኑ ኢማሙ እርሱን ሳያማክሩ ምንም ነገር አይሠሩም ነበር::

ለወዚር ዓድሊ ደብዳቤው የደረሰው "ዙቃላ" ሳለ ነበር:: "ዙቃላ"ን ለቆ ፈጥጋር አጠገብ ወደምትገኘው "ማሲን" አቀና:: ከዚያም በተለያየ አገር ወደተበታተኑ የጦር ሹማምንቶች ወደእርሱ ዘንድ

እንዲመጡ መልዕክት ላከባቸው:: ሁሉም ወደእርሱ ዘንድ ከተቱ:: አሚር አቡበክርም እንደዚሁ የኢማሙን ቤተሰቦችና እቁባታቸውን ይዞ ከ"በራራህ" በመነሳት ዓድሌ ዘንድ ደረሰ:: ሁሉም ተካተው ሲጠናቀቁ ዓድሊ የኢማሙን ደብዳቤ አነበበላቸው:: እርሱ በነርሱ ላይ መሾሙንም ነገራቸው:: ..ታዛዦች ነን፡ አሉት::

ፈርሽሐም ዓሊ በወቅቱ "ደብረብርሃን" ነበር:: ለኢማሙ እንዲህ የሚል መልዕክት ላከባቸው:- እኔ ደብዳቤዎትን ወይም መልዕክተኛዎትን በመጠባበቅ ላይ ነኝ:: ያዘዙኝን እፈጽማለሁ:: እኔ ወደርስዎ ልምጣ ወይም እርስዎ ወደኔ ይመጡና መልዕክተኛው ከኢማሙ ዘንድ ደርሶ መልዕክቱን ነገራቸው:: እርሳቸውም እኔ "ይፋት" ምድር ገብቻለሁ:: አማችህ አውራዓ ዑስማን ሰልሟል:: የይፋት ሰዎችም በሙሉ ሰልመዋል:: እኔም ይፋት ውስጥ ተቀምጫለሁ:: የሚል መልስ ላኩበት:: ፈርሽሐም ዓሊ ከሙስሊሞች አገር የምትገኘውን የአውራዓ ዑስማንን እህት አግብቷል:: ለዚህ ነው ኢማሙ አማችህ አውራዓ ዑስማን ሰልሟል ያሉት:: እንዲህም ሲሉ አዘዙት:- በ"ደብረብርሃን" ያለፋይዳ አትቀመጥ:: ወደ "ተጉለት"፣ "ወቅዳ"፣ "መገር" አገሮች ገብተህ ነዋሪዎቹን እስኪሰልሙ ወይም ግብር ለመስጠት እስኪስማሙ ተዋጋቸው::" ፈርሽሐም ዓሊ የኢማሙ መልዕክት እንደደረሰው ወዳዘዙት ሥፍራ ዘመተ::

ኢማሙ "ይፋት" ውስጥ ለአሥር ቀናት ከተቀመጡ በኋላ ባልደረቦቻቸውን እንዲህ ሲሉ አማከሩ:- ወደ "ደብረብርሃን" እንዝለቅና ከፈርሽሐም ዓሊ ጋር ሆነን ባልደረቦቻችንን ይዘን ወደ ፈጥጋር በመመለስ ጦርነት አለ በተባልንበት ቦታ ሁሉ እየሄድን እንዋጋለን:: ሲሉ፡ ሁለት ሰዎች፣ አንደኛው የሰለመው አውራዓ ዑስማንና ሌላኛው ደግሞ ከርሱ በፊት





የሰለመው አዝማች ሐይብ ወደ "ደብረ ብርሃን" ባንዘልቅ ይሻላል አሉ:: ኢማሙም፡ እንዴት ይህን ሐሳብ ልታቀርቡ ቻላችሁ? አሏቸው:: ወደኋላ መመለስ ጥሩ መስሎ አልታየንም:: እነዚህ አገሮች ሁሉም ሰልመዋል:: ስለዚህ ከወደፊታችን ወደሚገኙት አገሮች ወደ "ጅድም" እና በዙሪያዋ ወዳሉ ከተሞች ብንሄድ የተሻለ ነው አሉ:: በዚህ ጊዜ ኢማሙ ገራድ አብጅድ ቢን አቦኝ የተባለውን ሰው በማስጠራት የአውራዓ ዑስማንን ወታደሮች ደርበውለት፣ ከእርሱም ጋር የዕቂምን፣ ጌታ ኑርን ሹኩርን ሰጥተውት ገራድ አቦኝ ወደ "ጅድም" በመዝመት ነዋሪዎቿን ሁሉ አሰለመ::

## የሐበሻው ንጉስ ከወጅ ምድር ወደ ቤተ አምሐራ መመለሱ

የሐበሻው ንጉስ ወናግ ሰገድ ወጅ ምድር ላይ ነበር:: የዝናቡ ወቅት እስኪያልፍ እዚያው ተቀመጠ:: እዚያው እያለም የወሰን ሰገድ መገደልና የወታደሮቹ መሸነፍ መርዶ ደረሰው:: በእጅግም አዘነ:: የቅርብ አበጋዞቹን፣ አጋፋሪዎቹን፣ እና ባለሚሎቹን ሰበሰበና አሁን ምን እናድርግ? ምንስ ትመክሩኛላችሁ? የትኛውንስ ምድር ይቀበለናል? ሲል ምክር ጠየቃቸው::

እርስ በርስ ተነጋገሩ:: ንጉሱም እኔ በበኩሌ የአያት ቅድመ አያቶቻችን መኖሪያና የግዛታችን መሠረት ወደሆነችው "ቤተ አምሐራ" ብንሄድና በሮችን ዘግተን ሙስሊሞችን ብንዋጋቸው፤ ሙስሊሞች የተቆጣጠሯቸውንም ሀገሮች ትተንላቸው ቤተ አምሐራ ላይ ብንሞት እመርጣለሁ አላቸው:: የጦር አበጋዞችም በአንድ ድምጽ "ንጉስ ሆይ" ያሉት ትክክል ነው:: ከእርስዎ በፊት እኛ እንሞታለን በማለት

መስማማታቸውን ገለፁ። ከ"ወጅ" ምድር ወደ ቤተ አምሐራ አቀኑ። በዝናቡ ወቅት ለአንድ ወር ያህል ከተጓዙ በኋላ ቤተ አምሐራ ደረሱ።

## የቤተ አምሐራ ገጽታ

ቤተ አምሐራ ሰፊ ምድር ናት። ሲሳይ ይበዛታል። በተራራዎች የተከበበች ናት። በተራራዎች መሐል የምትገኝና በተራራዎችም ውስጥ መንገዶችና መግቢያዎች አሏት። የግዛታቸው መመኪያም ናት። ከምድረ "አባወይን" እንስቶ እስከ ምድረ "ዓንቁት" እስከ ባሕረ "ሐይቅ" የሚያስገቡ መንገዶች እያንዳንዳቸውም በሮችና ጠባቂዎች ያሏት ናት። ዙሪያዋም ሃያ ቀናት በሚያስኬድ ተራሪዎች የተከበበች ናት። አምስት መግቢያ በሮች አሏት። አንደኛው በ"ወሉቃ" መንገድ፣ ሁለተኛው በ"አኼ ፌጅ" መንገድ፣ሦስተኛው በ"መንዝ" መንገድ፣ አራተኛው ከምድረ ጅድም በ"ሚያት" መንገድ፣ አምስተኛው በ"ዋሲል" መንደር መግቢያ ላይ የሚገኙ ናቸው።

ንጉሱ ቤተ አምሐራ ውስጥ ድንኳኑን ተከለ። የንጉሱ አማች አበጋዝ ደጅለሃን የሚያት በርን ያዘ። ንጉሱም በርህን በርትተህ ጠብቅ። ከአንተ በር በኩል ጥቃት እንዳይደርስብን አደራ፣ በማለት አዘዘው። ደጅላሃን በርሱና ወደርሱ በሚያደርሰው መንገድ መካከል ከጋራው ላይ ምሽግ ቆፈረ። የጊደምና ግማሽ ያህሉ የትግራይ ወታደሮች ታከሉለት። በመንዝ በር በኩል ደግሞ አበጋዝ ራስ ቢንያት እንዲጠብቅ ታዘዘ። ወታደሮች ታከሉለት። ከጋራው በላይም ምሽግ ተቆፈረለት። በአኺፌጅ በኩል ያለው መግቢያ በር ግን ሡራዊት አላስፈለገውም። በስድስት ሰዎች





ከተጠበቀ እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ማንም ጥሶት ሊያልፍ አይችልም። በወሊቃ በኩል ያለውን በር ደግሞ አበጋዝ ደሐርጐይታ ሡራዊቱን ይዞ ተሰማራበት። በሁሉም ደሐርጐይታ በራፎች ሙስሊሞችን የሚፋለም ጦር ተዘጋጅቷል።

## የቤተ አምሐራ ቤተክርስቲያን ገጽታ

ቤተ አምሐራ ውስጥ በንጉስ ወናግ ሰገድ አባት ንጉስ ናውድ የታነፀች ቤተክርስቲያን ትገኛለች። ሐበሻ ውስጥ ወደር አይገኝላትም። ንጉስ ናውድ እርሷን ለማነጽ ብዙ ደክሞባታል። በወርቅ አንቆጥቁጧታል። እርሷን በመገንባት አሥራ ሦስት ዓመት አሳልፎባት ግን ሳያጠናቅቅ ሞተ። ልጁ ወናግ ሰገድም ያባቱን ጅምር ለመጨረስ አባቱ ከተጨነቀው ይበልጥ ለቤተክርስቲያኗ እነጻና ውበት ተጨነቀ። ለሃያ አምስት ዓመታት ያህል ሲከሽናት ከቆየ በኋላ አጠናቀቃት። ዙሪያውን የተቀባችው ወርቅ እንደ እሳት ነበልባል እንድትንቦገቦግ አድርጓታል። ከውስጧ የወርቅና የብር ቁሳቁሶች አለባት። ጐንዋ መቶ ክንድ፣ ርዝመቷ መቶ ክንድ፣ ከፍታዋ መቶ ሃምሳ ክንድ ይሆናል። ሁለመናዋ ወርቅ በወርቅ ናት። በሉልና በሌሎች የከበሩ ድንጋዮች አጊጧለች። ንጉሱ "መካነ ስላሴ" በሚል ስም ይጠሯታል። ትርጉሙ የሦስቱ አምላኮች ማዕከል ማለት ነው። አላህ ከዚህ የክህደት ቃል ጠራ። ክብር ለርሱ ይሁን። እርሱ አንድ ብቻ ነው። "አልወለደም፡ አልተወለደም። አንድም ብጤ የለውም" (አል-ኢኽላስ" 3-4)..

ቤተክርስቲያኗ ውስጥ የንጉሱ ናውድ ኢብን አድማስ የኢብን ዘራያዕቆብ ቀብር ይገኛል። ሌሎች የቀደሙት ነገስታት ያሠሯቸው ቤተክርስቲያኖች

ቢኖሩም የዚህችን ቤተክርስቲያን አሠራር ምስል ያላቸው አይደሉም፡፡

ንጉሱ ወታደሮቹን ወደየበሩ አስማርቶ ከጨረሰ በኋላ ወደ አባቱ ቤተክርስቲያን በመግባት ግራና ቀኙዋን አየና አነዚህ "ሙስሊሞች ይህችን የኔም የቀደምት ንጉሶችም የንግስና ማዕከል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ሊያቃጥሏት ይፈልጋሉ" አለ፡፡

እያንዳንዱ የሐበሻ ንጉስ በቤተ አመሐራ ውስጥ ቤተክርስቲያን ያሠራል፡፡ ሲሞት በሳጥን ውስጥ አድርገው ከቤተክርስቲያኗ ውስጥ ይቀብሩታል፡፡ ንጉሱ ከላይ ያወሳነውን ቃል እንደተናገረ አብረውት ያሉት "ንጉስ ሆይ" ሐሳብ አይግባህ፣ አትጨነቅ፡ ሙሥሊሞች የተናገርከ ላይ ፈጽሞ አይደርሱም፡፡ እንሞትላታለን፡፡ እስከመጨረሻው እንፋለማለን" አሉት፡፡ እርሱም "ይህ ቃላችሁ ከሆነ ሁላችሁም በር በራችሁን ጠብቁ አላቸው፡፡ "ታዛዦች ነን" በማለት ወደየተመደቡበት አቅጣጫ አመሩ፡፡ ንጉሱም ወደ ዋሲል በር በመሄድ ከዚያው ተቀመጠ፡፡

## ኢማሙ ካሳያ መድረሳቸውና በየአቅጣጫው የተበታተኑ የጦር ሹማምንቶቻቸው ወደርሳቸው እንዲከቱ ማዘዛቸው

ኢማሙ በበኩላቸው አብጀድ ከሄደ በኋላ ተከትለውት ተንቀሳቀሱ፡፡ ጉዌይታ ኑርም "ጅድም" ምድር ውስጥ ወደምትገኘው ወደ ካሳያ እንዲያመራ አዘዙት፡፡ ወደዚያም አመራ፡፡ "ጅድም" ውስጥ የቀደምት ነገስታት ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ትገኛለች፡፡ በቤተክርስቲያኒቷም አንድ ሺህ መነኩሴዎች ይኖሩባታል፡፡ ጉዊታ እንደደረሰም አቃጠላት፡ ውስጧ





የነበረውን ወርቅና ሌሎች ሃብቶች ዘረፈ፡፡ ኢማሙም እሱ ከሄደ በኋላ እርሳቸው ጥቂት ወታደሮችን ይዘው ወደ ካሳየህ አቀኑ፡፡ ከሳየህ ደርሰውም ሰፈሩ፡፡ ወደ ጃን ሀገርም "ስለሙ" የሚል መልዕክተኛ ላኩ፡፡ ኢማሙ ጃን ሲገቡም ከፊሉቹ ሰለሙ፡፡

አብጀድም ከሳየህ ምድር ላይ ከኢማሙ ጋር ተገናኘ፡፡ ከክርስቲያኖችም ወሰን ሠገድ ነጫጭ ከቆዳ የተሠሩ ጋሻዎች የያዙ አምስት መቶ እግረኞችን አስከትሎ በመግባት ከነወታደሮቹ በኢማሙ እጅ ሰለሙ፡፡ የሐበሻ ሰዎች ከፈረስ ይበልጥ በነጭ ጋሻ ይፎካከራሉ፡፡

## የንጉሱ አገልጋይ የሆነው ሙስሊም

አርሹነህ ከተባለች አገር ከሚኖሩ ሙስሊሞች መካከል አንዱ ንጉሱን ያገለግል ነበር፡፡ ንጉሱ ዘንድም ክብርና ሞገስ ነበረው፡፡ አማሙ ከሳያህ ሲደርሱ ይህን ሰው ወደ አልፈቂህ አቢበክር አል አርሹኒ ዘንድ እንዲህ የሚል መልዕክት አስይዞ ላከው፡- ከኢማሙ ዘንድ የደህንነት ዋስትና ተቀበልልኝ፡፡ ምክንያቱም ሙስሊም ሆኜ ንጉሱን በማገልገሌ እንዳይቀጡኝ እሰጋለሁ፡፡..

አልፈቂህ (ሊቁ) አልአርሹኒም ከኢማሙ ዘንድ በመግባት ዋስትናውን ተቀበለለት፡፡ ኢማሙም አዛን አድራጊያቸው ከቢር ኑርን ላኩለት፡፡ የዚህ ሰው ስም ሻፊዐ ይባላል፡፡ የፈቂህ አርሹኒ ሀገር የሆነችው የአርሹነህ ሰው ነው፡፡ የኢማሙ አዛን አድራጊ ወደዚህ ሰው በመሄድ ለኢማሙ ከተዘጋጁ ውድ ዕቃዎችና ለንጉሡ ከሚደለቡት የሚያማምሩ በቅሎዎች ጋር ከኢማሙ ፊት አቀረበው፡፡ ኢማሙ የሐበሻው ንጉስ የትኛው መንደር እንደሚገኝ ጠየቁት፡፡ "ቤተ አምሐራ"

ውስጥ ነው፡ ወታደሮቹን ከፋፍሎ በየበሩ አስማርቷል:: አማቹ ደጅለሃን ከእናንተ ቅርብ ነው:: ያለውም ሚያት በር ላይ ነው:: ንጉሡ ግን ዋሲል በር ላይ ነው:: ደጅለሃን ወደርሱ እንድሄድ ልኮብኝ ነበር:: ግን እናንተ ከሳያህ ምድር መድረሳችሁን ስሰማ እርሱን ትቼ ወደናንተ መጣሁ፡ አላቸው:: በኛና በንጉሱ መካከል ያለው ርቀት ምን ያህል ይሆናል? ኢማሙ አሉት:: "ስድስት ቀን ያስኬዳል:: ከጀልሃን ያላችሁበት ርቀት ደግሞ የአራት ቀን መንገድ ሲሆን በናንተና በራስ ቢንያት መካከልም ይህ ጋራ ነው የሚለያችሁ:: የአንድ ቀን መንገድ ብቻ ነው አላቸው:: ኢማሙ ይህን ወሬ እንደሰሙ:: ለአሚር ዓሊ፡- ያለህበትን አገር ትተህ ቶሎ ና:: ለጥብቅ ጉዳይ እፈልግሃለሁ፣ የሚል መልእክት ላኩበት:: መልእክተኛው በመጓዝ ላይ እያለ ከአሚር ዓሊ ከመድረሱ በፊት መንገድ ላይ ተገደለ:: ኢማሙ መገደሉን አላወቁም:: ወዚር ዓድሊ ንየጦር ሹማምንቶች የበላይ አዛዥ አድርገውት ስለነበር፣ እንደዚሁ በዚሁ ዕት ወደ እርሱም መልዕክት በመላክ፣ አብሰማኑርን ከጦር ጋር አድርገህ ላክልኝ ሲሉ፣ ፃፉለት:: ወዚር ዓድሊም አብሰማኑርን ከስልሳ ፈረሰኞችና ከበርካታ እግረኞች ጋር አድርጎ ላከው:: አብሰማኑር "ከሳያ" ላይ ከኢማሙ ጋር ተገናኘ:: በእጁም የወዚር ዓድሊን ደብዳቤ ይዟል:: የደብዳቤው መልዕክት እንዲህ የሚል ነው:- እርስዎ ያዘዙንን ፈጽመናል:: አሁን ያለነው በ"ፈጥጋር" ምድር ውስጥ "ላሊበላ" ላይ ነው::"





## ኢማሙ ለወዚር ዓድሊ የጻፉት ደብዳቤ

ኢማሙ ለአብሰማኑር አቀባበል አደረጉለት:: ስለአሚር ዓሊም ጠየቁት:: የትኛው ምድር ላይ ነው ያለው? ወደ እኔ እንዲመጣ መልዕክተኛ ልኬበት ነበር:: ግን እስካሁን መልስ አላከለኝም አሉት:: የላኩት መልዕክተኛ መንገድ ላይ የደረሰበትን ኢማሙ አላወቁም ነበር:: ሁለተኛና ሦስተኛ መልዕክተኞችን ላኩበት:: እነርሱም መንገድ ላይ ተገደሉ:: ኢማም ለአብሰማኑር፣ አሚር ዓሊ የት እንዳለ አናውቅም:: ምን እናድርግ? ካሉ በኋላ ለወዚር ዓድሊ መልዕክት እንላክበትና፣ እርሱ በርካታ ሠራዊት ስላለው በከፊል ወታደሮች ይላክልን:: ቀሪዎቹ ወታደሮች ከርሱ ጋር ይሁኑ በማለት እንዲህ የሚል ደብዳቤ ለዓድሊ ጻፉለት:: ለወዚር ዓድሊ የጻፉት ደብዳቤ እዲህ የሚል ነው:- በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ ለሆነው የዓለማት ጌታ ለአላህ ምስጋና ይድረሰው:: በመሪያችን በነቢዩ ሙሐመድ እና በቤተሰቦቻቸው ላይም የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን:: ከሙሥሊሞች ኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም አልሙጃሂድ ለወዚር ዓድሊ፣ ብቸኛ አምላክ ለሆነው አላህ ምስጋና አቀርባለሁ:: በነቢዩ ሙሐመድ ላይም እዝነቱን እንዲያሰፍን እማፀነዋለሁ:: ከ"ጅድም" ጊደም ምድር ካሳየ ውስጥ መግባታችንን እንድታወቀው:: ንጉስ ወናግ ሰገድ ቤተ አምሐራ ውስጥ ሰፍሯል:: ወታደሮቹንም ከፋፍሎ ሁሉንም መግቢያ በሮች እንዲዘጉብን አስማርቷል:: ለአሚር ዓሊ ወደእኔ እንዲመጣ ደብዳቤ ብልክለትም ወሬውም መልሱም እስካሁን አልመጣልኝም:: ዬት እንደገባም አላውቅም:: ከእኔ ዘንድ ያለው ሠራዊት ቁጥሩ አናሳ በመሆኑ ከጠሩ

ከፍለህ ከአሚር አቡበክርና ከአሚር ሙጃሂድ ጋር ሁለት መቶ ፈረሰኞችንና የባሕር እግረኛ ወታደሮችን በአስቸኳይ ላክልኝ:: ሰላም ላንተና አብረውህ ላሉት ሙስሊሞች ይሁን::

መልዕክተኛው ሌት ተቀን ተጉዞ ከአስር ቀናት በኋላ ከወዚር ዓድሊ ዘንድ ደረሰ:: አገኘውና ደብዳቤውን ሰጠው:: ወዚር ዓድሊ ሙስሊሞችን ሰበሰበና የኢማሙን መልዕክት አነበባላቸው:: ሁለት መቶ ፈረሰኞችንና በሕር በመባል የሚታወቁ አምስት መቶ ጋሻ ያነገቡ እግረኞችን እንዲሁም ሌሎች በርካታ ሰዎችን አዘጋጅቶ ትጥቅና ስንቃችሁን በመያዝ ወደ ኢማሙ ሂዱ ሲል፤ አዘዛቸው:: አሚር አቡበክር ቀጨን፣ አሚር ሙጃሂድና መሰሎቻቸውን የጦሩ አዛዦች አደረጋቸው::

## ኢማሙ የተሠባጠሩ ሠራዊታቸውን በመጠበቅ ካሣያ ውስጥ አርባ ቀናት ማሳለፋቸው

ኢማሙ በአቅራቢያቸው ያሉት የተሠበጣጠሩ ወታደሮችን ለማሰባሰብ እየተጠባበቁዋቸው ካሣያ ላይ ወር ከአሥር ቀን ቆዩ:: ከነወታደሮቹ በመጀመሪያ" ከእርሳቸው ዘንድ የደረሰ ሽምሱዋ ነበር:: የኢማሙ ሙአዝን (ሰላት ጥሪ የሚያስተንባ) ከቢር ሙሐመድ አብሮት አለ:: ጦሩ በአሥራ አምስት ፈረሰኞችና በአንደ ሺህ እግረኞች የተዋቀረ ነው::

አሚር ፈርሽሐም ዓሊ ግን እስከዚህ ወቅት አልደረሰም ነበር:: ምክንያቱም በ"ተጉለት"፣ በ"ወጅዳ" እና በ"መገር" ምድር ውስጥ ለሁለት ወራት ያህል ቆይቶ ስለነበር ነው:: ከዚያም ወደ "ደብረብርሃን"





ተመልሶ እዚያው በመቀመጥ የኢማሙን ወሬ የሚያመጡ ሰዎችን ወደ "ይፋት" ምድር ላከ:: "ጠቢዩ" ደረሱ:: የገራድ አህሙሻ ወኪል ይገኝባት ነበር:: ከርሱ ዘንድ በመግባት የፈርሽሐም ዓሊን ወሬ ነገሩት:: ፉት ነው ያለው ብሎም ጠየቃቸው? ኢማሙ ሦስት ጊዜ መልዕክተኛ ልከውበት ሦስቱም በከሓድያን ተገደሉ:: ኢማሙ የመልዕክተኞችን መገደል አላወቁም:: ፈርሽሐም ዓሊ ሩቅ አገር ነበር፤ አሁን ግን "ደብረብርሃን" ገብቶ የኛን መልስ እየጠበቀ ነው፤ አሉ:: አሁኑኑ ወደርሱ ሂዱና እንዲህ በሉት:- ኢማሙ ሦስት ጊዜ መልዕክተኛ ልከውብህ ሦስቱም መንገድ ላይ ተገደሉ:: ኢማሙ ተቀምጠው ያንተን መምጣት በመጠባበቅ ላይ ናቸው:: ይህ መልዕክት እንደደረሰህ ወዲያውኑ ተነሳ:: ኢማሙ ያሉት በካሣያ ምድር ነው በሉት፤ አላቸው:: መልዕክተኛው ከፈርሽሃም ዓሊ ዘንድ ደርሶ ወሬውን ሲነግሩት፤ ፈርሽሃም ዓሊ ይህን ሲሰማ ስለ ኢማሙ ሥጋት አደረበት:: ለኢማሙ ጥቂት ሠራዊት ብቻ ትተንላቸው በመበተናችን ጥሩ አላደረግንም በማለት፤ ወዲያውኑ ኢማሙ ወደሚገኙበት ከ"ደብረብርሃን" ተንቀሳቀሰ::

ኢማሙ በበኩላቸው ፈርሽሃም ዓሊን በክፉ እስከመጠርጠር ደረጃ ደርሰው ነበር:: ለርሱ ያሳዩት የነበረው መልካም ስሜትም ተቀየረ:: ኢማሙ "ካሣያ" ተቀምጠው ሳሉ ከስድስት ቀናት በኋላ ነበር ከርሳቸው ዘንድ የደረሰው:: ወታደሮቼን ይዘህ የሠራኸውን ሠራህ:: ለመሆኑ የትኛውን አገር አቀናህ? አሉት:: "ጌታዬ ሆይ" ተሳስተዋል:: ይህ መልዕክት ብቻ ነው የደረሰኝ፤ አላቸው:: ቀጥሎም ገራድ ቢሻረህ፣ ገራድ አህመዱሽና ገራድ ዓቢድ ለኢማሙ እንዲህ አሉዋቸው:- ጥሩ አልሠራንም፣ ያለ ሠራዊት ትተንዎት ወደአዘዙን ተሠማርተናል፤ አሁን የምናቀርበው

ምክንያትም የለንም አለ፡፡ ኢማሙም ለእነሱም ለወታደሮቹም ቦታችሁን ያዙ ሲሉ አዘዙ፡፡ ሙስሊሞች እርስ በርስ ተገናኙ፡፡ አላህንም አመሰገኑ፡፡

## አሚር አቡበክር ቀጨን ለኢማሙ ከወዚር ዓድሊ የተላከ ድጋፍ ይዞ መድረሱ

ከእነሱም ቀጥሎ ከሁለት ቀናት በኋላ አሚር አቡበክር ጦሩን ይዞ ደረሰ፡፡ ከኢማሙ ሰፈር አቅራቢያ ሲደርሱም ፈረሶቻቸውን ተቆናጠው የባሕር ወታደሮቹንም ከፈረሶች ፊት አሰልፈው ለውጊያ በሚዘጋጁበት አኳኋንና ሥርዓት ከኢማሙ ፊት ቀረቡ፡፡ ኢማሙም አደራረጋቸውን አመሰገኑላቸው፡፡ ከዚያም ከፈረሶቻቸው እንዲወርዱ አዘዟቸው፡፡ ወረዱና ከኢማሙ ጋር ተነጋገሩ፡፡ ኢማሙ ወዚር ዓድሊን የት አገር ተዋችሁት? ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ የተውነው "ዙቃላ" መሬት ላይ ነው አሏቸው፡፡ ከርሱ ከተለያችሁ ስንት ቀን ሆናችሁ?". በማለትም ጠየቋቸው፡፡ እርስዎ ዘንድ እስክንደርስ አሥራ ሁለት ቀናት ነው፣ ከንጋት እስከምሽት በቅሎ ላይ ተፈናጠን እየተጓዝን ነበር፣ ይኼውም ከእርስዎ ዘንድ ቶሎ ለመድረስ በመሻት ስንል፣ በየቀኑ ማለዳ በቅሎዎቻችን ላይ እንወጣና የምንወርደው በፀሐይ መጥለቂያ ወቅት ነበር፣ አሏቸው፡፡ ኢማሙም መርቀዋቸው፣ በልግሥናም አስተናገድዋቸው፣ የሐበሻውን ንጉስ ወሬም አጫወቷቸው፡፡ ከዚያም በኋላ ኢማሙ ባለሟሎቻቸውን ሰብስበው እንዲህ አሉዋቸው፡- ወታደሮቻችንና ፈረሰኞቻችን ተሰባስበዋል፣ አሁን በ"ቤተ አምሐራ" ጉዳይ ምክራችሁን አጠቃሉ፡ እኔ በዚህ ጉዳይ ሃሣቤን ቆርጫለሁ፡ ወደ ሐበሻው ንጉሥ እናመራለን አሏቸው፡፡ በዚህ ጊዜ የኢማሙ አዛን አድራጊ ከቢር ሙሐመድ





ተነሳና ለሙስሊሞች እንዲህ አላቸው፡- እናንተ ወደ "ቤተ አምሐራ" ለመሄድ ቁርጥ ውሳኔ አድርጋችኋል፣ ይህች ከኋላችን የተውናት የ"ሸገራ" አገር ነዋሪዎችም ሠልመዋል፣ ሁላችንም ጥለናት መሄድ የለብንም፡፡ እኔና ሸምሱ ወደ እርስዋ ዘንድ ከመጣን በኋላ በዚህች አገር አንድም የቀረ የለም፡፡ አሁን አንዳችን መመለስ አለብን፡፡ እንዲሁ ባዶዋን ከተውናት ነዋሪዎቿ ወደ ክህደት ይመለሳሉ ሲል ተናገረ፡፡ ኢማሙም መልካም ብለሃል፡፡ አንተና በቅርቡ እስልምናን የተቀበሉ ወታደሮችህ ተመለሱ፡፡ ከኢሥላም አገሮች (መንደሮች) የመጡ፡ ዋናዎቹ ሙስሊሞች የነበሩ ወታደሮች አይከተሉህም፡፡ አንተም ከእነሱ ተጠንቀቅ፣ በአላህ በረከት ተጓዝ፣ አላህ ይረዳሃል አሉትም፡፡

## የንጉስ እስክንድር የተቀበረ ሃብትና ገጽታው

እንዲህም ሆነና ከቢር ሙሐመድ ወደ "ሸጀራ" ተመለሰ፡፡ ወረብ ገብቶ አንድ ቀን እንደደረም የአገሬው ነዋሪዎች እንዲህ አሉት፡- ሸምሱዋ ካቃጠላት ቤተክርስቲያን አጠገብ ንጉስ እስክንድር ለቤተክርስቲያኗ በስለት ያስገባው የተቀበረ ወርቅ አለ፡፡ እነዚህ ከአንተ ጋር ያሉት ወታደሮች-አብረውት ካሉት ወታደሮች ወደ ጥቂቶቹ በማመልከት-ቦታውን ያውቁታል፡፡ እነርሱው ራሳቸው ያወጡታል፣ አሉት፡፡ ከቢር ሙሐመድ ይህን እንደሰማ የተጠቆሙትን ወታደሮች አሰረና ንብረቱን እንዲያወጡ አስገደዳቸው፡፡ በወርቅ የተሞላ አሥራ ሁለት ታኒካ አወጡለት፡፡ ለነዚያ ወሬውን ያመጡለት ሰዎችን ከተቀበረው ሃብት የቀረ ይኖራልን? በማለት ጠየቃቸው፡፡ አዎ ትልቅ ሳህን ይቀራል፡፡ መጠኑ ክብደቱ ሰባት መቶ ወቄት

ይደርሳል፡፡ ሁለት እጀታዎች ሲኖሩት እያንዳንዳቸው ሙቶ ወቄት ይመዝናሉ አሉት፡፡ በዚህ ጊዜ ወታደሮቹን የቀረውን ሳህን አምጡ በማለት አስገደዳቸው፡፡ እሺ ብለውት እርስ በርሳቸው ምክክር ያዙ፡፡ ይህንን ንጉስ እስክንድር ለቤተክርስቲያኗ በስለት ያስገባውን ሳህን ከሰጠናቸው ምናልባት ሙስሊሞች ወደሀገራቸው ከሄዱ ወይም እዚሁ እያሉ ካለቁና፣ ንጉሱ የተቀበረውን ሀብት ለምን አወጣችሁት? ይለናል፡፡ በዚህ ሰበብም ይቀጣናል፡፡ ስለዚህ ይህን ሰው ለመግደል መላ መምታት አለብን፡፡ እንዲያግዙንም ለወገኖቻችን እንላክባቸው ተባባሉ፡፡ ከመካከላቸው አንዱ ጫካ ውስጥ ያደፈጡ ክርስቲያኖችን አውቃለሁ ሲል፣ ማልዳችሁ፣ እንደደረሳችሁ እንዘምትበታለን፡፡ ከኛ ሰዎች ውጭ አንድም ወታደር አብሮት የለም፣ ብላችሁ ላኩባቸው አላቸው፡፡

እንዲህም ሆነና በምሥጢር ላኩባቸው፡፡ ያሰቡትንም ነገሯቸው፡፡ ሰዎቹ ሌሊት ተነስተው ከሀገሩ ደረሱ፡፡

## የከቢር ሙሐመድ መገደል

ከቢር ሙሐመድ ይህን ሁሉ አላወቀም ነበር፡፡ ከጋራው ሲወርዱ ተመለከታቸውና እነዚህ እነማን ናቸው? በማለት ወታደሮቹን ጠየቀ፡፡ አንተን ለመዋጋት የመጡ ኢአማንያን ናቸው አሉት፡፡ በዚህ ጊዜ ፈረሱን አዘጋጅቶና የጦር ልብሱን ለብሶ በመጋለብ ወታደሮቹን ለውጊያ ተዘጋጁ አላቸው፡፡ ታዛዦች ነን በማለት ከፊት ለፊቱ ሆኑ፡፡ ኢአማንያን በቀረቧቸው ጊዜ እንደሚዋጉ ለማስመሰል ለአንድ ሰዓት ያህል በወንጭፍ ተወራወሩ፡፡ በመጨረሻም ከቢር ሙሐመድን ብቻውን አጋፍጠው ከወገኖቻቸው ጋር ተቀላቀሉ፡፡





እየተዋጋ ከመካከላቸው ገባ፡፡ ቦታው ጠባብ በመሆኑ ለፈረስ ግልቢያ አይመችም ነበር፡፡ ኢአማንያኑ ሁሉም እግረኞች ነበሩ፡፡ በብዙ ድንጋይ እስኪያጠቁት ድረስ በብርቱ ሁኔታ ተዋጋቸው፡፡ በመጨረሻም መስዋእት ሆኖም ከፈረሱ ወደቀ፡፡ አላህ ይዘንለት፡፡

## ኢማሙ የሐበሻው ንጉስ ወደሚገኝበት ዋሲል ተራራ ስላደረጉት ጉዞ

ኢማሙ ከ"ከሳየ" ተንቀሳቅሰው ከሁለት ቀናት በኋላ "ሐንቡሬ" ምድር ገብተው እዚያው ሠፈሩ፡፡ ኻሊድ አል ወራዲ የ"ቁት" ሰዎች የሆኑ የአገው ወታደሮች ጋር ሆኖ ወደ ኢማሙ ደረሰ፡፡ ከዚያም "ሐንቡሬ"ን ለቀው ከሁለት ቀናት ጉዞ በኋላ "መያት" ገቡ፡፡ ደጃዝልሃን ካለበት መውጫ በርም ደረሱ፡፡ ደጃዝልሃን ወደ ሙሥሊሞቹ ጋራው ላይ ሲያይ፣ ፈረሱን ጫነ፣ ሠራዊቱንም አዘጋጀ፣ ነጋሪቱንም ጎሰመ፡፡ መርዛማ ቀስት ያነገቡ ቀስተኞችን ውጊያ ግጠሙዋቸው ብሎ ወደ ሙሥሊሞቹ ላካቸው፡፡ እንደአዘዛቸውም ከጋራው ወረዱ፡፡ ኢማሙም እንደአዩዋቸው ወደ ጋራው እስኪቀርቡ ወደ እነሱ ተንቃነቁና፣ እዚያው ከምትገኝ ዛፍ ሥር ተቀመጡ፡፡ የጋራው ሁኔታም አስገረማቸው፡፡ አንድ ጠባብ መንገድ በስተቀር ሌላ መንገድ የለውም፡፡ አንድ ሰው በላይ አያሳልፍም፡፡ ከጋራው ላይም የታረሱ ማሣዎችና አዝርዕቶች፣ እስኪታረሱት ሥፍራ ድረስ የሚወርዱ ወንዞችም ጋራው ላይ አሉ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢማሙም ሳያውቁ የተወሰኑ ሙስሊሞች ወደ ጋራው ወጡ፡፡ ከመካከላቸው የዓረብ ቀስት ወርዋሪዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነሱም ዓብዱሡላም አልሪፊ እና ወንድሙ ሐሡብ አንነቢ

ይገኙባቸዋል። ከጋራው ወደ ቁልቁል እየወረዱ ካሉት ከኢአማኒያን ቀስተኞች ጋር ተገናኙ። ውጊያም አደረጉ። በቀስትም ተወራወሩ። ኢአማንያኑ ሙሥሊሞቹ ላይ አንድ ወጥ የሆነ ወረራ ሠነዘሩባቸው፡ ቀስታቸውም እንደዝናብ ይወርድ ነበር። ከባድ ውጊያም ተዋጉ። የሚደነቁት ዐረቦች ወራሪዎች የሞት የሽረት ውጊያ ተዋጉ። ሐሠብ አነቢ ከኢአማኒያኑ መካከል አንዱን በቀስት ወግቶ ገደለው። ወንድሙም ሌላ ኢአማኒያኑን ገደለ። ውጊያው ድብልቅልቁ በመውጣቱ ኢአማኒያኑና ሙስሊሞች ተቀላቀሉ። ዓብዱሠላም አልሪፊ (ገጠሬው) የሚባል ሰው አንድን ኢአማኒ አጠቃ፤ እግሩን መታውና ቆርጦም ጣላት። ባልንጀራው አልሐጅ ዓሊ አግዞት ገደሉት። ከሙስሊሞችም አቦኝ የተባለ የኢማሙ ፈረስ ጠባቂ ኢማኒያኑ ከጋራው ላይ የለቀቁበት ናዳ ቋጥኙ ራሱን መታውና አንጎሉ ተፈጥፍጦ በረረ። አሁን ሕልሜ እውን ሆነ፣ አለ። መስዋእትም ሆነ። ይህ ሰው ከአሚር አቢበክር ጋር ኢማሙ ዘንድ ከደረሰው የድጋፍ ጦር ጋር በመጓዝ ላይ እያለ ሕልም አይቶ ነበር። አረንጓዴ ዎፍ የሚመስል ከራሴ ላይ አረፈና፤ ነፍሴንም ነጠቃት። ሞትኩም ሲል ሕልሙን ለባልደረቦቹ አወጋቸው። እነርሱም፡- መልካም ሕልም አይተሃል ሲሉት፣ እርሱም፡- በዚህ ዘመቻ መስዋእት እሆናለሁ ብሏቸዋል። እንዳለውም ሕልሙ ፀደቀለት።

ይህ ከሆነ በኋላ ኢማሙ ወደጋራው ሲያዩ ሙስሊሞቹ ከጋራው ጫፍ ላይ ከኢአማኒያኑ ጋር እየተዋጉ አዩ። በእጅግም ተቆጡና፡ እንዲዋጉ ማን አዘዛቸው? ሲሉም ጠየቁ። መልዕክተኛ ልከውም እንዲመለሱ አዘዟቸው። ሰማእታቱን አቦኝ ተሸክመው ተመለሱ። ቀበሩትም። ከዚያም ኢማሙ ድንኳናቸውን ተከሉ። ሙስሊሞችም እንዲሁ ድንኳኖቻቸውን ተከሉ።





ኢማሙ ሙስሊሞችን ሰበሰቡ። አውራዒ ዑስማንን አና መንድ መሪዎችን አስጠሯቸው። እነርሱም ዐናንየህ፣ ሐይብና እስልምናን ትቶ ወደ ክርስትና የገባው አይቢስ ለሕጤይ ነበሩ። አይቢስ ለሕጤይ እንዲህ ሲል ተናገረ፡- ጋራውን እያየኸው ነው። መንገዱም እጅግ አስቸጋሪና ለፈረስ መተላለፊያ የሚሆን የለውም። ያለፈረስ ልትወጡት ካሰባችሁም አትችሉትም። ይህን አቢጋዝ ብትዋጉና በእርሱ ላይ አላህ ድል ቢያጐናጽፋችሁም ወደ ንጉሡም ሆነ ወደ ቤተ አምሐራ መድረስ አትችሉም። ምክንቱም ከጋራው በታች ምሽጐችና ሸለቆዎች አሉ። ከቤተ አምሐራ ወዲህም አስቸጋሪ መንገድ አለ። ከዚያው ላይ ይዋጓችኋል። ይህን አቢጋዝ መዋጋት ትታችሁ ወደ ዋሲል መግቢያ ብታቀኑና ውጊያችሁ ከዚያ ላይ ቢሆን መልካም ይመስለኛል። አላህ ድልን ከሰጣችሁ ቤተ አምሐራ ለመግባት የሚያግዳችሁ ምንም ነገር አይኖርም። ይህ አቢጋዝ የሚፈይደው ነገር የለም። ንጉሱ ከተሸነፈ በኋላ ከቦታው አይንቀሳቀስም። ትክክለኛውን ስልት ነው የነገርኳችሁ አለ። ዓናንየህ ቆመና አይበስ ለሕጤይ እውነት ብሏል። የሰጠው አስተያየት ትክክል ነው። እኔም ይህን ሀገር በሙሉ አውቀዋለሁ። አሁን ያለንበት ጋራ ፈረስ የሚያሳልፍ መንገድ የለውም። ንጉሱ የሚገኝበት መንገድ ወደ "ዋሲል" የሚወስደው ነው። ፈረሶቹ ንጉሱ ዘንድ እስኪደርሱ በዚያ መንገድ መጓዝ አይቸግራቸውም ሲል አስተያየቱን ሰጠ። ኢማሙ አይበስ ለሕጢይና ዓናንየህ የሰጡትን ምክር ለገራድ አህመሻ፣ ለአሚር ዘህረቦኝ፣ ሙሐመድና ለአሚር አቡበክር ቀጪን ለተባሉ ሹማምንቶቻቸውና አማካሪዎቻቸው ነገሩ። ጥሩና ትክክለኛ ምክር ነው። በሦስትና በአራት (በሮችም) ጦርነት አንከፍትም። ውጊያችን በአንድ

ብቻ እንዲሆን ማድረግ አለብን ሲሉም በዚህ ሐሳብ ተስማሙ:: ሌሊቱንም ከጋራው ሥር አሳለፉ::

የሌሊቱ ሩብ እንደተገባደደ ከተራራው ላይ ሆነው ሙስሊሞቹን ያጠቁ የነበሩ ኢአማኒያን ከጦር ሰፈሩ ቀርበው እንደገና በቀስት ጥቃት ከፈቱ:: ከሶማሊያዊው መታን አጠገብ ነበሩ:: እርሱም ፈረሱን ጋለበና ወደጋራው ጫፍ እስኪወጡ ድረስ አጥቅቷቸው ወደቦታው ተመለሰ:: የቀስቶቻቸው ፍላጻዎች አንድንም ሙስሊም አልጎዱም:: መሬት ላይና በየድንኳኖቹ ተሰክተው ቀሩ::

## ደጀልሃን ወደ ንጉሡ ደብዳቤ መላኩና፣ ኢማሙንና ወታደሮቻቸውን በውጊያ እንዳሸነፈ በመግለጽ ያሠፈረው የሐሰት ወሬ

ደጀልሃን ሌሊት ሙስሊሞችን ያጠቁት ቀስተኞች ወደርሱ እንደተመለሱ ወዲያውኑ ለንጉሱ ደብዳቤ ጻፈለት:: እንዲህም አለ:- "ኢማሙ ሠራዊታቸውን ይዘው ከኔ ዘንድ ደርሰው ነበር:: በሩን ዘጋሁባቸው:: በጽኑም ተዋጋኋቸው:: አንድ መቶ ሃምሳ የኢማሙን ወታደሮች ገደልኩ:: ሰላሳ ፈረሶችም ማረኩ:: ፈረሰኞችንም ገደልኳቸው:: ሙስሊሞችም ወደኋላ አፈገፈጉ:: ሰፊ ቦታ ላይም ሰፈሩ:: ሌሊት ላይ የትግራይ ሰዎች የሆኑ ቀስተኞችን ላኩባቸው:: አጠቋቸውና ብርቱ ጉዳትም አደረሱባቸው:: ብዙዎቹንም ገደሏቸው:: ሊቋቋሙን አልቻሉም:: ወደ "ፊጥጋር" መሸሽ ይፈልጋሉ:: ደብዳቤውን በሁለት እግረኞች ወደ ንጉሱ ላከ:: በሌሊት ተጉዘው ከንጉሱ ዘንድ ደረሱና ደብዳቤውን ለንጉሡ አስረከቡ::





በደብዳቤው ያሰፈረውን መልዕክት ሲመለከት ከፍተኛ ደስታ ተሰማው:: ፊነደቀና ዘውዱን በራሱ ላይ ደፍቶ፣ ዙፋኑ ላይ በመቀመጥ መልዕክቱን ለወገኖቹ ነገረ:: በዚህ ጊዜ ነጋሪት ጎሰሙ:: መስቀሉና ማርያም በጠላታችሁ ላይ ድልን አጎናፀፏችሁ አሉ:: ሁለት ቀናትም በደስታ አሳለፉ:: ንጉሱም አማቼ አልመው የነበረውን ፈፀመልኝ ሲል ደስታውን ገለፀ:: ግን የደረሰው ወሬ ሁሉ ውሸት ነበር::

## ኢማሙ ወታደሮቻቸውን ወደ ሐበሻው ንጉሥ ዋሲል በር ድረስ መምራታቸው

ኢማሙ ከሠራዊታቸው ጋር ሌሊቱን ከዚያው ሥፍራ አሳለፉ:: በማግሥቱ ሠራዊቱን ለሁለት በመክፈል አልወዚር ኑር የተባለውን አበጋዝ በአንደኛው ክፍል ላይ ሾሙ:: ፈረሰኞችም ጨመሩለት:: ከእነሱም መሐል የኢማሙ የአጎት ልጅ የሆነው አሚር ዘህረቦኝ ሙሐመድ፣ ፈርሸሐም ዓሊ፣ የሱልጣን ዑመርዲን የአጎት ልጅ የሆነው ሸሃቡዲን ጊዳያ ጊሪ፣ የሱልጣን መሐመድ ልጅ አውረዓ ዑመረዲን፣ ገራድ አህመሻና ተከታዮቻቸው ሁለት መቶ ፈረሰኞች ይገኙበታል:: ከኋለኛው ጦር እንዳትለዩ፣ ደጅልሐን ወደ እናንተ ከወረደ ተዋጉት ሲሉ አዘዟቸው:: እኔም (ኢማሙ) ተቀዳሚው ጦር ጋር ወደ ሐበሻው ንጉሥ አመራለሁ:: ሲሉአቸው፣ ትዕዛዙን ሰምተናል፣ ታዛዦችዎም ነን አሉ:: ኢማሙ ተቀዳሚው ጣር ጋር በጠባብ መንገድ ውስጥ ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: ዓናንያ ከፊት ለፊታቸው እየተጓዘ መንገድ ያመላክታቸዋል:: አውረዓ ዑስማን እንደሆን ለአፍታ እንኳ ኢማሙን አይለያቸውም:: ጉዟቸውንም በርትተው ቀጠሉ::

## ለደጀልሐን ከወንድምየው ጋር የተላከለት የጦር ድጋፍ በኢማሙ ሠራዊት መማረኩ

ሙስሊሞች በ"ጐጃም" መንገድ ወደ ንጉሱ ባመሩበት ጊዜ አበጋዝ ደጀልሐን በጋራው በኩል እጅግ አስቸጋሪ በሆነ መንገድ እየወጣና እየወረደ ንጉሱ ወዳለበት አቅጣጫ ተጓዘ፡፡ የኢማሙ የኋላ ጦር የኋለኛው ሥፍራቸውን አልተለዩም፡፡ ለውጊያም ዝግጁ ሆኗል፡፡ ኢማሙ ከቃፊሩ ከዓናንየህ ጋር ከፊት ለፊት በመጓዝ ላይ እያሉ፣ ሐንጣሥ የተባለ የደጀልሐን ወንድም፣ ፈረሶችና ወታደሮች ይዞ ወደ ወንድሙ አበጋዝ ደጀልሐን በመጓዝ ላይ ነበር፡፡ ሙስሊሞች ከጋራው መንቀሳቀሳቸውን አላወቀም ነበር፡፡ እርሱና ቃፊሩ ዓናንየህ ተገናኙ፡፡ የዓናኒየህ ወታደሮች እንደተመለከቱ ከበቡት፡፡ ፈረሶቹንና በቅሎዎቹንም ማረኩ፡፡ አበጋዛቸው ሐንጣስ ግን ጫካ ውስጥ ዛፍ መሐል ተደበቀ፡፡ ግን ሙስሊሞች ያዙት፡፡ ዓናንየህ ተመለሰ፡፡ ኢማሙ ምርኮውን በሙሉ ለአውረዒ ዑስማን ሰጡት፡፡ ቃፊሩ ዓናንየ የአውረዒ ዑስማን ሎሌ በመሆኑ አውረዒም ምርኮውን በሙሉ ለዓናንየህ ሰጠው፡፡ አውረዒ ዑስማንም በምርኮው በጣም ተደሰተ፡፡ ከዚያም ኢማሙ ከጎጃም ምድር "አብሽሎ ዘራፍ" ከተባለ ቦታ በመስፈር እዚያው አደሩ፡፡ የኋለኛው ሠራዊት ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ኢማሙ ከሰፈሩበት ቦታ ደረሰ፡፡ ሌሊት ዓናንየህ እንዲጠራ ኢማሙ በማዘዛቸው ዓናንየህ ከኢማሙ ፊት ቀረበ፡፡ ኢማሙ ይህ ዛሬ የተጓዝንበት መንገድ ጠባብ ነውሳ? ሲሉ ዓናንያን ሲጠይቁ አሱም መልሶ፣ ነገ የምንጓዝበት ደግሞ ካሁኑ የጠበበ ነው አላቸው፡፡ ታዲያ አሁን ምን እናድርግ ብለው ሲጠይቁት፡ ሠራዊቱን በሶስት ቡድን ያከፋፍሉት፡





ከእርሱዎ ጋር አንድ ቡድን ይኖራል፡፡ ተቀዳሚው ሠራዊት አንድ ቡድን፣ የኋለኛውም አንድ ቡድን፣ ይሆንና፡ እርስዎ ተቀዳሚው ሠራዊት ጋር ይሄዳሉ፡፡ አንዱም ቡድን በመሀል ይሄዳል አላቸው፡፡ ኢማሙ ይኼንን ንግግር ሲሰሙ፡ ኢማሙ ገራድ አህሙሻን ከመሀከለኛው ጦር ቡድን እንዲጓዝ በማዘዝ፣ በሻረህ ዓሊ አልወራዒ፣ ገራድ ዓቢድና መሰሎቻቸው የሚገኙበትን አምሳ ፈረሰኞችን ጨመሩለት፡፡ ኢማሙም ከቀዳሚው ጦር ጋር ከፊት ለፊት ዓናንያ እየመራቸው አስቸጋሪውን መንገድ በርትተው ተጓዙ፡፡ መንገዱና ደኑ እጅግ አስቸጋሪ ከመሆኑም የተነሳ ከንጋት እስከ እኩለ ቀን ያለመታከት ነበር የተጓዙት፡፡ ከዚያም የ"ዋሲል" ጋራዎች ከፊት ለፊት ታዩአቸው፡፡ ኢማሙ መንገድ መሪውን ይህ የምናያቸው ጋራዎች ከዬትኛው ምድር ናቸው፣ ሲሉ ጠየቁ፡፡ ዓናንየህም የ"ዋሲል" ምድር ነው፡፡ ንጉሱ ከዚህ ጋራ ላይ እንዳለ ይነገራል አላቸው፡፡ ኢማሙም "በእርግጥ ንጉሱ ከዚያ ተቀምጦ ይኖራልን?" ሲሉ ጠየቁት፡፡ መንገድ አመላካቹም፡- አብረን እንሰማ እንደሆን ነው እንጅ የማውቀው ነገር የለም፡፡ በእርግጥ ጋልቤ ወሬ ላመጣላችሁ እችላለሁ አለ፡፡ ከአራት ፈረሰኞች ጋር በመሆን ፈረሱን ጋልቦ ሸመጠጠ፡፡ ራቅ ብለወም ሳይሄዱ፣ ከኢአማኒያኑ እረኞች ወገን የሆኑትን ሲያገኙ፣ እረኞቹ መንገድ መሪውን ከማን ወገን ናችሁ ብለው ይጠይቁታል፡፡ እኛ ከ"ደጀልሐን" ወገን ወታደሮች ነን፡፡ ወደ ንጉሱ ተልከን ነው፡፡ ደብዳቤ ይዘናል፡፡ ንጉሱ የት እንደሚገኙ ታውቃላችሁ? አሏቸው፡፡ እረኞቹም አዎ ንጉሱ በዚህ ጋራ ላይ "ሐቀህ" ከተባለችው ቦታ ይገኛሉ በማለት መለሱ፡፡ በዚህ ጊዜ እረኞቹን አሥርዋቸው ሙስሊሞች መሆናቸውንም

አልነገሯቸው::: ወደ ንጉሡ የሚወስደውን መንገድ ታመላክቱናላችሁ በማለት ይዘዋቸው ከኢማሙ ዘንድ አቀረቧቸው:: ዓናንየህ ለኢማሙ እነዚህ የያዝናቸው የኢአማኒያኑ እረኞች ናቸው:: ከጋራው ላይ ንጉሡ የሚገኝበትን ቦታ አመላክተውናል አሏቸው:: ኢማሙ፡ ወሬውን ለኢአማኒያኑ እንዳይነግሩ ግደሏቸው በማለት አዘዙ:: ዓናንየህ በበኩሉ፡- እነዚህ ሰዎች ማንነታችንን አላወቁም፣ እንደዚሁ የአገሩም ሰዎች ያወቁት የለም:: ከገደልናቸው አገሬው ሙስሊሞች መሆናችንን ያውቁና ለንጉሡ ወሬውን ያደርሳሉ:: ስለዚህ ማንነታችንንም ስለአላወቁ ብንለቃቸው የተሻለ ነው አለ:: ኢማሙም እውነትህን ነው ልቀቋቸው ሲሉ፤ አዘዙ:: ከዚያም ኢማሙና ሠራዊቱ መንገዳቸውን ቀጠሉ:: ኢማሙ ለሠራዊታቸው እንዲህ አሉአቸው፡- መንገድ ላይ ክርስቲያን ካጋጠማችሁ በቋንቋው እንጅ በሌላ አታናግሩት:: ሙስሊሞች መሆናችሁንም ለማንም አትንገሩ:: ለምታገኟቸው ሰዎች የደጀልሐን ወታደሮች ነን፣ ወደ ንጉሡ እየሄድን ነው በሉ፤ ሲሉ አዘዙ:: በትጋተኞች አካሄድ በመጓዝ ላይ ሆነው፣ ብዙም ሳይጓዙ ከርቀት ጋራው ላይ ነጭ ነገር ተመለከቱ:: ጋራው ላይ የተተከለ የንጉሡ ድንኳን ነበር:: ትልቅ ድንኳን ስለሆነ ሁለት ቀን ከሚያስኬድ መንገድ ርቀት ላይ ይታያል:: እርዝመቱ ስድሳ ክንድ፣ ቁመቱ ወደ አምሳ ክንድ ይሆናል:: የሐበሻ ንጉሶች ይኸን የመሰለ ልምድ አላቸው:: ሙስሊሞቹ ያዩት ነገር የንጉሡ ድንኳን መሆኑን ሲያውቁ ፍጥነታቸውን አለዝበው ከኋላ ያሉት እስኪደርሱባቸው ቀስ ብለው ይጓዙ ጀመር:: በአለባበስና በማጌጥም የክርስቲያኖቹ የአለባበስ ወጥ እንዲኖራቸው ሆኑ:: ኢማሙ፣ በአላህ-በአላህ (አደራ ለማጥበቅ ነው) ያለ አገው ቋንቋ





በሌላ ቋንቋ አትነጋገሩ አሉዋቸው:: መንገድ ላይ በመጓዝ ላይ እንዲሁም ክርስቲያኖች አጠገባቸው ያልፉሉ:: ኢአማኒያኑ ሁላቸውም በሥራ ተመሳርተዋል:: ሙሥሊሞቹም ክርስቲያኖች ይመስሉቸዋው ነበር::

## የኢማሙ ጦር ዋሲል መድረሱና የሐበሻው ንጉስ ጦር ከሰፈረበት ጋራ ሥር መስፈሩ

በጉዞ ላይ እያለ አንዲት የክርስቲያን ሴት ኢማሙ አበጋዝ ደጀልሐን እንደሆነ በማሰብ እየጮኸች ወደ ኢማሙ ቀረበች:: ኢማሙ በአገው ቋንቋ ሊያናግሯት ፈልገው፣ በሙሥሊሞች ቋንቋ በመናገር፣ ጓዟን መልሱላት ሲሉ ቋንቋቸውን በማወቅ፣ ወደኋላ አፈገፈገች:: ሙስሊሞች ናቸው እያለችም ባለችበት ተቀመጠች:: ወደርሷ ሳይዞሩ ጉዟቸውን ወደፊት ቀጠሉ:: ክርስቲያኖቹ በሥራ ተጠምደዋል:: ከፈሎቹ ሲያርሱ ከፈሎቹ ልብስ ያጥባሉ፣ ከፈሎቹም ዱቄት ተሸክመው ወደ ንጉሡ ዘንድ ጋራውን ሲወጡ፣ ከፈሎቹ ደግሞ ከንጉሡ ዘንድ ፍርድ ፍለጋ ጋራውን ይወጣሉ:: "ዋሲል" ከተማ እስኪደርሱ ስለሙሥሊሞች የሚያውቁት ወሬ አልነበራቸውም:: ከተማዋን በስተቀኝ በኩል ትተዋትም አለፉ:: ንጉሡ ከሰፈረበት ጋራ ስርም ደረሱ:: ከጋራው በታችም ቆመዋል:: ይህ ሁሉ ሲሆን ክርስቲያኖች የነርሱን እዚያ መኖር አሁንም አያውቁም:: ደጀልሐን ለንጉሡ በሙስሊሞች ላይ ድልን ተቀዳጀሁ በማለት በላከው ደብዳቤ መልዕክት በደስታ ተውጠዋል:: ሙስሊሞች ወደ "ፊጥጋር" ወረዱ:: መንገድ አመላካቹ ዓናንያ ከኢማሙ ዘንድ በመቅረብ ቦታው ይህ ነው፣ ደርሰናል አለ:: ኢማሙም ምን ሐሳብ አለህ? ያለህን ሐሳብ ተናገር አሉት:: እርሱም

ሠራዊትም እስኪሚላ ድረስ ከዚህ ብናርፍና ሌሊቱን ብናሳልፍ መልካም ይመስለኛል:: ሲነጋ ያሉንን መድፎች እናስናዳለን:: ከኋላ ያለው ጦርም ይደርስብናል:: ከፈረሰኞች በፊት እግረኞችን በማስቀደም ወደ ጋራው እንወጣለን:: አላህ ድልን ያጐናጽፈናል አለ:: ኢማሙም እነዚህ ክርስቲያኖች ሙስሊሞች መሆናችንን ያውቃሉ ወይስ የደጀልሐን ሰዎች መስለናቸዋል? ሲሉ ጠየቁ:: መንገድ አመላካቹም ኢአማኒያኑ ሙስሊሞች መሆናችሁን አላወቁም:: የደጀልሐን እንደሆናችሁ ነው የሚያስቡት አለ::

## ኢማሙ የሐበሻን ንጉሥ ለመዋጋት ወደ ዋሲል ተራራ መውጣትን መወሰናቸው

ኢማሙም "የማያውቁን ከሆነ አሁን ጋራውን እንዳንወጣ ምን የሚያግደን ነገር አለ? ሲሉ ጠየቁ:: መንገድ አመላካቹም፣ ከኋላችን ያሉት እግረኞችና ፈረሰኛ ወታደሮች የት አሉ? እነርሱንስ መጠበቅ የለብንምን? አለ:: ኢማሙም ሰላሳ ፈረሰኞችና ሃምሳ ያህል እግረኞች አሉን:: እግረኞችን አስቀድመን እንውጣ:: በአላህም እንመካ:: የኋለኛው ጦር አባላት ይደርሱብናል:: ወደጋራው ብንወጣ የተሻለ ነው:: ከዚህ ካደርን ግን ኢአማኒያኑ መኖራችንን አውቀው ሊዘጋጁና መንገዱን ሊዘጉብን ይችላሉ:: አንድ ሰው ከላይ ወደታች ናዳ ቢለቅብን ከጠቀስካቸው መድፎቻችን የበለጠ ጉዳት ያደርስብናል:: ስለዚህ ጋራውን መውጣት አለብን አሉ:: መንገድ አመላካቹ ኢማሙ ወደጋራው ለመዝለቅ ያላቸውን ቁርጠኝነት ሲያይ እኔ በበኩሌ ከዚህ የተለየ አስተያየት የለኝም:: የመጨረሻው ውሳኔ የእርስዎ ነው አላቸው፡ አሚር





አቡበክርና በለው ዐብዱ ቆሙና መሪያችን ሆይ! መንገድ አመላካቹ የተናገረው እውነት ነው አሉ:: መልስ አልሰጧቸውም:: ኢማሙ ለአበሰማገር ኑር "ወደ ደጀልሐን በሚያደርሰው መንገድ እንወጣለን ስትለኝ እኔም ደጀልሐን ካለበት የተሻለ በር አውቃለሁ አላልኩህም ነበርን? ያ ያልኩህ በር ይህ ነው አሉት:: አብሰማገር ኑርም አዎ እንዲህ ተባብለን ነበር፣ አሁን ግን የሚገጥመን ሞት እንኳ ቢሆን እንውጣው አለ:: ኢማሙ ከፈረሳቸው ላይ ወጥተው ለባልደረቦቻቸው ተዘጋጁ! አላህ ይባርካችሁ ብለው አበረታቷቸው:: የጦር ልብሶቻቸውን ለበሱ:: ከነርሱም መሐል አብሰማ ኑር፣ አሚር ሙጃሂድ፣ አሚር አቡበክር ቀጪን፣ አህመድ ጁዌይታ፣ አድሙሽ፣ አውረዒ አቡበክር ዓሊ ጁዌይታ፣ በለው ዓብዱ፣ ዓሊ ጣይ ኢግር፣ አውረዒ ዑስማን ኢብን ዳር ዓሊ፣ የዕቂም አዝማች ሐይቤ፣ ፈርሽሐም ሱልጣንና "ዒሳ" የተባለ የኢማሙ የሌሊት ጠባቂ ይገኙበታል:: ዒሳ መንፈሳዊ ሰው ነበር::

ኢማሙ ሡከብ በመባል የሚታወቀው ፈረሳቸው ላይ በመውጣት ሸምሱዋ የተባለው የእግረኞችን መሪ አስጠሩት:: በሁለት ቡድን ተከፍላችሁ በጋራው ጐን ወጥታችሁ በዛፎች መሀል አድርጋችሁ ሂዱ:: እኛ መንገዱን ይዘን እንጓዛለን፣ ከክርስቲያኖች አንዱ መንገድ ከዘጋብንና ከቆምን እናንተ ከበላያቸው ስለምትሆኑ ተዋጓቸው ሲሉ አዘዙ:: የሌላኛው ጦር ቡድን መሪ ፈንጅ ሰበር ይባላል ከፈረሶቻችን ፊት ቅደሙ ሲሉ አዘዟቸው:: እነርሱም ሰይፎቻቸውን ከየስገባው መዝዘው ጋሻዎቻቸውን ወድረው ጉዞ ቀጠሉ:: እነርሱ ከሄዱ በኋላ ኢማሙ የሙስሊሞች ፈረሰኛ ወደሆነው ወደ አብሰማኑር ዞረው ቅደምና ከአሚር ሙጃሂድና ከአድመሽ ጋር ሂድ አሉት:: አህመድ ጐዌይታ ከእግረኞች ጋር ሰልፉን አስተካክሎ ነበር::

ኢማሙ ከአሚር አቡበክር፣ ከፈርሽሐም ሱልጣን፣ ከዓሊ ጉዌይታ፣ ከዓሊ ባይ ኢግር፣ ከበለው ዓብዱ፡ ጋር ሆኑ። ቀሪዎቹ ፈረሰኞችና ባልደረቦቻቸው ከኋላ ተከትለዋቸው ወደጋራው ወጡ። ይህ ሁሉ ሲሆን ኢአማንያኑ የሙስሊሞችን ከዚያ መኖር አላወቁም። ኢማሙና ባልደረቦቻቸው መንገዱን እንዲጋመሱ አንድ በጫት ሱስ የተጠመደ ሙስሊም ከጋራ ሥር ደጋግሞ ያስለው ነበር። ከሥፍራው ትልቅ ቤተክርስቲያን ነበረች፡ አጋያት ኢአማንያኑ ከጋራው ላይ ሆነው ቃጠሎውን ሲመለከቱ መተራመስ ጀመሩ። ሙስሊሞችም ወደ እሳቱ ዞሩ። ኢማሙ የሆነውን ሲያዩ ይህን ያደረገው ማን ነው? አላህ በረከት ይንሳው አሉ። ባልደረቦቻቸውንም ፈረሶቻችሁን እየገረፋችሁ በፍጥነት ወደጋራው ገስግሱ በማለት አዘዙዋቸው። ኢአማኒያኑ የቤተክርስቲያኑን መቃጠል እንዳወቁ ከፊሎቹ ፈረሶቻቸውን ይጭኑ ጀመር። ከፊሎቹም ጋሻዎቻቸውን ወድረው ተዘጋጁ። በዚህ ሁኔታ እያሉ ከአብሰማኑር ጋር የቀደሙ ሙስሊም ፈረሰኞች ከመሐከላቸው ገቡ። "አላሁ አክበር" (አላህ ትልቅ ነው) እያሉ ልጓሞቻቸውንም አላሉ። በመጀመሪያ ጥቃት የሠነዘረባቸው አድሙሽ ከኢአማንያኑ አንዱን በጦር ወግቶት ወዲያውኑ ገደለው። አብሰማኑር መሀላቸው ሆኖ ከ"አላህ ሌላ አምላክ የለም፤ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው" ይል ነበር። ኢአማንያኑ ተሸነፉና ወደ ንጉሱ ድንኳን ሸሹ፤ በድንኳንዋም ተከለሉ። ከፊሎቹ ደግሞ ወደ ፊት ሸመጠጡ። ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ንጉሱን ከበውት ከድንኳኑ ወጣና፡ እርሱም አጃቢዎችም ፈረሶቻቸውን ጋለቡ። አራት መቶ ፈረሰኞች ነበሩ። ከመሐከላቸው ንጉሱ ይታያል፣ ሌሎችም ጋሻ አንጋቢው ሠራዊት ቁጥሩ በርካታ ነበር። ሙስሊሞች በበኩላቸው፡ ኢአማኒያኑ ወደ ንጉሱ ድንኳን ሲሸሹና፡ መሸሻቸውን ሲያውቁ፡ ኢማሙ





እስኪመጡ ድረስ ባሉበት ቆመው ጠበቋቸው። ኢማሙ ከቦታው ሲደርሱ የኢአማኒያኑ ሠራዊት የንጉሱን ድንኳን ከበው አዩዋቸው። አዳኝ አንበሳ የመሰሉ ሃምሳ የሙስሊም ፈረሰኞች በስፍራው ከተፍ አሉ። ከመካከላቸው አብደናስር፡ የሙሥሊሞቹ ጀግናው ፈረሰኛ የሆነው ሰብረዲን፣ ገራድ መታን፣ አብጀድና ሌሎቹም የእነርሱን መሰሎቻቸው ናቸው። ሙስሊሞችም ሆኑ ኢአማኒያኑ በያሉበት ቆመው እያሉ ከኢአማንያኑ ጦር መሐል አንድ ፈረሰኛ አፈትልኮ ወጣና የፈረሱን ልጓም ለቀቅ አድርጎ ወደ ሙስሊሞች አቅጣጫም ገሰገሰ። ሰብረዲን ሊወጋው ቀስቱን አነጣጠረ። በዚህም ጊዜ ፈረሰኛው ከአላህ ሌላ አምላክ የለም። ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው ሲል፤ ሰብረዲን ቀስቱን መለሰ። የሰማውም ቃል አስገረመው። ኢማሙም የተናገረውን ሰሙ፤ አንተ ማን ነህ? ሲሉም ጠየቁት። ጐሻ ነኝ። በአላህና በነቢዩ አምኛለሁ። ልጄ ቢሻረህ ከናንተ ጋር ነው። እኔ አባቱ ነኝ ሲል መለሰ። ኢማሙም አላሁ አክበር! ተውት፤ ሙስሊም ነው አሉ። ከዚያም አውሪዒ አቡበክር አሁን የቆምነው ለምንድን ነው? አላህ ከኛ ጋር ነው። ለኢማሙ ሲላቸው፡ ኢማም አህመድም ጥቃት ጀምሩ፤ ቀዳሚያችሁ ነኝ ሲሉም አዘዙ። ሙስሊሞችም ጥቃት ለመሰንዘር ሲያስቡ፤ ከነፍሳቸው የተቀደሰውን አምላክ ማስደሰትን አስቀደሙ።

*ይኸም አላሁ ተዓላ በቅዱስ ቁርአን እንዳጠቀሰው፦*

*"ከአማኞች መካከል ለአላህ የገቡትን ቃል ኪዳን ያረጋገጡ አሉ"*

*ሡረት አልአሕዛብ፡ አ.የ 23*

እንደ አንድ ሰው ሆነውም ጥቃት ሰነዘሩ:: እርስ በርስ እየተጋፉ ወደ ኢአማኒያኑ ተሽቀዳደሙ መሀላቸው በመግባት ስብስባቸውንም በተኑ:: ተጋደሉም:: አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አላህ በከሓድያን ሠራዊት ልቦና ላይ ፍርሃት ለቆባቸው ሽሽት ጀመሩ:: ከስፍራው ወደነበረው "ሐቀህ" ወደተባለ ከፍተኛ ጋራ እስኪጠጉ ድረስ ሙስሊሞች እየተከተሉ ወጓቸው::

## አው አቢበከር ፈቂር ሼክ አልበርኸሌ ከንጉሱ ሠራዊት ጋር የነበረው ክስተት

አቡበክር ፈቂር ሼኽ አልበርኸሌ የተባለ አንድ ሙስሊም፣ ከንጉሱ ልዩ ጠባቂዎች አንዱን አጠቃ:: የሐበሻው ንጉስ አንተ ነህ? እያለው ከኮርቻው ፈነቀለው:: እርሱም የሐበሻ ንጉስ እኔ አይደለሁም:: አትግደለኝ፣ የሐበሻው ንጉስ ያ ነው በማለት ወደ አንድ አቅጣጫ በጣቱ አመላከተ:: ልትዋሽኝ ትሞክራለህን? አለው፣ ሁለቱ እየተነጋገሩ ሳሉ፣ ከኢአማኒያኑ መካከል የተወሰኑ ሰዎች ጌታቸው በዚሁ በተጠቀሰው ሰው ተማርኮ ሲመለከቱ ሰውዬውን አጠቁት:: ከፊሎቹ ፈረሱን ያዙ:: ከፊሎቹም እየመቱት ኢአማኒያኑ ከማረኩት በኋላ ኢማሙ ከቦታው ደርሰው በእጃቸው መግባቱን ሲያዩ፣ ኢማሙ አጥቅተዋቸው ሰውዬውን አተረፉት::

ኢማሙ በግራ እጃቸው ሰይፍ መያዛቸውን የሀበሻው ንጉስ ተመለከተ:: በፈረሳቸው ምልክትና ግራኝ በመሆናቸውም ሰይፍ በግራ እጅ መያዛቸውን በማየቱ አወቃቸው:: ለባልደረቦቹም ሰይጣኑ ራሱ መጣላችሁ አላቸው:: ወታደሮቹም ድግምት





አድርገህብናል፣ ድግምት አድርገህብናል በማለት በኢማሙ ላይ ጮኹባቸው:: በቋንቋቸው ሶሮር ቆርጦ ቅጠል በጥሶ አፍዝ አደንዝዝ የሚያደርግ ነው ማለታቸው ነበር:: አባባሉ በእርግጥ ቅጥፈት ነው::

## ኢማሙና ሠራዊታቸው የሐበሻው ንጉሥና ሠራዊቱን ማሸነፋቸውና ለሽሽት መዳረጋቸው

ኢማሙ ከመሐከላቸው ገብተው ስብስባቸውን በተኑ:: አባባላቸውንም በእውነት በትር አረጋገጡላቸው:: እግሬ አውጭኝ ብለውም ወደ ጋራው ሸሹ:: ግን መውጫ መንገድ አላገኙም:: ከፈረሶቻቸው ወርደው ልጓሞቻቸውን በእጅ ይዘው ወደ ተራራው መውጫ መንገድም ይማትሩ ጀመር:: ኢማሙም ደርሰንባችኋል፣ ፈረሶቻችሁን ተውና ነፍሳችሁን አድኑ በማለት ጮኹ:: ኢአማንያኑ ጩኸታቸውንና ንግግራቸውን ሲሰሙ ደነገጡ:: ፍርሃት ውስጣቸውን አመሰው:: ፈረሶቻቸውን ትተው ተራራውን ለመውጣት ይታገሉ ጀመር፣ በጉልበታቸውም ተንበረከኩ፣ አንዱ ተራራውን ለመውጣት ዛፍ ይይዛል፣ ቅርንጫፉ ይሰበርና ተምዘግዝጎ ሲወድቅ ሙስሊሞች ይገድሉታል:: ከኢአማኒያኑ በብርቱ ትግል ተራራውን የወጡም ነበሩ:: ኢማሙ ኢአማኒያኑ ወደ ተውአቸው ፈረሶች ሰው ላኩ፣ ቁጥራቸው ሰባ ይሆናል፣ ኮርቻ እንደተጫኑ፣ ወይናማ የሱፍ ጨርቅ ግላስ እንደለበሱ አገኟቸው:: ቀሪዎቹ ሙስሊሞች በሁሉም አቅጣጫ ተበታትነው ኢአማኒያኑን መግደልና መማረኩን ተያያዙት:: ከኢማሙ ሠራዊት መሀል አብስማኑር፣

የዕቂም፣ አድሙሽ፣ አሚር ሙጃሂድ፣ ገራድ አህመዱሽ ኢብን አሚር መሕፉዝ፣ ፈርሸሃም ሲጦትና አብደላህ ኢብን ሙህረም አል መህሪ ይገኛሉ::

የሐበሻው ንጉስ ከፈረሱ ወረደ:: ወደፊትም ይገሰግስ ጀመር:: አምስት ያህል የተጫኑ ባለልጓም ፈረሶች ከንጉሡ ፊት ሆነው ይነዳሉ:: መንገዱ እጅግ አስቸጋሪ ነበር:: ኢማሙም ከባልደረቦቻው ጋር በሌላ መንገድ ተጓዙ:: ከፈረሶቻቸው ወርደው በእግር ይጓዙም ጀመር:: ሌሎችም ሙሥሊሞች ከእነሱም፡ ገራድ ዑስማን ኢ. ብን ጀውሃር፣ አውረዒ ዑስማን የኢአማኒያኑን ንጉስ መንገድ ላይ ቀድመው ጠበቁት:: ንጉሱ ሲያያቸው ዛፍ ውስጥ ተደበቀባቸው:: እነርሱ ግን አላወቁም:: በዚያ ሁኔታ ላይ እያሉ ኢማሙ ከባልደረቦቻቸው ጋር ከቦታው ደረሱ:: ንጉሱ ከታች ይመጣል ብለው በማሰብ ከላይ በኩል ቀድመውት ይጠባበቁ ነበር:: ወዲያውኑ አንድ ፈረሰኛ ወደነርሱ አቅጣጫ እየጋለበ መጣ:: አውራዒ ዑስማን አሳዶ ያዘው:: ንጉሱ ዘንድ ክብርና ሞገስ ያለው ትልቅ የጦር አበጋዝ ነበር:: ኢማሙ ሲያዩት እንዲገደል አዘዙ:: አላህ ነፍሱን በአፋጣኝ ወደ ገሃነም ወሰዳት::

## በዋሲሉ የጦርነት ውሎ የኢማሙ ሠራዊት ያገኘው ትሩፋትና የሐበሻው ንጉስ የሃብት ዝርዝር

በዕለቱ ቆመው እያሉ ፀሐይ ጠለቀች:: ደመናው አረበበ:: ዝናብም ወረደ:: የበረታ ብርድም ነበረ:: ሙስሊሞች ከባልደረቦቻቸው ጋር ለመቀላቀል ወደ ኋላ እንደተመለሱም ንጉሱ ከነበረበት ሥፍን ወጣ:: ወደ አንባ መንገድም በማቅናት ሙሉውን ሌሊት ሲጓዝ አደረ:: ሙስሊሞቹም ወደ ባልደረቦቻቸው





ደረሱ:: ከኢአማንያኑ ድንኳን ውስጥ ሆነው እሳት አቀጣጠሉ:: በደስታ ተውጠዋልም:: በርካታ የወርቅ፣ የብር፣ የፈረስና የበቅሎ፣ የሐርና ስፍር ቁጥር የሌለው የንጉሱ ልብሶች፣ የንጉሱና የባለሟለሎቹ የሐር አልባሳት፡ የሚያማምሩ የአበጋዞች ሴቶችና ወንዶች ልጆችን እንዲሁም ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ ትሩፋቶችን አካብተዋል:: የንጉሱ እልፍኝ እንደተተከለ ነው:: ከውስጡ አልጋውና መሣሪያው ይገኛል:: ኢማም አህመድ በስፍራው እንደደረሱ ድልን ያጐናፀፋቸው አላህን አመሰገኑ:: ለባልደረቦቻቸውም የንጉሱ ድንኳን ውስጥ የነበሩ ቁሳቁሶችን የት አደረሳችኋቸው? ሲሉ ጠየቁ:: ሁሉንም መሣሪያዎች ሙስሊሞች ወስደዋቸዋል:: የንጉሱ አልጋና ፍራሽ ግን እቦታቸው አሉ አሏቸው:: ኢማሙም "ድንኳኑን አልፈልጉም:: ቆራርጡና ወስዱት:: አልጋውንና ፍራሹን ግን ይዛችሁልኝ ኑ በማለት አዘዟቸው:: ወታደሮቹ ወደ ንጉሡ ድንኳን በመሄድ ድንኳኑን በብለዋዎች ቆራረጡት:: ሙስሊሞች በደስታ ተውጠው አነጉ:: ከሌሊቱ ጥቂት ጊዜ እንደተገባደደ ከገራድ አህሙሻ ጋር መሐል የነበረው ቡድን ወደዚሁ ስፍራ ደረሰ:: ተራራው ላይም ወጥተው ነበር:: ገራድ አህሙሻ "ዙል ጀናሕ" (ባለ ክንፍ) የሚመባል ፈረሱ ነበረው:: ለፈረሱ ይህን ስም የሰጡት ኢማሙ ናቸው:: በዚያን ዕለት ፈረሱ አዳለጠውና ወድቆ ሞተ:: ገራድ አህሙሻም ለፈረሱ አለቀሰለት:: ኢማሙም ከንጉሱ ልዩ ፈረሶች መካከል አንድ ጥሩ ፈረስ መርጠው ሰጡት:: የኋለኛው የጦር ቡድን በጦርነቱ ሳይሳተፍ መንገድ ላይ አድሮ በሁለተኛው ቀን ከቦታው ደረሰ:: ሙስሊሞች ሰላምታ ተለዋወጡ:: አላህ ድልን ስላጐናፀፋቸው በእጅጉም ተደሰቱ:: ኢማሙም በጦርነቱ ለተሳተፉት ሁሉ

ለእያንዳንዳቸው ፈረስ ሰጧቸው:: ሌሎቹን ግን "እናንተ ከኛ ጋር ጦርነቱን ስላልተሳተፋችሁ ምንም ነገር አልተሰጣችሁም" አሏቸው::

ይህ የዋሲል ውጊያ የዋለው በዕለተ ዓርብ "ጁሙዓ" በወርሃ ረቢዕ አል አወል 16ኛ ቀን በ938 ዓመተ ሂጅራ ነበር::

## ወደ ቤተ አምሐራ ስላደረጉት ጉዞ

ቤተ አምሐራ አዝርዕት፣ እርሻዎች፣ ወንዞችና ዝናብ የሚበዛባት የስንዴና የገብስ አገር ናት:: የክርስቲያን መጽሐፍ ዐዋቂዎቻቸው፡ ቄሶቻቸው፡ መነኮሳቶቻቸው የሚገኙባትና የግዛታቸውም መናኸሪያ ናት:: ግን ንጉሱ ሁሌም አይቀመጡባትም:: ሐበሻን የሚገዛ ማንም ንጉሥ ቤተ አምሐራ ላይ አስቀድሞ ሳይነግስ ንጉስ አይሆንም:: ነዋሪዎቹዋ በብዛት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው:: በቋንቋቸው "ደብተራ" በሚል ስያሜ ይጠሯቸዋል:: ትርጉሙ የክርስትና ሃይማኖትን ጠንቅቆ የሚያውቅና አንደበተ ፍቱሕ ማለት ነው፡ ደብተራዎች ንጉሱ ዘንድ ከፍተኛ ክብርና ተሰሚነት አላቸው:: አንዳንዶቹም የንጉሱ አለቃና አማች እስከመሆን ይደርሳሉ::

ኢማሙ ከዚህ ክስተት ከሦስት ቀናት በኋላ ወደ ቤተ አምሐራ ተጓዙ:: ላሊበላ ከሚባል ሥፍራም አደሩ:: ቦታው ውሃን የሚያጠጥር ብርቱ ብርድ ያለበት ሥፍራ ነው:: ከሙስሊሞች በብርዱ ሳቢያ ለሞት የተዳረጉም ነበሩ:: አንድ ሰው ውሃ መጠጣት ሲፈልግ የተጋገረውን የረጋ ውሃ በጦር መውጋትና መስበር ግድ ይሆንበት ነበር::

ከዚያም ከላሊበላ እንደተንቀሳቀሱ ቤተ አምሐራ ውስጥ ያለችው የንጉሱ ቤተ ክርስቲያን በሩቅ





ታየቻቸው:: መንገድ አመላካቹ ቆመና፡ ለኢማሙ ቤተክርስቲያኗ የምትታይዋት ናት፣ ደርሳችኋል አላቸው:: ኢማሙም ለመንገድ አመላካቹ፡ ወታደሮቻችን እስኪደርሱብንና እስኪያገኙን ቆመን እንጠብቃቸው ወይስ መንገድ እንቀጥል?" ሲሉት ጠየቁት:: መንገድ አመላካቾቹ ከወታደሮቹ ጋር አብረን እንገባ ዘንድ ቆመን እንጠብቃቸው:: የጦር ዝግጅትም እናድርግ አለ:: ኢማሙም የሙስሊሞች ጦር እስኪሟላ ድረስ ቆመው ጠበቁ:: መንገድ አመላካቹን የቤተ ክርስቲያናቱ ብዛት ስንት ነው? ሲሉ ጠየቁት:: መንገድ አመላካቹም በርካታ ቤተ ክርስቲያናትን ቆጠረላቸው:: ከእነዚሁም "መካነ ሥላሴ፡" አትሩስ ማርያም" የንጉሥ ዳውድ ልጅ ንጉሥ ዘርአያዕቆብ ያሳነጻት፤ "ደብረ ነጐድጓድ"፤ "ቤተሠማያት" አብያተ ክርስቲያናትን ቆጠረላቸው:: ኢማሙም ከመካነ ስላሴ ቤተክርስቲያን በስተቀር በቀሩት ቤተክርስቲያናት በእያንዳንዳቸው ቤተክርስቲያን ላይ ሙሥሊም መሪ ከሾሙባቸው በኋላ ኢማሙ ራሳቸው ወደ መካነ ስላሴ ሄዱ:: ለአትሩሳ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወዚር ኑር ኢብን ኢብራሂምን መደቡ:: በ"ደብረ ነጐድጓድ" ቤተክርስቲያን ላይ ሠዬዲ መሐመድን ከነሠራዊቱ መደቡ:: በ"ቤተ ሠማያት" ቤተ ክርስቲያን ላይ በሻራህ ቢን ጐሽን መደቡ::

## ኢማሙ መካነ ስላሴ ቤተክርስቲያን መግባታቸው፣ የቤተ ክርስቲያኗ ገጽታና ዐረቦች ስለርሷ የሰጡት አስተያየት

ኢማሙ ወደ መካነ ስላሴ ሄዱ፡ እዚያም ሲደርሱ እርሳቸውና ሠራዊታቸው የቤተክርስቲያኗን አጥር ከበው ቆሙ:: ኢማሙ እጅግ እየተገረሙ ወደ

ውስጥ ገቡና፡ ከቅርብ ረዳቶቻቸው ጋር ሲመለከቷት ዓይን የምትማርክ ሆና አገኙዋት። በወርቅና በብር ቅብ የተንቆጠቆጠች ናት። የሉል ፈርጦችም በብዛት አሉባት። በሯ ከእንጨት የተሰራ ሲሆን፡ ርዝመቱ አስር ክንድ ስፋቱ ደግሞ አራት ክንድ ይሆናል። በሩ በብርና በወርቅ ተሸቆጥቁጦአል። ከወርቁ ላይ የተለያዩ ቀለማት ያሏቸው ፈርጦች ተደርገውባቸዋል። የቤተ ክርስቲያኒቱ እርዝመት መቶ ክንድ ሲሆን፣ ከጐንዋም በኩል እንደዚሁ ነው። ከፍታው ደግሞ አንድ መቶ ሃምሳ ክንድ ይሆናል። ጣሪያውና ወለሉ የወርቅ ቅብ የተቀባ፣ በወርቅ ስዕሎች ያሸበረቀ ነው። በሥራዋም ተገረሙ። ወደ ውስጥ ያልገቡት ሙስሊሞች ኢማሙን በሩን ክፈቱልንና ገብተን እኛም እንዝናና.. በማለት ጮኹ። ከፈቱላቸው፣ እየተጋፉ ገቡ። ከመጽሐፍቱ በስተቀር እያንዳንዱ ሰው የሚወስደው ነገር የየራሱ ይሆናል ኢማሙ አሉዋቸው። ቤተክርስቲያኒቷ ውስጥ ያለውን ወርቅና ሉል መፈነቀል ጀመሩ። በአንድ ሺህ ምሳር ይገነጣጥሏት ጀመር። ከአስር ሰዓት ፀሎት በኋላ /ዐስር/ እስከ ምሽት ድረስ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የሚገኘውን ወርቅና ብር በመንቀል ሥራ ተጠምደው አመሹ። ሁሉም የሚሻቸውን ያህል ወርቅና ብር እንደያዙ ድህነት በማያስጋው ሃብት ፀጋን ተጐናፀፉ። አንድ ሦስተኛ ያህሉ የወርቅ ሃብት ግን ከቤተ ክርስቲያኗ ጋር ተቃጠለ። ኢማሙ ከቤተ ክርስቲያኗ ጐን አደሩ።

ኢማሙ አብረዋቸው ያሉ ዐረቦችን ጠሩና በሮም፣ በሕንድ ወይም በሌላ ስፍራ ይህን የመሰለ ቤት፣ ስዕላ ስዕልና የወርቅ ሃብት ይኖራልን? አሏቸው። በሮምም ይሁን በሕንድ እንዲህ ዓይነት ነገር መኖሩን አላየንም። አልሰማንምም። ምድር ላይም ይኖራል ብለን አናስብም አሏቸው። ከቤተክርስቲያኒቱ ጐን የንጉሱ መኖሪያ





የሆኑ ሦስት ቤቶች ይገኛሉ። ለተመለከታቸው እጅግ ያስደንቃሉ። ኢማሙ ከአንዱ ቤት ውስጥ ገቡና ተቀመጡ።

አንዱን ቤት ለአሚር አህሙሻ ለአሚር አቢበከር ቀጪን ሰጧቸው። ሁለቱ አሚሮች ከነሠራዊቶቻቸው ወደ ቤቱ ገቡ። ከእነሠራዊታቸውም ቻላቸው። ሦስተኛውን ቤት ኢማሙ መስጊድ አደረጉት።

## የአትሮስ ማርያም ቤተክርስያን ምርኮዎች

አልወዚር ኑር ወደ አትሮስ ማርያም ቤተክርስቲያን ደረሰ። ውስጧም እንደገባ አሰራሯ አስገረመው። ተከታዮችዋ ኢአማኒያን የነበረባትን ወርቅ አስቀድመው ስለወሰዱት፣ ምንም በውስጧ አላገኙባትም። አራት መነኩሳትን ውስጧ በማግኘቱ አልወዚር ኑር የቤተክርስቲያኗ ካዝና የት ነው? ሲል ጠየቃቸው። በማርያም ሃይማኖት እንደፀናን እንሞታለን እንጅ አናሳያችሁም በማለታቸው፣ ሙስሊሞቹ ገደሏቸው። ከሙስሊሞች መካከል ፈርሸሐም ዓሊ የተባለ ሰው ከቤተ ክርስቲያኗ በአንድ ጐን በብረት የተዘጋ ቤት በመመልከቱ ሰበረውና ወደ ውስጥ ተመለከተ። ከቤቱ ወለል ላይ እስከ ጣሪያ ድረስ የተነባበሩ ሳጥኖችን አየ። ወደ ወዚር ኑር ተመለሰና ቤቱን አሳየው። ወዜሩም ወደዚሁ ቤት መጣና በር ላይ ቆሞ፣ መቶ ያህል ወታደሮችንም አዘጋጀና፣ ግቡና ገንዘቡን ሁሉ አውጡ.. ሲልም አዘዛቸው። ሁላቸውም የሐር አልባሳትን እየተሸከሙ ደግመው ደጋግመው ቢያወጡም፣ ከቤቱ ውስጥ ያለው ሃብት ክምር ግን ገና ሳይነካ ወታደሮች ድካም ተሰምቷቸውና ተቀመጡ። ወዚሩ ምን ነው ተቀመጣችሁ? ቤቱ ውስጥ ያለው ንብረት አለቀን? በማለት ጠየቃቸው። ገና

አልነካነውም፡ እንዳለ ነው:: ቢሆንም ግን እጅግ ደክሞናል አሉት:: የሐር ጨርቆችንና አልባሳትን ብቻ ነው እስካሁን ያወጣችሁት:: ወርቅ የለበትምን? አላቸው:: ከቤቱ አንድ ጉን አለ:: እስካሁን ያወጣነው የሐር አልባሳት ያለባቸውን ሳጥኖች ነው አሉት:: አልወዚር ኑር ሌሎች ወታደሮችን የሐር አልባሳትን ተውትና ወርቁን ብቻ አውጡ ብሎ አዘዛቸው:: ወርቅና ብር እንዲሁም በርካታ የወርቅ ቁሳቁሶችን፣ እጣን ማጨሻዎችን፡ ስኒዎችን አወጡለት:: ሁሉንም እየተሸከሙ ከፊቱ ላይ ከመሩለት:: 2000 እግረኛ ወታደሮቹን ሰበሰበና ይህ የኔና የኢማሙ ድርሻ ነው:: እንደገና ግቡና የራሳችሁን ድርሻ አውጡ:: እያንዳንዱ ሰው ያወጣው የራሱ ድርሻ ይሆናል አላቸው:: ሁሉም ገቡና ወርቅ፣ ብርና ሐር እየተሸከሙ ወጡ፤ ከፊሎቹ ሦስት፣ ከፊሎቹ ደግሞ አራት ሸክም አወጡ:: በዚህ ሁኔታ ከቀትር ፀሐይ እስከትጠልቅ ከዚያም በኋላም እስኪነጋ ድረስ ቆዩ:: በዚህ ቆይታቸው ንብረቱን ከማጋዝ አልተቆጠቡም:: አሁን ጠግባችኋል፤ የምትሸከሙበት ግመሎችም የላችሁም:: በቅሎዎቻችሁም ላይ፣ በትከሻችሁም ተሸክማችኋል፤ ቤቱ ግን አሁንም እንደሞላ ነው:: እንዲሁ ይኼንን ሐር ለኢአማኒያን ትተነው አንሄድም፤ ቤቱን አቃጥሉት ሲል አዘዛቸው:: ከውስጡ ከቀረውና ከነሐር አልባሳቱ አቃጠሉት:: ቤተክርስቲያኒቱዋንም አቃጠሉዋት ወደ አመድነት ተቀየረች::





## የታቦቱና እንዲሁም ስዕላ ስዕሎች ያሉበት የወርቅ መጽሐፍና የሌሎችም ትሩፋቶች ገጽታ

ቤተክርስቲያኒቱን ካቃጠሉ በኋላ ወደ ኢማሙ ተመለሱ:: ንጉሱ ቤት እንደተቀመጡም ደረሱ:: ለኢማሙ የሐር አልባሳትና የወርቅ ድርሻውን ሰጣቸው:: ቁጥር ስፍር የሌለው የወርቅ ክምር ነበር:: ሐበሾች "ታቦት" በሚል ስም የሚጠሩት ባለ አራት እግር የወርቅ ወይፈንም ነበረበት:: መጠነ ክብደቱ ከአንድ ሺህ ወቄት ያልፋል:: የሰው፣ የአውሬና የአዕዋፋት ስዕሎች ያለበት የወርቅ መጽሐፍም ነበር:: አራት ሰዎች ሊመገቡበት ከሚችሉ የወርቅ ሳህኖቹ መካከል አራቱን ለተከበሩት ጌታ ሙጃሂድ ጀማል አዲን ሙሐመድ መርዙቅ ሰጡአቸው:: አንዱንም ለጌታ ሙሐመድ ሁንዳዱል ሰጡአቸውና፤ ቀሪውን ከሙስሊሞች ግምጃ ቤት አስገቡ::

ጌታው ሙሐመድና በሻረህ የንጉስ ወናግሰገድ እናት ወዳሳነፀቻት "ቤተሰማያት" ቤተክርስቲያን አመሩ:: ውስጧ ሲገቡ እጅግ የሚያስደንቅ ነገር ተመለከቱ:: ሀብት ግን አላገኙባትም:: አራት መነኩሴዎችን አገኙና ስለሀብቱና ስለወርቁ ጠየቁአቸው:: የንጉሱ እናት በሳጥን ተደርጋ ቤተክርስቲያኗ ውስጥ ተቀብራ ነበር:: የናንተን መምጣት ሲያውቁ የንጉሱን እናትና፡ ሀብቱንም አውጥተው ወደ አል አንባ አሸሽተውታል፤ በማለት መነኮሳቱ ነገሩዋቸው:: ከዚያም ቤተክርስቲያኗን አቃጠሏት:: መነኮሳቱም አለቀሱና ወደ ቤተክርስቲያኗ ገብተው አብረዋት ተቃጠሉ::

## በደብረ ነጐድጓድ ቤተክርስቲያን የተገኘ የወርቅና የሀብት ትሩፋቶች

በሻራ ከጌታ ሙሐመድ ጋር ወደ ነጐድጓድ ቤተ ክርስቲያን በጋራ አመሩ። ግዙፍ ነበረች። ያሳነፃት የዘርዓ ያዕቆብ ልጅ የሆነ ንጉስ አድማስ ነበር። ከቤተክርስቲያኗ ደርሰው ውስጧ ሲገቡ፣ በርካታ ሃብት አገኙ። ንጉስ አድማስ ከቤተክርስቲያኗ መሐል በሳጥን ተቀብሯል። ሀብቱዋን አወጡ። የሰው ቁመት የሚመጥን ርዝመት ያለው የወርቅ ወይፈንም፣ እናም የሰምበራ ወርቅ የሆነ፣ ሁለቱም ሰዎች ክብደቱን ለማወቅ (ሁለቱም ሰዎች) ክብደቱን ለማወቅ የማይችሉት በርካታ የተቀበረ የወርቅ የወርቅ ሃብትም አወጡ። በጊርጊይ ማስታወሻ እንዳመለከተው፣ የሰምበራ ወርቅ የተባለው፣ የሽምብራ ኮሬ ወይንም የዱሜራ ወርቅ ይሆናል። ቤተክርስቲያኗንም አቃጥሉዋትና፣ ወደ ኢማሙ ተመለሱ።

ኢማሙም ከሐር አልባሳቱና ከወርቁ ለሁለቱም ድርሻ ድርሻቸውን ከሰጠ በኋላ ቀሪውን ወደ ሙስሊሞች ግምጃ ቤት አስገቡት።

ዑብደናስር ደግሞ ወደ "ገነተ ገርጊስ" ቤተ ክርስቲያን ደረሰ። ያሳነፃት ንጉሥ እስክንድር ነበር። ንጉሣቸው -ወናግ ሠገድ- የተሸነፈ ዕለት የእርሱ ግምጃ ቤት ጠባቂዎች የነበሩ ሁለት ምርኮኞች አትግደሉን፣ የንጉሡን የወርቅ፣ የብርና የሐር ክምችት እናሳያችኋለን ብለው የተናገሩትን ኢማሙ ለዑብዲናስር ነግረውት ነበር። ክምችቱ፣ ከክብደቱ አምስት መቶ ወንዶች የሚሸከሙት ነው። ሥፍራው ዬት ነው? ብሎ ሲጠይቋቸው "ወለቀሀ" ምድር ጋራው ላይ ከምትገኝ አንዲት ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው





አሏቸው። ኢማሙ ይህን ወሬ በመስማታቸው ዑብዱናስርን ከሁለቱ ምርኮኞች ጋር አያይዘው ወደ ሥፍራው ላኩት። ግን ከቤተ ክርስቲያኗ ሲደርሱ ምንም ሀብት ባለማግኘቱ ቤተክርስቲያኒቷን አቃጠላት። ካዝናው ወዳለበት "ወለቀሀ" ምድር አመሩ። መንገድ አመላካቹ ከፊት ለፊት እየተጓዘ መንገድ ላይ ለሚያገኟቸው ክርስቲያኖች "እኛ የንጉሱ ወታደሮች ነን። ወደ ጐጃም እየሄድን ነን፣ እያሉ ያልፏቸው ነበር። ንጉሡ የተሸነፈ ዕለት ወደ ጐጃም ሄዶ ስለነበር ነው። መንገድ አመላካቹ ለዑብደናስር "ካዝናው ካለበት ስፍራ ደርሰናል፣ ከዚህ ከምታየው ጋራ ላይ ካለችው ቤተክርስቲያን ውስጥ የንጉሱና የአያት ቅድመ አያቶቹ ካዝና ይገኛል" አለው።

## የወለቃህ ምድር ትሩፋቶችና የኢማሙ ሠራዊት እንዴት ወደዚያ ስፍራ እንደደረሰ

ወደ ተራራው የሚያስወጣው መንገድ የንጉሱ ባሪያዎች በሆኑ ሐምሳ ወንዶች ይጠበቃል። ጠባቂዎቹ አለቃ አሳቸው። እንዳጋጣሚ የዚያን ቀን ከጋራው ሥር ካለች አንዲት መንደር የአለቃቸው እናት ሞተው ሁሉም ለቀብር ሄደዋል። ከሙስሊሞች ጋር መንገድ ላይ ተሳልፈዋል። በቤተክርስቲያኗ አራት መነኩሴዎችና ሦስት ሥልቦች ብቻ ቀርተዋል። ሙስሊሞች ከጋራው ሥር ሲደርሱ ዑብደናስር ጋሻውንና ሰይፉን ያዘ። ባልደረቦቹም ሰይፎቻቸውን መዘዙ። ጋሻዎቻቸውንም ወደሩ። ወደ ተራራውም ወጡ። ከቤተ ክርስቲያኗም ደረሱ። በራፏ ላይም ቆሙ። መነኩሴዎችና ስልቦችም ቆመዋል። ሙስሊሞች መነኩሴዎቹን ገደሉዋቸው። ስልቦቹ ግን አምስት መቶ

ሽክም የሚሆን በወርቅ የተንቆጠቆጡ የሐር አልባሳትና ወርቅን አወጡ:: ቤተክርስቲያኗ ውስጥ ከነበሩ አስገራሚ ነገሮች መካከል በርካታ የንጉሱ ዘውዶችና የቀደምት ንጉሶች ዘውዶች ነው:: ንጉሶች የሚደፏቸው አክሊሎችም ነበሩ:: ከአክሊሎችም ፊት ለፊት በፈርጥ የተጌጠ የወርቅ ሰሌዳ፡ የወርቅ ዝናሮች፡ የወርቅ አንባሮችና የወርቅ ጩቤዎች ይገኛሉ:: እያንዳንዱ ጩቤ ስለቱም ስገባውም ወርቅ ነው፡ መርፌ ቁልፍና የወርቅ እግሮቻቸው በፈርጥ የተጌጡ የወርቅ ወይፈኖችም ነበሩ:: የወይፈኖቹ አንገት ርዝመት ሁለት ክንድ ይሆናል:: የወርቅ ልጓሞች፣ የወርቅ ሳህኖችና ስኒዎችም ይገኙባት ነበር:: ዐብደናስር የኢማሙ ካዝና ጠባቂ በመሆኑ ይህን ሁሉ ሰበሰበ:: መዝገብ ውስጥም አስፈረው:: ለባልደረቦቹ ለያይቶ አሸከማቸው:: ቁጥራቸው 3000 ይደርስ ነበር:: እያንዳንዱ ቡድን መሪዎች አሉዋቸው:: የእያንዳንዱ ቡድን መሪዎችን እየጠራ ንብረቱን አከፋፈላቸው:: ከፊሎቹ ሁለት ሺህ ወቄት፣ ከፊሎቹም 1500 ወቄት፣ ከፊሎቹም 1000 ወቄት፣ ከፊሎች ደግሞ 500 ወቄት ተሸከሙ:: ከዚያም ኢማሙ ዘንድ ደረሱ:: የደረሱትም ኢማሙ በቀድሞው ቤታቸው እንዳሉ ነበር:: ኢማሙና ባልደረቦቻቸው በምርኮው ብዛት እጅግ ተገረሙ:: ከዚህ ቀደም አይተውት የማያውቁት ነገር ሆነባቸው:: ኢማሙ የሐር አልባሳቱን ከሦስት ከፋፈሉ:: አንዱን እጣ ራሳቸው ያዙና ከሙስሊሞች ግምጃ ቤት አስገቡት:: ሌሎችን ሁለት እጣዎች ደግሞ ለዐብደናስርና ለባልደረቦቹ ሰጧቸው::

እጅግ ድንቅና ውብ የሆኑ ቁሳቁሶችንና ጌጦችን ኢማሙ ለአገልግሎት ያዟቸው:: ቁጥር ስፍር የሌለውን "ሱንቡረህ" የተባለ ከብዛቱ የማይመዘነውን ወርቅ ደግሞ ለወታደሮቹ አከፋፈሉ:: በቤተ አምሐራም ቆዩ::





# የአባ ወይንና የወእለህ ትሩፋቶች

ኢማሙ "ቤተ አምሐራ" ሳሉ፡ ከአባይ በላይ "አባወይን" በምትባል ከተማ ውስጥ በምትገኝ "ወእለህ" በምትባል ቀዬ ውስጥ ተረጋግተው ስለሚኖሩት ክርስቲያኖች ይሰማሉ:: መንደሪቷ (ከተማዋ) በአባወይንና በቤተ አምሐራ መካከል እንደምትገኝና፡ የንጉሱ አያት ቅድመ አያቶች የቀደምት ንጉሳን አብያተ ክርስቲያናት እንደሚገኙባት ተነገራቸው:: ኢማሙ ይህን እንደሰሙ አውረዒ አቦኝን ወደዚያው ላኩት:: ነጭ አርማም አስያዙት:: ረዳቶችንም ሰጡት:: ከነርሱም መሐል ዘህረቦኝ ሙሐመድ፣ አሚር አቡበክር ቀጪን፣ አሚር ሙጃሂድ፣ አብስማኑር፣ አህመድ ጉዌይታ፣ ሼክ ዳዋና አውረዒ አህመድዲን ይገኙበታል:: መንገድ መሪው አዝማች ሐይብ ነበር:: በድምሩ 200 ፈረሰኞችና 1500 እግረኞች ነበሩ:: ኢማሙ ለአውረዒ አቦኝ አርማውን ሰጥተውት ስለቤተክርስቲያኖቹ የነገሯቸውንም ሰው አብሮ እንዲጓዝ አደረጉ:: እስከ "ወእላህ" ምድር ተጉዘውም ደረሱ:: አራት ቤተክርስቲያኖችንም አገኙ:: ሁለቱ የወርቅ ቅብ ሲሆኑ የተቀሩት ሁለቱ የወርቅ ቅብ ባይሆኑም በሥራቸው ብዙ የተደከመባቸውና በእጅጉ የተጌጡ ናቸው:: የወርቅ ቅብ ወደሆኑት ቤተክርስቲያኖች ገብተው ወርቁንም በምሳር ይነቅሉት ጀመር:: ሁሉንም ወርቅ ከያዙ በኋላ ከእንጨት ወደተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት አመሩ:: ከውስጣቸው ባለ አራት እግር የወርቅ ወይፈኖችን አገኙ:: መሪዎቹ እያንዳንዳቸው አንዳንድ የወርቅ ወይፈን ይዘው ወጡ:: የእያንዳንዱ ወይፈን ክብደት ሁለት ሺህ ወቄት ነው:: ሌላውም ወይፈን ክብደቱ

1500 ወቄትና፣ ሌላም ወይፈን 1000 ወቄት የሚመዝን ነው:: ከአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ ከወርቅ በስተቀር ሐር አላገኙም:: ያገኙትን በሙሉ ከያዙ በኋላ ቤተክርስቲያኒቱን አቃጠሉ::

## ከሐበሾች አንዱ ንጉሡ ያለበት ቦታን ለመጠቆም ለኢማሙ ሃሣብ ያቀርባል

ኢማሙ አውረዒ አቦኝን ልከውት ለስድስት ቀናት ከተጓዘ በኋላ፣ አንድ ክርስቲያን የሆነ ሰው ወዚር ኑር ዘንድ መጥቶ እንዲህ አለው:- ንጉሡ የሚገኝበትን ቦታ አውቃለሁ:: ጫካ ውስጥ ተደብቆ ይገኛል:: 15 ፈረሰኞች አብረውት አሉና ቦታውን ካመላከትኩዋችሁ ምን ትሰጡኛላችሁ? አለው:: ወዚርም የፈለግከውን ያህል ገንዘብ እንሰጥሃለን:: ግብርም እናነሣልሃለን፣ አለው:: ንጉሡ ያለበትን እኔ አመላክታችኋለሁ አለ:: ወዚር ኑርም ለገራድ አህሙሽ ክርስቲያኑ ያለውን ነግሮት ሁለቱም ኢማሙ ዘንድ ቀረቡና የክርስቲያኑን ሐሳብ ነገሩዋቸውና፣ እኔ ወይንም ገራድ አሕሙሻ እንሂድ ሲል፣ ኢማሙ ገራድ ኢሕሙሽ ይሂድ ብለው፣ አሕሙሻም ሄደ:: አውረዒ ዑስማንን ከነሠራዊቱ፣ ፈርሽሃም ዓሊ፣ ዓሊ ዋራዲ፣ ፈርሽሃም ዑስማን፣ ፈርሽሃም ሰጥወትን፣ ሽምሱዋ የበሕሩ ተቀዳሚ፣ የኢማሙን የወንድም ልጅ ዓባስን ሰጡት:: መንገድ መሪው ፊት ፊት እየሄደ ተጓዙና ንጉሱ ይገኝበታል ከተባለው ቦታ ሲደርሱ አጡት:: ንጉሱ የት አለ? ሲሉ መንገድ መሪውን ጠየቁት:: ከዚህ ነበር:: እሳት ያነዱበት የነበረው ቦታ ይኸውና አለ:: በዚህ ጊዜ ገራድ አህመሻ ፈረሰኞችን በየቦታው አሰራጨ:: ሁለት ገበሬዎች ተማርከው ከፊቱ ቀረቡና፣ ስለ ንጉሱ ጠየቋቸው:: እዚህ ነበር:: ሌሊት ያቀጣጠላችሁትን እሳት ተመልክቶ ሥፍራውን ለቀቀ:: "በሽሎ" የተባለውን ወንዝ ተሻግሮም "ቤጌምድር" ወደ ተባለው ቦታ ሄደ:: አሉት:: ገራድ አህመሻ ለሁለት ቀናት ያህል ተከታተለውና "በሽሎ" ወንዝ ደረሰ:: ግን አላገኙትም:: ካሉበት ቆሙና ንጉሱን ከእንግዲህ አንደርስበትም:: ወደ ኢማሙ መመለስ አለብን በማለት ወሰኑ::

## ገራድ አህሙሽ ወደ አንባ ለመዝለቅ ባልደረቦቹን ማማከሩ

ተመለሱና ለሁለት ቀናት እንደተጓዙ ከአንድ ቦታ ላይ አረፉ:: አህሙሽ ወታደሮችን ሰበሰበና "አንባ የምትባለው ከተማ ካለንበት ቦታ እጅግ ቅርብ ናት:: እንክበባትና እናቅናት (እንቆጣጠራት)፣ አለ:: ሸሪፍ ኑርና ሌሎቹም ሰዎች፣ "አንባ" በገደላ ገደሎችና ሸለቆዎች፣ በማይዘለቅ ምሽግ የተከበበች በመሆንዋ ያለመሰላልም አትወጣም" አሉት:: ሸሪፍ ኑር "ኢማሙ ወደ አንባ እንድንሄድ አላዘዙንም፣ እና ወደርሳቸው እንመለስ ሲል፣" ገራድ አህሙሽ "የጦሩ አዛዥ /አሚር/ እኔ ነኝ ወይስ አንተ? አለው:: አንተ ነህ ሲል ሸሪፍ ኑር መለሰለት:: "አሚሩ እኔ ከሆንኩ ታዘዙኝ:: በዚህ ላይ ምንም አስተያየት እንድትሰጡ አይፈቀድላችሁም አላቸው::

## አንባና ገጽታዋ

አስቸጋሪውን መንገድ አልፈው፣ ጋራ እየወጡና ሸለቆ እያቆራረጡ አንባ ሲደርሱ በመሰላል ካልሆነ የማይወጣ ቀጥ ያለ ተራራ አዩ:: ከተራራው ላይ የነገስታት ልጆች የሚኖሩባቸው ከሺህ የሚበልጡ

ቤቶች አዩ:: በቦታው ላይ ወንዞች፡ ካዝናዎችና የነገሥታት ልጆች ይገኛሉ::

## አንባ ውስጥ የነገሥታት ልጆች የአስተዳደጋቸው ገጽታ

እያንዳንዱ ንጉስ ወንድ ልጅ በተወለደለት ቁጥር አንባ ወደተባለው ወደዚሁ ጋራ ያወጣቸዋል:: ይህን የሚያደርጉት በአስተዳደሩ ውስጥ የእርስ በርስ ውዝግብና ሽኩቻ እንዳይነሳ ለመከላከል ነው:: ንጉሱ ሲሞት አንባ ጋራ ላይ ካሉት ወንዶች ልጆች አንዱን ያወርዱትና ያነግሡታል:: ይህ የቆየ የአያት ቅድመ አያቶቻቸው ባሕል ነው:: አንባ ውስጥ ሁለት ሺ ሦስት መቶ ያህል የነገሥታት ወንዶችና ሴቶች ልጆች ይኖሩ ነበር:: ንጉሱ የሚያስፈልጋቸውን ያህል ልብስና ጉርስ ይሰጣቸዋል::

## አህሙሻ አንባ መድረሱና በሮቿን መክበቡ

አህሙሽህ ወደ አንባ እንደደረሰ መግቢያዎችዋ ላይ ከበባ አደረገ:: በሮቹም ላይ ሌሊት ተጋድለዋል፡ ሙሥሊሞቹ ሌሊት በሮቹ ላይ ሲዞሩ አደሩ:: ወደ ጋራው ለመውጣትም መሰላሎችን አዘጋጁ:: ኢአማኒያኑም በሮቹ ላይ ሆነው እሳት እያቀጣጠሉ በየመንገዱ ጥበቃቸውን አጠናክረዋል:: ጠዋፍ አብርተው በመዘዋወር ሙስሊሞችን ይጠብቃሉ:: ሙስሊሞች ወደ ጋራው ለመውጣት ሲሉ መሰላሉን አንዴ በጋራው ጐን ያደርጉታል:: ለመውጣትም ይዘጋጃሉ:: ግን ኢአማኒያኑ በድርጊታቸው ይነቁና ናዳ ይለቁባቸዋል:: ሙስሊሞችም ወደኋላቸው ይመለሳሉ:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ በርካታ ሌሊቶች





አለፉ:: አንድ ሌሊት ከፈሎቹ ሙስሊሞች ወደጋራው ለመውጣት ተዘጋጁ:: ሰባት ነበሩ:: እነርሱም አብደላህ ኢብን ናስርአዲን አልሐመዊ፡ ነስር ኢብን ዴለን፡ ሸሪፍ ኑር፣ አዲሽ -ተኸለየሱስን የገደለ-፡ ሣዒድ -የገራድ አሕሙሻ ሎሌ፡ አነሥ - ከኢማሙ ሎሌዎች- እና ዐብደላ አሶማሊ ነበሩ::

በሌሊቱ ወደ በሩ አመሩና ዛሬ በአላህ ፈቃድ የግድ መውጣት አለብን በማለት ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ:: ተሠውረው ጋራውን መውጣት ጀመሩ፡ ማንም ድምፁን እንዳያሰማ ተመካክረዋል:: ከጋራው ዋናው ሥፍራ ከበታች በኩል ቆሙ:: በሩ ላይ የተቀመጠውን ጠባቂ አዩት:: ጋራው ሶስት ወደ ላይ የሚወጡበት በሮች አሉት:: በእያንዳንዱም በር ላይ ጠባቂዎች አሉ:: ጠባቂዎቹን እሳት አቀጣጥለው ሲያዩአቸው፤ በመሀላቸው በምሥጢር በመነጋገር እንዲህ አሉ፡- ይህ ጠባቂ ተቀምጦአልና እስኪያሸልብ እንቀመጥ፤ ያነደደውም እሳት እንደተቀጣጠለ ነው:: እሳቱ እስኪጠፋ እንታገሣለን፤ እሳቱ ሲጠፋ መተኛቱንም እናውቃለን ጠባቂው እስኪተኛም ታግሰው ቆዩ:: እሳቱ ጠፋ:: በዚህ ጊዜ ናስር ኢብን ደለን ቀድሞ መውጣት ጀመረ:: ሌሎች ባልደረቦቹም ተከተሉት:: እየዳኹና እየተንፏቀቁ ተራራውን በመውጣት ከበሩ አጠገብም ደረሱ:: ናስሩዲን ቀድሞአቸው ወጥቶ ነበር::ጩቤውን አውጥቶ ጠባቂውን ሊያርደው ፈለገ:: ሸሪፍ ኑር ተዳክሞ ስለነበር ሁለት ሦስት ጊዜ ስላሳለው ጠባቂው ከእንቅልፉ ነቃ:: "ሌባ ሌባ" እያሉም ይጯጯሁ ጀመር:: ድንጋይና ቋጥኝም ለቀቁባቸው:: ሙስሊሞች አንዱ ከአንዱ ላይ እየወደቀና እየተንከባለሉ ወረዱ:: ሸሪፍ ኑር ግን አብሯቸው ሊወርድ አልቻለም:: ከአንድ ቋጥኝ ሥር እስኪነጋጋ ድረስ ከቆየ በኋላ ብቻውን ወረዶ ከባልደረቦቹ ጋር ተገናኝቶ ሰላምታ ተለዋወጡ::

አውረዲ ዑስማን ወደ አንዱ በር ሄደ። ከሠራዊቱ ጋር በአንደኛው የአንባ በር፡ ገራድ አህሙሻ ደግሞ በሌላኛው በር ነበሩ። አውረዲ ዑስማንሙሉውን ሌሊት በብርቱ ሲዋጋቸው አደረ። በመጨረሻ ኢአማኒያኑ ተሸንፉና ከሙስሊሞች የተወሰኑት ወደጋራው ይወጡ ጀመር። ከእነሱም፦ ፈንጀሰበር፣ ባልሱር ኢብራሂም፣ ገራድ አምየስ፣ በርበሪ፡ ዓሊ ወራዲ አሸሂድ፡ ዓሊ ባይ አሂር፡ የተባሉ የታወቁ ጀግኖች ከመሐከላቸው ነበሩ። ጋራውን ወጥተው ጨረሱና ከመጀመሪያው በር ደርሰውም ሰበሩት። ወደ ሁለተኛው በርም አመሩ፤ በብረት የተቆለፈ ነበር። ለመስበር ይቀጠቅጡት ጀመር። ከበሩ በላይ ካለው መቆጣጠሪያ (ማማ) ላይ ኢአማኒያኑ የተድቦለቦለ ድንጋይ በወፈንጭት የድንጋይ ናዳ መልቀቃቸውን ተያያዙት። ሙስሊሞችም በብዙ ውጣ ውረድ ወደታች ወረዱ።

## ገራድ አህሙሽህ ለኢማሙ የይድረሱልኝ መልዕክት መላኩና ኢማሙም ከርሱ ዘንድ መድረሳቸው

ገራድ አህሙሻ "አንባ"ን ከብቤያታለሁ፡ እርስዎ ይድረሱልኝ የሚል መልዕክት ለኢማሙ ላከ። ኢማሙ በቀድሞው ሥፍራቸው እንዳሉ መልዕክተኛው ኢማሙ ዘንድ ይደርሳል። ኢማሙ የአህሙሻን ደብዳቤ ሲያዩ "አንባ" እንድትገበ ማን አዘዛችሁ? ሲሉ መልዕክተኛውን ጠየቁት። መልዕክተኛው፡ ንጉሱን ፍለጋ ስንሄድ ከነበረበት ቦታ አጣነው። ለሁለት ቀናት ብንከተለውም ልናገኘው አልቻልንም። ተመለሰን ለሁለት ቀናት ያህል እንደተጓዝን ገራድ አህሙሻ ለሠራዊቱ "አንባ" መግባቴ ነው አለ። ሙስሊሞች





ወደዚያ መግባትን አልፈለጉም ነበር። ታዲያ ገራድ አህሙሽ ሠራዊቱን መሪያችሁ አይደለሁምን? ሲል ጠየቃቸው። አዎን የሚል መልስ እንደሰጡት እንግዲያውስ ታዘዙኝ አላቸው። ወደ "አንባ" ይዟቸው ገባና አንድ ሌሊት እንዳሳለፈ ወደ እርስዎ ላከኝ አላቸው። ኢማሙም ፈረስ የሚያስገባ መንገድ ይኖራት ይሆን፣ ወይስ የላትም? ሲሉ ጠየቁት። መልዕክተኛው ለፈረስም ሆነ ለእግረኛ መንገድ የላትም። በመሰላል ካልሆነ በቀር አይወጡም አላቸው። ኢማሙ ለመልዕክተኛው እንዲህ አሉት፦ አንተ ቅደመኝ፡ እኔም እከተልሃለሁ፡ ለጋራድ አሕሙሻም፤ እኔ እስኪደርስባቸው፣ ያላችሁበትን ሥፍራ ለቃችሁ ስፊ መሬት ላይ እንድትሠፍሩ ብለህ ንገረው አሉት። መልዕክተኛው ከገራድ አህሙሻ ዘንድ እስኪደርስ በፍጥነት በመጓዝ ኢማሙ የሰጡትን ትዕዛዝ ነገረው።

ኢማሙ መልዕክተኛውን ከላኩ በኋላ አውረዲ አቦኘን እየተጠባበቁ ለሁለት ቀናት ቆዩ። በሦስተኛው ቀን አውረዲ አቦኝ ከአሁን ቀደም የተጠቀሰውን የወርቅ ምርኮ ይዞ ደረሰ። ኢማሙ ድርሻቸውን ወሰዱ። ለሌሎችም ድርሻቸውን አከፋፈሉ። የኢማም አሕሙሽ መልዕክተኛ በሄደ በአራተኛው ቀን ቤተ አምሐራን ለቀው ገራድ አህሙሻ ወዳለበት ወደ አንባ ጉዞ አደረጉ። ለሦስት ቀናት ተጉዘው አንባ ሊደርሱ የአንድ ቀን መንገድ ሲቀራቸው ካሉበት ቦታ ሰፈሩ።

## የነገሥታት ልጆች የሆኑት የአንባ ነዋሪዎች ከሐበሻው ንጉስ እገዛ መጠየቃቸውና እርሱም ኃይል ስለመላኩ

የነገሥታቱ ልጆች የሆኑት የአንባ ነዋሪዎች፣ በሙስሊሞች ሲከበቡና መፈናፈኛ ሲያሳጧቸው፡ ወደ ንጉሱ ሙስሊሞች ከተማችንን ከበዋታል። መፈናፈኛም አሳጥተውናል ሀገሪቱን ከማስረከባችን በፊት ጦር ላክልን። ሠራዊትህ ከዘገየብን ሳንወድ በግድ ከተማይቷን እናስረክባቸዋለን ሲሉ መልዕክት ላኩበት። ንጉሱ መልዕክቱን እንደሰማ ሦስት የጦር አበጋዞችን ከነሠራዊቶቻቸው ላካቸው። ከእነርሱም አበጋዝ ሠርጠ ቢትወደድ የዓምዱዋ ልጅ፣ አበጋዝ ዮውኤል፣ እና አበጋዝ ይሥሐት ይገኙባቸዋል።

## በሐበሻው ንጉስ ወታደሮችና በኢማሙ ወታደሮች መካከል አንባ ላይ ስለተደረገው ጦርነት

ሙስሊሞች በሩን በሰበሩበትና አውረዒ ዑስማን ከኢአማኒያኑ ጋር ውጊያ በገጠመበት ሌሊት የንጉሱ አበጋዞች ሠራዊታቸውን ይዘው ከሥፍራው ደረሱ። እስከኒነጋ ድረስ ጠብቀዋቸው ከዚያም በ"ዓንቁት" መንገድ በኩል ሙሥሊሞቹ በውጊያ በመጠመዳቸው የንጉሱን ሠራዊት መምጣት አላወቁም ነበር። ያወቁትም የኢአማኒያኑ ጦር አውረዒ ዑስማን ባለበት በር በኩል ሲደርስ ነበር። ፈረሶቻቸውን ሁሉ ከገራድ አህሙሻ ዘንድ በመተዋቸው አውረዒ ዑስማን ለርሱም ሆነ ለሠራዊቱ ፈረሶች አልነበሩትም። አውረዒ ዑስማን ውጊያ እንደተከፈተባቸው ሲያውቅ ባልደረቦቹን





በማነቃቃት ለውጊያ ተዘጋጁና፡ እሱና ባልደረቦቹም ሰይፋቸውንና ጋሻቸውን ያዙ። የውጊያው ሥፍራ ለእግረኛም ለፈረሰኛም የማያመች ነበር። ኢአማኒያኑ ፈረሶቻቸውን ትተዉ፣ ጦራቸውንና ጋሻቸውን በማንገብ ብርቱ ውጊያ አደረጉ። ኢአማንያኑ "ሲመት" በመባል ከሚታወቁ ትግሬዎችና ከ"ዐጋሜዎች"ም በርካታ ቀስተኞች ነበሯቸው። ሙስሊሞቹም ጥቃታቸውን ሠነዘሩ። ተቀዳሚዎቻቸው ታዋቂዎቹ የሙስሊሞች ፈረሰኛ ዓሊ ዋረዲና የባሕር ወታደር ፈንጅ ሰበር በጣምራ ጥቃት ሰነዘሩ። ብርቱው ተዋጊ አሚር ጋፋት፣ በርበሪና፣ ዓሊ ባይ ኢጊርም ይገኙ ነበር። ከወታደሮች መሐከል ሰንበታይ የተባለው ወታደር ምስጋና ይግባው። ከነርሱ ጋር በጥቃቱ ተሳተፈ፣ አራት ኢአማንያን ወታደሮችንም ገደለ። አውረዒ ዑስማን ፊት ብርቱ ውጊያ በማድረጋቸው ከሓድያኑ ሸሸት ጀመሩ። ሙስሊሞች ተከተሏቸው። ከዚያም ዳግም ተሰባስበው ወደ ሙስሊሞች ተመለሱና ሲመጡ በነበሩበት ቦታ አገኙዋቸው፣ ውጊያ ተደረገና፣ ሆኖም ዳግም ሽንፈት ቀምሰው ሸሸት ያዙ። ግን ባሉበት ፀኑ። ለሦስተኛ ጊዜም ውጊያም ተካሄደ። ኢአማኒያኑ የመጀመሪያው ዓይነት ሽንፈት ተከናንበው ሸሹ። ለአራተኛ ጊዜ ብርቱ የጨበጣ ውጊያ ተደረገ፣ ዓሊ አልወራዒ ከመሐከላቸው ዘሎ ሲገባ አንድ የትግራይ ሰው ደረቱን በጦር ወጋው። በከዕባው ጌታ እምላለሁ፣ ጀንነትን አገኘሁ አለ። ለባልደረቦቹም የኔ ሞት አያሳስባችሁ፣ በርትታችሁ ተዋጓቸው አላቸው። አሚር ጋፋት ዓሊ አልወራዲን የገደለውን አረማዊ ወታደር በጦር ወግቶ ገደለው።

## የኢማም አህመድ ጦር መሸነፉ፡ መሪው ገራድ አህሙሻ መማረኩና አውረዒ ዑስማንና ሌሎች የጦር አዛገሮች ስለመገደላቸው

የኢአማኒያኑ ጦር እየተበራከተ ሄደ። መርዛማ በሆነ ቀስትም ሙስሊሞችን በጋራ ያጠቁ ጀመር። ሙስሊሞች ጥቃት ሲበረታባቸው ሽሽት ጀመሩ። ፈንጂ ሰበር የተባለው ሰው ሲቀር ሁሉም ወደኋላ አፈገፈጉ። እርሱ ግን እንደ ግመል እያጉራ ውጊያውን ቀጠለ። ምስጋና ይግባውና ባልደረቦቹ ሁሉ ሲሸሹ እርሱ ብቻውን ባለበት ፀና። ሰይፉን በእጁ ያዘና ብርቱ ፍልሚያ አደረገ። የኢአማኒያኑ ሰይፎች በጋሻው ላይ ተረባርበውት እጀታው ብቻ ስትቀረው፣ በዚያችው እጀታ የአንዱን ኢአማኒያን ፊት ሲመታው ኢአማኒያኑ ተደናገረ። ፈንጅ ሰበር በዚሁ ሰው ላይ ዘሎ በሠይፍ መታውና ለሁለት ከፈለው። ከዚያም የሸሹት ባልደረቦቹን ተከትሎ በሰላም ከነርሱ ጋር ተቀላቀለና አንድ ላይ ሽሽታቸውን ቀጠሉ። በዚህ ውጊያ አውረዒ ዑስማን መስዋእት ሆነ። ዓሊ ወራዲም ባለበት ተገደለ። ቀሪዎቹ ሙስሊሞች ግን ወደኋላ አፈገፈጉ። ከጋራውም ወረዱና በየሸለቆዎችና በየዛፎች ውስጥም ተሰወሩ።

## የ938 ዓመተ ሂጅራ የወርሃ ረቢዕ አልአኼር 14 ዕለተ ረቡዕ ውሎ

ገራድ አህሙሽና ባልደረቦቹ የአውረዒ ዑስማን ባልደረቦችን መሸነፍ ሲያውቁ፡ ያለ ውጊያ ተሸነፉ። እየተንከባለሉም እስከ ጋራው ሥር ወረዱ። የዚያን





ዕለት የባሕሩ ጦር ፊታውራሪ ሽምሱዋ፡ ሾተላይና ወሰን ጃን ምስጋና ይግባቸውና ሙስሊሞች ሲሸሹ የኋለኛውን ጦር ይዘው ከኋላ በኩል ኢአማኒያኑን አጠቋቸው። በሽሽት የወደቁ ሙስሊሞችንም በማዳን ባልደረቦቻቸው ትንፋሽ እስኪያገኙና እስኪረጋጉ ድረስ በብርቱ ተፋለሙ። ከዚህ በኋላ የቤተ አምሐራን መንገድ ያዙ። በውጊያው ገራድ አህሙሽ ተማረከ። ገራድ መታን ሶማሊ፣ አብደላህ ኢብን ናስረዲን አሉሐመዊ፣ ሳሊሕ፣ ዑመር፣ ሰዒድና ሱማሌው ዓሊ ደግላይ ተገደሉ።

ኢአማኒያኑ አሥራ አምስት የሙስሊሞችን ፈረሶች ማረኩ። አልጃዛኒ እንደዘገበው ይህ ሽንፈት የተከሰተው በሂጅሪያ የዘመን ቀመር በ938 ዓመት በወርሃ ረቢዕ አልአኺር 14ኛው ቀን በዕለተ ረቡዕ ነበር።

ኢአማኒያኑ ገራድ አህሙሻን እንደተማረከ ከሐበሻው ንጉሥ ፊት አቆሙት። የተገደሉትን ሙስሊሞችም አንገቶቻቸውን ቆርጠው ከፈረሶቹ ጋር ከንጉሱ ፊት አቀረቧቸው። ንጉሱና ተከታዮቹ እጅግ ተደሰቱ። ንጉሱ ገራድ አህሙሻን ለተወሰኑ ቀናት ካሰረው በኋላ ገደለው።

ሽሽተው ያመለጡት የገራድ አህሙሽህ ባልደረቦች ኢማሙ ወደ "አንባ" ጉዞ በጀመሩበት ቀን ደረሱ። የደረሰባቸውን ሁሉ ነገሯቸው። በአማቻቸው በመታን ሞት እጅግ አዘኑ፤ ደጋግመውም አለቀሱ። ከዚያም የሸሹትን ሁሉ ሰበሰበና አስቀመጧቸው። በውጊያው ላይ የተሳተፉ ሁሉ ይምጡ ሲሉም አዘዙ። ሲሰበሰቡ አውረዒ ዑስማንና ባልደረቦቹ ጠንክረው ተዋግተው እንደነበር አውቀናል፡

ተዋግተውም አሚራቸው (መሪያቸው) ተገድሎአል:: ዓሊ ዋራዲና ሌሎችም እንዲሁ ተዋግተዋል:: እናንተ የገራድ አሕሙሻ ባልደረቦች፡ ሳትዋጉ መሸነፋችሁ ምን ይባላል፣ ፈረሶችና መሣሪያዎችም እያሉዋችሁ አሚራችኑ (መሪያችሁን) መተዋችሁስ ምን ይባላል? ሲሉአቸው፡ ዝም ብለው አንገታቸውን ደፉ:: ምንም መልስ አልሰጡም:: ኢማሙ መሪዎቻቸው እንዲታሰሩ አዘዙ:: ታሠሩ:: እነሱም:- ፈርሽሐም ዓሊ ከማቅናት (ድል) በኋላ የ"ዓንቁት" አስተዳደሪ፡ እና ገራድ አሕመዱሽ እና አንድ መቶ የማይሆኑ ፈረሰኞች ናቸው:: የሃይማኖት አባቶችና የጦር አበጋዞች በአማላጅነት ስለለመኗቸው እንጅ ሊገድሏቸው ነበር:: ከእስር እንዲፈቱ በማድረግ፡ እንዲሁ አልተዋችሁም፡ "አንባ" ድረስ እወስዳችሁና ትዋጋላችሁ፡ አሏቸው:: አዛዦቹም ለኢማሙ እንዲህ አሉዋቸው:- በዚያ ጠባብ ሥፍራ ላይ ሁላችንም እንድናልቅ ይፈልጋሉን? እንድናልቅ ከፈለጉ ውሰዱን:: ካልሆነ ግን እርስዎ ያውቃሉ፡ አላህ ድልን ሰጥትዎት አንባን ቢቆጣጠሩአት እንኳ ከንጉሣውያን ልጆች ሌላ የሚገኝ ምንም ነገር የለም:: ፈረስም ወታደርም የሉባትም:: ገንዘብ እንደሆነ ለአላህ ምስጋና ይግባውና ከኛ ዘንድ እንደ አፈር ነው:: ሰዎች መሸከምም አቅቷቸዋል:: ሌሎች የሐበሻ ክፍሎች መች ተነኩ! ደዋሮ፣ ባሌ፣ ሸርኸት፣ ሐድያ፣ ወጁ፣ ጉንዝ፣ ዳሞት እነኝህ ሁሉ ከተሞች ገና በቁጥጥር ሥር አልዋሉም:: አሁንም በአረመኔነታቸው ላይ ናቸው:: እነኝህ ሁሉ ከተሞች ወታደሮች፣ ፈረሶች፣ የጦር አበጋዞችና ፈረሰኞች አሉባቸው:: ወደኋላ እንመለስና ከወዚር ዓድሊና "ፈጥጋር" ላይ ከተውናቸው ሠራዊቶቻችን ጋር እንሰባሰብ ሲሉ ኢማሙ ንግግራቸውን አስተውለው ትክክል ናችሁ አሏቸው:: አንባ ለመግባት የነበራቸውንም ሐሳብ አነሱ::





"መርጋይ" በቁጥጥር ሥር ከዋለች በኋላ ገዥዋ ለሆነው ዓናንዩም ኢማሙ እንዲህ አሉት:- የዚህን አገር መንገዶች አንተ ይበልጥ ታውቃቸዋለህ:: "አንባ"ን ተውአት ብለኸን ትተናታል:: አንተ ወደ ጠቀስካቸው አገሮች (ከተሞች) ምንሄድ ከሆነ፡ መንገዱን አመላክተን:: ደብረ እዝሔር ቤተክርሲያንንም አሳየን አሉት:: እርሱም "ታዛዥ ነኝ! ቦታዋንና መግቢያ መውጫውንም አውቃለሁ" አለ::

## ኢማሙ ሠራታቸውን ይዘው ወደ ዓንቁት ምድር መጓዛቸው

ኢማሙ ከሰፈሩበት ቦታ አደረሩ:: በበነጋታው ሊንቀሳቀሱ ሲያስቡ የሡልጣን ዑመረዲን የአጐት ልጅ አውረዒ ሺሃቡዲንና ኻሊድ አልወራዲ አረፉ:: በዚሁም ሕልፈት ሰበብ ያን ቀን ሐዘን ተቀመጡ:: በሦስተኛው ቀን "አንቁት" ወደተባለች ምድር አቀኑ:: ለአራት ቀናትም ተጓዙ:: ባሕረ "ሐይቅ" አጠገብም ሰፈሩ:: ውሃውም ጣፋጭ ነው:: በመሀሉም ደሴት ይገኛል:: ደሴቲቱ ላይ ቤተክርስቲያንና የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ ሩማን፣ ኮክ፣ ሠፈርገል (ጣፋጭ ሎሚ) ወይን፣ አገዳ፣ ሙዝ፣ ዝንጅብል፣ አሪቲ እና ሌሎችም ፍራፍሬዎች የሚገኙበት የአትክልት ቦታ አለ:: ቤተክርስቲያኗ ውስጥ የአገሩ ነዋሪዎች የሆኑ መነኩሳት አሉ:: ኢማሙ የአጐታቸው ልጅ የሆነውን አሚር ዘህረቦኝ ሙሐመድን፣ አል-ወዚር ሙጃሂዲንና ዐብደናስርን ከነሠራዊቶቻቸው፣ እንዲሁም ገራድ ሳዲቅን፣ አውረዒ አሕመድንና መሰሎቻቸውን ሦስት መቶ ፈረሰኞችን አክለውላቸው ወደዚያው ላኩ::

## ኢማሙ ለአዛዥ ዘህረቦኝ ሙሐመድ ያስተላለፉት ትዛዜ

ኢማሙ ለዘህረቦኝ ሙሐመድ ሠራዊትህን ይዘህ ወደ "ደብረ እዝሄር" ቤተክርስቲያን ሂድ:: ዓናንየህ መንገድ ይመርሃል:: ወደ ጋራው ዝለቅ:: ውጊያ ካጋጠማችሁ ሳትልክብኝ አትዋጋ፡ እደርስልሃለሁ:: ለእግረኛም ለፈረሰኛም አመች የሆነን ሥፍራ ምረጥ" ሲሉ አዘዙ:: የጦር አዛዡ (አሚር) ዘህረአቦኝ ሙሐመድ "ታዛዥ ነኝ" አለ:: ወዲያውኑም ተንቀሳቀሰ:: መግሪብ ስግደት ሰዓት (ፀሐይ ስትጠልቅ) ደብረ እግዝሄር ደረሱ:: የ"አንቂት" ሠራዊቶችና የ"በደል ነስር" ሠራዊት ከተራራው ላይ ከቤተክርስቲያኒቱዋ አጠገብ መሽገው መሥፈራቸውን ተመለከተ:: በቤተ ክርሲቲያኒቷ ዙሪያም ምሽግ ተቆፍሯል:: አሚር ዘህረቦኝ ሙሐመድ ሠራዊቶችን ሲያይ ፀሐይ እስክትወጣ በዚያው አደረ:: እናም፣ ለኢማሙ የጦርነቱን ወሬ የሚነግሩ ሦስት መልዕክተኛ ፈረሰኞችን ላከ:: ፈረሰኞቹ ኢማሙ ዘንድ እንደደረሱ ስለ ጦሩ አስታወቁዋቸው:: ፀሐይ ስትወጣ ወታደሮችና የጦር አበጋዞቹ ለምን እንቀመጣለን? ሲሉ አሚሩን ጠየቁት:: ታዲያ ምን እናድርግ? በማለት መልሶ ጠየቃቸው:: ጋራውን እንውጣ ሲሉት ኢማሙ እንድዋጋ አላዘዙኝም፣ ስለዚህ ቦታ ቦታችሁን ያዙ:: የኢማሙን ምላሽ እንጠባበቅ አላቸው:: የጦር አበጋዞቹና ወታደሮቹ ቃሉን በመቀበል ፈረሶቻቸውን ጭነው ረድፍ በመያዝ ተቀመጡ:: ከዚያም መንገድ መሪው ተነስቶ ወደ ጋራው ወጣ:: ከክርስቲያኖችም ጋር ተነጋገረ:: የተቀመጥነው ደንግጠን ወይንም ፈርተን እንዳይመስላችሁ:: ኢማሙ ውጊያ ከገጠማችሁ ሳትነግሩኝ እንዳትዋጉ፣ እደርስላችኋለሁም ስላሉን





ነው:: ኢማሙን በመጠባበቅ ላይ ነን:: ነፍሳችሁን ብታድኑ ይሻላችኋል:: ኢማሙ መድረሻ አሏቸው:: ከተከሉሰባችሁ ያላችሁበትን ተራራም ሆነ ቤተ ክርስቲያናችሁን ያወድምባችኋል አላቸው:: ኢአማኒያኑ ይህን ሲላቸው በፍርሃት ራዱ:: መልዕክተኛው ዓናንየም ወደ ሙስሊሞች ተመልሶ ተቀመጠ::

## ኢማሙ ለዘህረቦኝ መሐመድ በአድኝነት መድረሳቸውና የዓንቁትና የበደል ነስር ሠራዊት መሸነፉ

ኢማሙ የዘረህቦኝ ሙሐመድ መልዕክት እንደደረሳቸው ጊዜ ሳያጠፉ ጉዞ ጀመሩ:: ከተራራው ሲቃረቡ ኢአማኒያኑ የሚነሳውን አቧራ በመመልከታቸው ሽሽት ጀመሩ:: ሙስሊሞቹ ተከትለዋቸው እያሳደዱ ይገድሏቸውና ይማርኳቸውም ጀመሩ:: ከግድያና ከመማረክ የተረፉትም ከጋራው እየወደቁ ተሰበሩ::

## ከሰባት መቶ ሃያ ዓመት በፊት ንጉስ ሰይፉ አርዓድ ያሳነጻት ደብረ እዝሄር ቤተክርስቲያን ገጽታ

ሙስሊሞች ወደ ደብረ እግዝሄር ቤተክርስቲያን በመግባት አስገራሚ ነገሮችን ተመለከቱ:: በወርቅ የተንቆጠቆጠች ቤተ ክርስቲያን ናት:: በርካታ የወርቅ ወይፈኖች አሉባት:: አንዱን ወይፈን አምስት ሰዎች ሊሸከሙት አልቻሉም::

ዘህረቦኝ ለሙስሊሞች ቤቱ ውስጥ ያለውን ሃብትና ንብረት በሙሉ አላህ ባርኮላችኋል:: የያዛችሁትን ውሰዱ:: የወርቅ ወይፈኖችን ግን

አትቅረቡዋቸው ካለ በኋላ፡ ወይፈኖቹን ውጭ እንዲያወጣ አንዱን አዘዘና በዘህረአቦኝ ፊት አስቀመጡዋቸው:: ከዚያም ወታደሮች ወደ ቤተ ክርስቲያኗ እየተጋፉ ገቡ:: ይተራመስባትም ጀመር:: የወርቁን ቅብ ከፊሎቹ በሰይፍ፣ ከፊሎቹ ደግሞ በቢላዋ መቆራረጥን ተያያዙት:: እያንዳንዳቸውም የቤተክርስቲያኒቱን የወርቅ ዝርጎችን መውሰድ ጀምሩ:: የቤተክርስቲያኗ መላው ጣሪያዋም ሆነ ወለሏ በወርቅ ንጥፍጣፍ የተለበጠ ሲሆን፣ ያሳነጻት ሰይፉ አርዓድ የተባለ የጥንት ንጉስ ነበር:: ያቃጠሉዋት ዕለት ከተገነባችበት ጀምሮ ሰባት መቶ ሃያ ዓመት የነበራት ናት:: ንጉሡ ያሣነፀባት ቀን ተጽፎባት ነበር:: ከውስጧ ካሉት የወርቅ ወይፈኖች፣ ሳህኖች ማንቆርቆሪያዎችና ሌሎች ቁሳቁሶች ውጭ ዘጠኝ መቶ ዘጠኝ ሺህ ከዘጠኝ መቶ ዘጠና ወቄት ወርቅ ጨርሳለች:: ሙስሊሞች ሁሉንም ከያዙና ቤተክርስቲያኗንም ካቃጠሏት በኋላ ወደ ኢማሙ ተመለሱ:: ኢማሙም ከጋራው አጠገብ ሰፍረው ነበር:: ከኢማሙ ጋር እንደተገናኙም ወይፈኖቹን አስረከቧቸው:: ሌሎቹን ወርቆች ሁሉ ወታደሮቹ ወሰዱ:: ኢማሙ ወደ "ሐይቅ ባሕር" በመመለስ እዚያው ሰፈሩ:: ወደ ደሴትዋ ነዋሪዎችም፤ ወደ ተገዢነት እንድትገቡ፤ ከእናንተ ዘንድ የሚገኘው ምርኮኛ ሰው አውረዒ ሐርብ አርዓድ ቢን ሰብረዲን አልሙጃሂድ የተባለውን ላኩልኝ፡ የሚላቸው መልዕክተኛ ላኩባቸው::

## አውረዒ ሐርብ አርዓድ የተባለው ምርኮኛ ታሪክ

ይህ ምርኮኛ ከሚቹ ሡልጣን መሐመድ ጋር ሆኖ ዘምቶ ነበር:: ሙስሊሞች "ድል ሜዳ" ላይ ሲሸነፉ ኢአማንያኑ የማረኩት ነው:: ንጉሱ የሡልጣኑ ዘመድ





መሆኑን ሲያውቅ ከመነኩሳቱ ጋር "ሐይቅ ባሕር" መሀል ወዳለችው ደሴት ላከው:: ክርስትና እንዲያነሡትና ወንጌልም እንዲያስጠኑት አዘዛቸው:: የእምነት መጽሐፋቸውን በቃሉ መሸምደድ እስኪችል ድረስ ተማረው:: በእነሱም ዘንድ በደሴቷ ለአሥራ ድስት ዓመታት ቆየ:: ልቦናው ግን በቀድሞው እምነቱ በእስልምና እንደፀና ነበር:: ኢማሙ ከቦታው ሲደርሱ እርሱን ለማስለቀቅ ሲሉ ነበር መልዕክተኛቸውን የላኩባቸው:: መልዕክተኛው እየዋኘ ወደ እነሱ እንደተቃረበ ድንጋይ ወረውሩበት:: ወደናንተ ተልኬ ነው እንዳትወረውሩብኝ አላቸው:: መልዕክተኛም ብትሆን አትጠጋን፤ ያ ድግምተኛ ነው የላከህ:: እዚያው በርቀት ሁነህ አናግረን" አሉት:: መልዕክተኛው ኢማሙ ያሉትን ሁሉ ነገራቸው:: እነሱ ግን "ለጌታህ ግብር አንከፍልም፣ አንገዛም፤ ምርኮኛውንም አንፈታም፤ የሚችለውን ያድርግ ጋራዎችን በእግርና በፈረስ እንደወጣ እናውቃለን፣ ይህ ግን ባሕር ነው:: እስኪ ከቻለ ወደኛ ይግባ አሉት:: መልዕክተኛው ወደ ኢማሙ ተመልሶ ያሉትን ነገራቸው::

## የሐይቅ ባሕር ደሴት ነዋሪዎችን ለመዝመት የጀልባዎች መሥራት ክስተት

ኢማሙ ታላላቅ ሰዎችን፣ ዐረቦችን፣ የመሃግብ፤ (የሰሜን አፍሪካ) የመህራ፤ ሰዎችን ሰበሰቡ:: "እኛ ከሜዳና ከጋራ በስተቀር ጉዞ አናውቅም:: ስለ ባሕር እውቀቱ ያለው ከናንተ ዘንድ ነው:: ምን ማድረግ እንዳለብን አስተያየታችሁንና የምታደርጉትን ንገሩን፤ አሏቸው:: እነርሱም እንጨት እንፈልጋለን፣ ከዚያ የምንሠራውን ያያሉ አሏቸው:: ኢማሙ እንጨት እንዲያቀርቡላቸው ወታደሮቹን አዘዙ:: ብዙ እንጨት

ሰበሰቡ:: "ገመድም ይቅረብልን አለ:: ኢማሙ እንዲያቀርቡላቸው አዘዙ:: በአንድ ሰዓት ውስጥ አሥር ሺ ያህል ገመዶች ቀረቡላቸው:: አሁን ያሰባችሁትን ሥሩ:: እንጨቱም ገመዱም ቀርቦላችኋል አሏቸው:: ዐረቦች ተሰበሰቡና ያዘዙንን እንሠራለን ለሥራው ግን ሦስት ወይም አራት ቀናት እንዲሰጠን እንፈልጋለን:: ኢማሙም ይሁንታቸውን ገለፁላቸው:: ሦስት ትልልቅና ሁለት ትንንሽ ጀልባዎችንም ሠሩ:: ሠርተው እንዳጠናቀቀም ኢማሙ አንዱን ጀልባ ባሕሩ ላይ ሞክሩትና ልመልከተው አሏቸውና፣ አንዷን ትንሽ ጀልባ ወደባሕሩ መሐል ከተቱት:: በዝግታ ስትንቀሳቀስ ኢማሙ ተመለከቱ:: በዚህ ጀልባ ከተጓዛችሁ ከደሴቷ ከመድረሳችሁ በፊት በድንጋይ ናዳና በቀስት ፍላጾ ይጨርሷችኋል:: ሌለ የምትሠሩት ካላችሁ በስተቀር ይኼኛው አይጠቅመንም፣ ሲሏቸው፣ ዝም አሉ:: ከመሐከላቸው ስሙ ጃውሻ አቡ በሻረህ የተባለ ተነስቶ እኔ ሐሳብ አለኝ አለ:: ኢማሙም ሐሳብህን አቅርብ አሉት:: ላም አርዳችሁ ግፈፉትና ስልቻ ሥሩበትና ስልቻውንም ንፉት፣ አላቸው:: ብዙ ሥልቻም ሥሩ:: ይህን ካደረጋችሁ በኋላ ምን እንደምታደርጉ አሳያችኋለሁ አለ:: እንደተጠየቀው ስልቻዎች ተሠርተው ቀረቡ:: በእያንዳንዱ ጀልባ ሥር የተነፉና አፋቸው የታሠሩ ስልቻዎች እንዲንጠለጠሉ ተደረጉ:: በእያንዳንዱ ጀልባ ላይ ዘጠኝ ስልቻለች ታሠሩ:: ሦስቱ ከፊት ለፊት፣ ሦስት ከመሐልና ሦስት ከጀልባው ኋላ ከታሰሩ በኋላ ኢማሙ አንዷን ጀልባ ባሕር ላይ ሞክሯት ሲሉ አዘዙ::አንዱን ጀልባ አስገብተው ሲወጡበት እንደወሥፈንጥር (ቀስት) ተወርውሮ ተጓዙ:: ኢማሙ ይህን ሲያዩ ተደስተው የፈለግኩት ይህንኑ ነበር አሉ::





ይኸ ሰው በሐበሻ የሚገኙ የባሕር ሰዎች በቋንቋቸው "ለኺይ" የሚሉት እየሠሩ የሚሸጋገሩበትን አይቶ ነበር:: ከዚያም ኢማሙ ከቤተ ዚያድ ለሆነው የአልመህራ ሰዎች ተቀዳሚ የሆነው አሕመድ ቢን ሡሌይማን አል መህሪን፣ አንተና ባልደረቦችህም ተዘጋጁ ሲሉ አዘዙ::

ኢማሙ ባልደረቦቻቸውን በማበረታታት አሁን ከዐረቦች ጋር ባሕር ላይ የሚጓዝ ማን ነው? አሏቸው፡ በአላህ ፈለግ ባሕር ላይ የተጓዘ ሰው የሚያገኘውን ምንዳም ነገሩዋቸው:: የተወሰኑ ሰዎች ተነሱና "እኛ ነፍሳችንን በአላህ ፈለግ ልናበረክት ቃልኪዳን ከኢማሙ ጋር እንገባለን አሉና፡ የኢማሙን እጅ በመያዝ ቃልኪዳን /በይዓ/ አደረጉ፣ አላህ ደግ ያስብላቸው:: ሙስሊሞች ሁሉ ዝግጅት በማድረግ:: እያንዳንዳቸውም ጦሮቻቸውን፣ ሰይፎቻቸውንና ቀስቶቻቸውን ለውጊያ ያዘጋጁ ጀመር::

## ዕለተ ረቡዕ

አሕመድ ቢን ሡሌይማን አል መሡሪ እንዲህ አለ፡- አሁን የዓስር ወቅት ነው:: አሁኑኑ ጉዞአችንን ከጀመርን ይጨልምብናል:: በሌሊት ውጊያ አይሆንም:: ያኔ እኛ ከባሕሩ መሐል ነን:: በተጨማሪም ቀኑ ረቡዕ ነው:: የባሕር ሰዎችም እንዲህ ይላሉ፡- ረቡዕ አይዘልቅም:: በእነሱ ዘንድ ረቡዕ ቀን ገደቢስ ነው:: ነገ ሐሙስ በመሆኑ አላህንና መልዕክተኛውን የሚያስደስት ውጊያ እንከፍትባቸዋለን የሚል ሐሳብ ሠነዘረ:: ኢማሙ ይህን ሐሳብ ሰምተው፡ በአላህ ፈቃድ ይህ ይሆናል በማለት ወደ ድንኳናቸው ተመለሱ:: ያን ዕለት አላህን በፀሎት ሲማፀኑ አደሩ::

## የደሴቷ ነዋሪዎች ፈርተው ያላቸውን ሀብት በሙሉ ለኢማሙና ለሠራዊታቸው አስረክበው፡ ለራሳቸውና ለቤተክርስቲያኗ የሰላም ዋስትና ስለ መሻታቸው

የደሴቷ ነዋሪዎች ክርስቲያኖች፡ ሙስሊሞቹ ለሙከራ የጋለቢት ጀልባ እንደ አሞራ ስትበር ባዩዋት ጊዜ በፍርሃት ውስጣቸው ራዱ። ምክክርም አደረጉ። እነዚህ ሙስሊሞች አይተነው የማናውቀውን ነገር ሰርተዋል። ይህ የዐረቦች ሙያ ውጤት ነው። መድፍም አላቸው። የሚሉትን ካልተቀበልን በኃይል ይገቡና እኛንም ይገድሉናል። ቤተክርስቲያናችንንም ያቃጥሏታል። በእነሱም ላይ ኃይል የለንም። ስለዚህ እርቅ ይሻለናል ተባባሉ። አባታቸው ፓትሪያርኩ እንዲህ የሚል ሐሳብ አቀረበ፡- ከኛ ዘንድ ያለውን ይህን ምርኮኛ ወደእነሱ ዘንድ እንላከው፣ ለኛም ለቤተክርስቲያናችንም የደህንነት ዋስትና ይቀበልልን። ያለውን ሀብት በሙሉ ይውሰዱት ብሎ፣ ምርኮኛውን ጠሩትና አነጋገሩት። በሐሳባቸው ተስማማ። በሌሊት ታንኳ ላይ አሳፍረውና ሁለት ሰዎችን ጨምረው ከባሕሩ ለሁለቱ ሰዎች እንዲህ አሉዋቸው፡- ዳርቻው ላይ አውርዱትና ሙሥሊሞች ስለማንነታችሁ ሳያውቁባችሁ እናንተ ተመለሱ። የታዘዙትንም በመተግበር ሌሊት ዳርቻው ላይ አውርደውት በታንኳቸው ወደ ደሴቷ ተለሱ። ሲነጋ ኢማሙና ተከታዮቻቸው የንጋት ስግደት በሕብረት ለመፈፀም ወጡ። ስግደታቸውን እንደፈፀሙ ኢማሙ ወደ ድንኳናቸው ተመለሱ። አብስማኑር ከርሳቸው ጋር ቁርስ ይመገብ ዘንድ ላኩበት። አብሰማኑር ወደ ኢማሙ በመሄድ ላይ እያለ ከተላከው ምርኮኛ ጋር ተገናኙ። አንተ ማን ነህ? አለው። ሐርብ አርዓድ





ኢብን አውረዒ ስብረዲን ነኝ አለ። የት ነበርክ? ሲልም ጠየቀው። ከደሴቷ ላይ ምርኮኛ ነበርኩ፡ የደሴቷ ነዋሪዎች ወደ ኢማሙ ልከውኝ ነው አለ። አብሰማኑር ኢማሙ ዘንድ በመግባት ምርኮኛው ያለውን ነገራቸው። የት አለ? መጀመሪያውኑ መልዕክተኛ የላኩባቸው እርሱን እንዲልኩልኝ ነበር አሉ። በሩ ላይ ቆሟል አለ አብስማኑር። አስገባው ሲሉ አዘዙት። ኢማሙ ዘንድ አስገባው። ኢማሙ ሰውየውን በምርኮኝነት በመቆየቱ ሳቢያ ተቀይሮ ሲያዩት ጥልቅ ሐዘን ተሰማቸውና አለቀሱ። ምርኮኛውም አለቀሰ። ከዚህች ደሴት ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ቆየህ? በማለት ኢማሙ ጠየቁት። አሥራ ስድስት ዓመታት ቆይቻለሁ። ኢአማኒያኑ ዐረቦች የሠሩትን ጀልባ ሲመለከቱ ፍርሃት አደረባቸው። እናም በአማላጅነት ላኩኝ። ሀብታቸውን ሁሉ ወስደው እነርሱን ላለመግደልና ቤተክርስቲያናቸውንም ላለማቃጠል ዋስትና እንዲሰጧቸው ይፈልጋሉ ሲል መለሰላቸው። ኢማሙ አጠገባቸው ያሉ ባልደረቦቻቸውን አነጋገሩ። እነሱም አሚር አቡበክር ቀጪን፣ አልወዚር ሙጃሂድና አብሰማኑር ነበሩ። ያቀረበውን የእርቅ ሐሳብ ሰምታችኋል። ምን ትላላችሁ? አሏቸው። ሊጫወቱብን ይፈልጋሉ። ሁሉንም ሀብት አያወጡልንም አሉ። ወሬያችሁን ተውት፣ የላኩልን ይህ ምርኮኛ ከጋራ ወርቅ የበለጠ ዋጋ አለው፡ አሏቸውና፡ ለምርኮኛውም ወደነርሱ ተመለስና እንዳላችሁት ይሆናል በላቸው አሉት። ምርኮኛው ጀልባ ላይ ተሳፍሮ ወደ ደሴቷ አቀና። ደሴቷ ሲቀርብ ጮኾም አናገራቸው። ቃላችሁን ከጠበቃችሁ ለናንተም ለቤተክርስቲያኗም ዋስትና ተቀብየላችሁ መጥቻለሁ። አባታችሁ ፓትሪያርክ ይውረድና የዋስትናውን ውል ይዋዋል፡

አላቸውና ወደ ኢማሙ ተመለሰ። ኢማሙ ወደ ባሕሩ ዳርቻ ቀረቡና የዐረብ፣ የመህራና የመግሪብ ሰዎች፣ ታላላቆች ሰዎችም፡ ሸሪፍ ኑር ኢብን አህመድና ሸሪፍ ሙሐመድ ሀንዱል እንዲሁም የባሕሩ ጦር ወታደሮች ቦታ ቦታቸውን ያዙ። በዚያው ወቅት አባታቸው ፖትሪያርኩ ከቤተክርስቲያኗ ወጣና ታንኳ ላይ ተሳፈረና ኢማሙ ዘንድ ደረሰ፡ ከፊታቸውም ቆመ፡ መሬት ሊስም ፈለገ። ኢማሙ ግን ለሰው አትስገድ ሲሉም ገሰፁት፤ ራሱን ቀና አደረገ። ኢማሙም የመጣህበትን ጉዳይ ተናገር አሉት። መነኩሳቱ በሙሉ ላትገላቸው፤ ቤተክርስቲያናቸውንም ላታቃጥል ዋስትና እንድትሰጣቸው ይፈልጋሉ፣ አለ። ኢማሙም የቤተክርስቲያኗም ሆነ ሌላም ሀብት ላትደብቁ ቃል ከገባችሁ ዋስትና እሰጣችኋለሁ አሉት። ዋስትና ከሰጣችሁን ታዛዦች ነን። ወደ ደሴቷ ሄጄ ሀብቱን ሁሉ ላምጣላችሁ አለ። አንተ ፖትርያርክ አናምንህም። ይልቅ የኛን ሰዎች ካንተ ጋር ወደ ደሴቷ ታስገባቸዋለህ። ያገኙትን ሀብት ሁሉ ይወስዳሉ አሉት። ያንተ ሰዎች የግድ ደሴቷ ውስጥ መግባት ካለባቸው ቤተክርስቲያናችንን እንዳይወሯት፤ ቃልህንም እንዲጠብቁ ንገርልን በማለት ፖትሪያርኩ ተማፀነ። ኢማሙም እኔ ዋስትና ከሰጠሁህ ማንም ዋስናዬን ሊያፈርሰው አይችልም አሉት። ፖትሪያርኩም ተደሰተ። ኢማሙ ለዘህረቦኝ መሐመድ አሁኑኑ አንተ ሂድ ብለውት፤ ከዐረቦች፤ የመህራዎችንና የመግሪባውያንን ሰዎች፣ ባላባቶችንና በርከት ያሉ የባሕር ወታደሮች አብረውት ይሄዱ ዘንድ አደረጉ። ከፖትርያርኩ ጋር በእግርህ ወደ ደሴቷ ግባ። ቤትክርስቲያኗን አታቃጥል፣ መነኩሳቶችንም አትግደል። ከቤተክርስቲያኗም ከደሴቷም ውስጥ ያሉ





ንብረቶችን በሙሉ አውጣ። ቤሳ ቤስቲን እንዳትተው" ሲሉ ኢማሙ አዘዙት። እሱም ትዕዛዙን ተቀብያለሁ ሲል ታዛዥነቱን አረጋገጠ።

## የኢማሙ ሠራዊት ከደሴቷ ቤተክርስቲያን ያሰባሰበውን ሀብትና ቅርፃ ቅርፆች የማከፋፈሉ ትውስት

በጀልባዎቻቸው ተጉዘው አሚር ዘህረቦኝ ሙሐመድ ወደ ቤተክርስቲያኗ ገባ። ቤት ውስጥ ያለና ጉድጓድ ውስጥ የተቀበረ ሀብቶችን በሙሉ አወጣ። የወርቅና የብር መስቀሎች ብቻ በመቶ ሰው የሚሸከም ነው። ቁጥር ስፍር የሌላቸው የወርቅ ቀንዲሎችና ሠንሠለቶቻቸው ተገኙ። እያንዳንዱ ሙስሊም እግረኛ ሦስት መቶ ወቄት የሚመዝን ታቦትና የወርቅ ሳህኖችን ያዘ። አንዱ ሳህን ሦስት ሰዎችን የሚያጠግብ ምግብ ይይዛል። በርካታ ቁሳቁሶችንና የሐር ጨርቆችን አወጡ። ዘህረቦኝ ደሴቷ ውስጥ ሀብት ሲሰበስብ አደረ። ሲነጋ ሦስት ጀልባ ሙሉ ወርቅና፣ ብር ጭኖ ወደ ኢማሙ ላከ። በጀልባዎቹ ከመሐከል ሁለት ሰዎችና ከፊት ለፊት ሦስት ሰዎች ብቻ ነበሩ። ቀሪው ቦታ በሀብት ተሞልቷል። እያንዳንዱ ጀልባ 150 ሰዎችን ማሳፈር የሚችል ነው። ጀልባዎች ከኢማሙ ፊት ተራገፉ። ኢማሙ በእጅግ ተገረሙና ከዚህ ቀደም ያዩትን ሀብት ረሱት። ጀልባዎቹ ለሁለተኛና ለሶስተኛ ጊዜ ወደ ደሴቲቷ ተመልሰው ሀብት ተጫነባቸው። ጭነታቸውም እንደፊተኞቹ ነበር። ወደ ደሴቷ ተመልሰው የቀሩ ሰዎችን ሁሉ አመጡ። ዘህረቦኝ በሁለተኛው ቀን ተመለሰ። ከኢማሙ ጋር ፀሐይ ስትጠልቅ ተገናኙና ወደ ቦታውም ተመለሰ። ሲነጋ

ኢማሙ አስጠሩትና የተገኘውን ሀብት አከፋፈሉ:: አንድ ድርሻ ለዐረቦች፡ አንድ ድርሻ ለዘሀረቦኝ መሐመድ፡ ለባሕር ወታደሮችም ሰጧቸው:: ቀሪውን ሁለት ድርሻ ለሙስሊም ወታደሮች አከፋፈሉ::

## ኢማሙ ከነሠራዊታቸው ወደ ዋሲል ምድር ስለመጓዝ

በአራተኛው ቀን ኢማሙ ከነሠራዊታቸው "ፈጥጋር" ላይ የተውትን ወዚር ዓድሊን ለማግኘት ተጉዘው ወደ "ዋሲል" ምድር ደርሰው አደሩ:: በነጋታው ሙስሊሞቹን ሰበሰቡና ካገኛችሁት ምርኮ አንድ አምስተኛውን ግምጃ ቤት አስገቡ:: አደራ ማጭበርበር እንዳትፈጽሙ አሏቸው:: ሁሉም በአንድ ድምጽ ሀብታችንን እናምጣልዎትና እርስዎ ራስዎ አንድ አምስተኛውን ቀንሰው ቀሪውን ይመልሱልን አሏቸው:: አላህ ይመለከታችኋል፤ እያንዳንዱ አለቃ በስሩ ካሉት ወታደሮች አንድ አምስተኛ ይሰብስብ አሏቸው:: ሁሉም የጦር አለቃዎች በየጦራቸው ተበተኑና፤ ከወታሮቻቸው አንድ አምስተኛ ሰብስበው ለኢማሙ አቀረቡላቸው:: በ"ሪጥል" (የክብደት መመዘኛ ሲሆን አንድ ሪጥል 2564 ግራም ነው::) ሲመዝኑት ቁጥር ስፍር የሌለው ሃብት ሆነ:: ከቢር አቦኝን በንብረቱ ላይ ወከሉት:: ጸሐፊና ሂሣብ አዋቂም ነበር:: እሱም "ዋሲል" ላይ ከወታደሮች አንድ አምስተኛ ድርሻ በመሰብሰብ ስድስት ቀናትን አሳለፈ::





## የኢማሙ ወደ ቤተ አምሐራ መጓዝ

ኢማሙና ሠራዊታቸው ተጉዘው ወደ "ገጅም" ምድር ገቡና "አብሽሎ ዛፍ" ከተባለ ቦታ ላይ ሰፈሩ:: ከዚያም ኢማሙ የባሕር ወታደሮችን ይዘው ወደ ቤተ አምሐራ ተጓዙ:: ምክንያቱም ሁለት ቤተክርስቲያኖች ቀርተዋቸው ስለነበር ነው ወደ ቤተ አምሐራ የተመለሱት:: ከቤተክርስቲያኖቹ አንዷ "መካነ ማርያም"፣ ሌላኛዋ ደግሞ "ደብተራ ማርያም" ይባላሉ:: ለሰፈሩበት ቦታ አልወዚር ኑርን በጣብያው እንዲቆዩ አደረጉ::

ቤተ አምሐራ እንደደረሱም አብያተ ክርስቲያናትን አቃጥለው ወደ ሰፈሩበት ቦታ ተመለሱ:: ሳይወድ የሠለመ አይብሥ ለሐጤና እንዲሁም አበጋዝ ኢሥላሙዋ በዐስር ወቅት (አስር ሰዓት) አካባቢ ሸሽተው፤ ንጉሱን ፍለጋ ወደ ቤተ አምሐራ አቅጣጫ ተጓዙ::

## ኢማሙ በገደም ምድር ሐንቡር ላይ መሥፈራቸውና የበር ሠዕድ አዲን ልዑካንን መቀበላቸው

ኢማሙና ሠራዊቱ የ"ጐጃምን" ምድር ለቀው ከጃዲም ምድር "ሐንቡራህ" ወደተባለች ከተማ ተጉዘው እዚያው ሰፈሩ:: የሐገሩ ሰዎች ከሙስሊሞች ጋር የሰላም ውል የተዋወሉ በመሆናቸው ሙስሊሞችን በመልካም ሁኔታ አስተናገዱ::እዚያው እንዳሉም የበር ሰዕደዲን ሰዎች ከቦታው ደረሱ::ስጦታም ይዘው ከመጡት ሰዎች መሐል የዘይላ ገዥ ወረጋይ አቦኝና ባልደረቦቹም ይገኛሉ:: ኢማሙ ወደ ሡልጣን ዑመረዲን ልከውት የነበረ መልዕክተኛም ወሰን ሰገድ

የመገደሉን ብሥራት ይዞ መጣ:: ኢማሙ ወደ እነርሱ እስኪደርሱም የመንደሩዋ ነዋሪዎች ዘንድ ቆዩ:: እንደደረሱም ኢማሙ ስለ በር ሠዕድዲን ዜናዎች፣ እናም ወዚር ዓድሊ የት እንደሚገኙ ወሬ ሰምተው እንደሆነ ጠየቃቸው:: ወዚር ዓድሊ "ፈጥጋር" ውስጥ እንደለ ወሬውን መንገድ ላይ ሰምተናል:: የበር ሰዕደዲን ሰዎች (ነዋሪዎችም) ደህና ናቸው፤ አሉዋቸው:: ኢማሙ የ"ጃንዘለቅ"ን ገዥ ገራድ ዑስማንን ወደ ወዚር ዓድሊ ላኩት:: ድልሰገድና አውረዒ ዑመርንን ጨምሮ አብረውት የሚሄዱ ሰዎችን ከ50 ፈረሰኞች ጋር አዘጋጁለት:: የትም ቢሆን ሂደህ አግኘው፣ አላህ የሰጠንን ድልና ስኬትም ግለጽለት:: ልጆቻችንና ሴቶቻችንንም ይዞ ወደ "ደብረብርሃን" እንዲመጡና እዚያ እንድንገናኝ ንገሩት አሏቸው:: በዚያው ቀን ወዚር ዓድሊን ፍለጋ ወደ "ፈጥጋር" ምድር ተንቀሳቀሱ::

ሸሪፍ አህመድ አልቀዲሚ በመታመሙ ኢማሙ ሐንቡራህ ውስጥ 10 ቀናት ተቀመጡ:: ሸሪፍ አህመድም ሲሞት እዚያው ቀበሩት:: ኢማሙና ፈቂህ አቡበክር፣ አልአርሹኒ፤ እናም መላው ሙስሊሞች ሰገዱበት፣ ከዚያም ሐንቡራህን ለቀው "ጅደም" ምድር ውስጥ ወደምትገኘው ወደ"ካሳያህ" ተጓዙ:: የ"ይፋት" ሰዎች ከመሪዎቻቸው አዝማች ፈስኸ ጋር መጡ:: ኢማሙም ስለ ሐገሩና ስለኢአማኒያኑ ጠየቋቸው:: እርስዎ ከኛ ከሄዱ በኋላ ብርቱ ፈተና ገጥሞን ነበር:: አሁን ግን ለአላህ ምስጋና ይግባው በድልንና በክብር፣ እርስዎም ሀገራችን ደርሰውልናል:: ከሃዲያን እስካሁን ያደረሱብን እዳው ገብስ ነው፣ "ካሣያ" ለአገራቸው ቅርብ በመሆኑዋ ነው፤ አሉዋቸው:: በዚህ ጊዜ ኢማሙ ተጨማሪ ወታደሮች አክለውለት አውረዒ አቦኘን ለ"ይፋት" ምድር ሾሜሃለሁ:: ከይፋት ሰዎች ጋር ሂዱና እዚያው ተቀመጡ ሲሉ አዘዙ:: አውረዒ አቦኝም





ታዛኘ ነኝ ሲል ተቀበለ:: ሠራዊቱን ይዞም ወደ ይፋት ተንቀሳቀሰ:: ኢማሙ ወደ "መንዝ" መጥተው ተቀመጡ:: አብስማኑርንም፡ የዓድሊን ወሬ ያልነው ቦታ መጥቶ እንደሆነ እዚያው እንገናኝ ዘንድ አጠያይቅ በማለት ላኩት::ሠላሳ ፈረሰኞችንም አክለውለት ወደ "ደብረብርሃን" ተጓዙ::

## ወዚር ዓድሊ "ፈጥጋር" ውስጥ ሐንቡራህ ላይ ሠፍሮ ወደ ደዋሮ የጦር ቡድን ማዝመቱ

ዓድሊን በተመለከተ ኢማሙ ወደ ቤተ አምሐራ ሲጓዙ የተሰባጠሩ የጦር አበጋዞችን ሰበሰበና "ፈጥጋር" ውስጥ "ሐንቡራህ" በተባለች መንደር ሰፈረ:: ወዚር ዓድሊ፤ ለአውራዒ ኑር ሰባ ፈረሰኞችን አካትቶለት ወደ "ደዋሮ" ሂዱ ብሎም አዘዛቸው:: ከእነዚሁም ገራድ ሽምዑን፣ ገራድ አህመድ ኢብን ላድ ዑስማን፣ ገራድ ዘይናይ፣ ገራድ ሲዲቅና መሰሎቻቸው ተካተዋል:: አዋሽ ወንዝ እስኪደርሱም ድረስ ተጓዙና፤ ወንዙን ውሃ ሞልቶ አገኙት:: በወንዙም አጠገብ የእልማያን አረመኔዎች ጦርና የኢአማኒያዝ አዝማቾች፤ ከእነዚሁም የወጅ ገዥ አዝማች ፋንዔልና የ"ሊጋባ" ገዥ አርኪየህ ይገኙባቸው ነበር:: ከወንዙም በላይ በረድፍ ተሠልፈዋል:: በመሐላቸው ወንዝ ስላለ ሙስሊሞች ወደነርሱ መድረስ አልቻሉም:: ሦስት ቀናት ተቀመጡ:: ኢአማኒያኑ በሌሊት ቀስት ያስወነጭፉባቸ ነበር:: በመጨረሻ፤ ለዓድሊ አዋሽ ወንዝ ደርሰናል፤ ሞልቶም አገኘነው:: በጐኑ ሁለት የጦር አበጋዞች ከነሠራዊታቸው ሠፍረዋል፣ ወደነርሱ እንዳንሄድ ውሃው አግዶናል፤ የሚል መልዕክት ላኩበት:: ዓድሊ እዚያው በነበረበት ሥፍራ እንደአለ